# አማርኛ

## እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ

## የመምህር መምሪያ

## አንደኛ ክፍል


አዘጋጆች

እሸቱ ኣጋ

አንበሴ በቀለ

አርታኢ

መላኩ ጽጌ

ትጃኒ ምትኩ

ጥራት ተቆጣጣሪዎች

በርናባስ ደበሎ

ይልፋሸዋ ጥላሁን

ታምሩ ገለታ

ግራፊክስ

ሰለሞን አለማየሁ ጉተማ

© የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ 2014 ዓ.ም.

ይህ መፅሐፍ በ2014 ዓ.ም በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ እና በነቀምቴ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በትብብር የተዘጋጀ ነው፡፡ የመጽሐፉ ህጋዊ የቅጂ ባለቤት የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ ©2014 ዓ.ም. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፡፡

የዚህን መጽሐፍ ክፍል በተለያዩ መሳሪያዎች ያለባለቤቱ የቅድሚያ ፈቃድ እንደገና ማሳተም፣ ማሰራጨት፣ ማከማቸትና መልሶ መጠቀም አይቻልም፡፡

# ማውጫ


መግቢያ........iv

ምዕራፍ አንድ፡ ቤተሰብ ........1

ምዕራፍ ሁለት፡ ቤት ........9

ምዕራፍ ሶስት፡ ትምህርት ቤት ........16

ምዕራፍ አራት፡ ጓደኛሞች ........24

ምዕራፍ አምስት፡ ተክሎች ........32

ምዕራፍ ስድስት፡ የመንገድ ደህንነት ........39

ምዕራፍ ሰባት፡ ተረቶች........46

ምዕራፍ ስምንት፡ ምግብ ........59

ምዕራፍ ዘጠኝ፡ የግል ንጽህና........70

ምዕራፍ አስር፡ የቤት እንስሳት........79

## መግቢያ

ይህ የመምህር መምሪያ የተዘጋጀው በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን ለፈቱ ተማሪዎች ማስተማሪያ የተዘጋጀውን የተማሪ መፅሐፍ መሠረት በማድረግ ነው። በመሆኑም በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን ይዘቶች እንዴት ማስተማርና ተግባራቱን እና መልመጃዎቹን እንዴት ማሠራት እንደሚገባ ሁሉአቀፍ የሆነ ጥቆማ ለመምህር ያቀርባል። ከዚህም ሌላ የክፍል አደረጃጀትና አስተዳደሩ ምን መሆን እንደሚገባው አቅጣጫ ያስቀምጣል። በዚህም መምህራን የየክፍላቸውንና የየተማሪዎቻቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት መምሪያውን ተግባራዊ ያደርጉታል ተብሎ ይጠበቃል።

## የመምሪያው አደረጃጀትና ይዘት

ይህ የመምህር መምሪያ ከላይ እንደተገለፀው የተማሪ መጽሐፍን በመንተራስ የተዘጋጀ በመሆኑ የይዘት አደረጃጀቱም ይህንኑ የተከተለ ነው። ስለሆነም በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ የተቀመጡት ምዕራፎች በቅደም ተከተል ቀርበውበታል። በየምዕራፉ ለሚከናወኑ የማዳመጥ ተግባራት የተዘጋጁት ምንባቦችም በመምህር መምሪያው ተካተዋል። አስፈላጊ ይሆናሉ ተብለው በታሰቡ ይዘቶች ላይም ተጨማሪ ማስታወሻዎች የተሰጡ ሲሆን፣ በየደረጃው ለቀረቡ መልመጃዎችም ናሙና መልሶች እንዲካተቱ ሆኗል። እነዚህ ናሙና መልሶች የቀረቡትም በቋንቋ ትምህርቱ አሰጣጥ ወቅት ወጥነት ያለው አካሄድ እንዲኖር ታስቦ ሲሆን፣ መምህርና ተማሪዎቹ እንደየሁኔታው (አውዱ) የሚያቀርቧቸው ተጨማሪ ምላሾችም ከግምት የሚገቡ ናቸው።

## ልዩ ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገቡ ነጥቦች

- የየትኛውም ክፍል ጊዜ ትምህርት ሲቀርብ አራቱን የቋንቋ መሠረታዊ ክሂሎች በተመጣጠነና በተቀናጀ መልኩ ያካተተ ሊሆን ይገባል፤
- የትምህርቱ አቀራረብ አሳታፊ፣ ትብብራዊ እና ተግባቦታዊ የማስተማር ዘዴ መርህን የተከተለ ሊሆን ይገባል (ለምሳሌ ተማሪን ማዕከል ያደረገ መሆን)፤
- የልሥራ፣ እንሥራ፣ ሥሩ አካሄድ ሁልጊዜም ይተግበር፤ በተለይ አዲስ ርዕሰ ጉዳይ እና መልመጃ ሲቀርብ ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፤
- ሁሉም ተማሪዎች ከተመሳሳይ ዳራ ያልመጡ ወይም ተመሳሳይ ልምድ የሌላቸው

- ስለሚሆን በመማር ወቅት የሚቸገሩ ተማሪዎችን ቀስ በቀስ የማብቃት ስልትን (scaffolding) በመተግበር ማገዝ ያስፈልጋል፤
- ልዩ ተሰጥዖ ያላቸው ተማሪዎችና ላቅ ያለ አፈፃፀም የሚያሳዩ ተማሪዎች ሲያጋጥሙንም ችሎታዎቻቸውን ለማዝለቅ ማበረታትና ተጨማሪ ተግባራትን እያዘጋጁን በመምጣት ማትጋት ይገባል፤
- በክፍል ተሳትፎ ወቅት ጥንቃቄ የተሞላበት አካሄድን መከተል ይገባል (የባህል፣ የሀይማኖት፣ የፆታ ወዘተ አካታችነትን ከግምት ማስገባት)
- ተማሪዎቹ በሚማሩበት አካባቢ በሌላ መልኩ የሚተረጎም ቃል ወይም አገላለፅ ወይም ምስል ሲያጋጥም (ታቡ የሆነ) በሌላ መተካት/ማለዘብ
- ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የአካቶ ትምህርትን መርህ በመከተል ተገቢ እገዛ ሊያደርጉላቸው ይገባል፡፡

# ምዕራፍ አንድ
# ቤተሰብ

(18 ክፍለ ጊዜ)

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- መምህር ስለ ህትመት ግንዛቤ የሚያደርገውን ገለጻ ካዳመጡ በኋላ ለጓደኞቻቸው ሀሳቦችን ያጋራሉ፡፡
- ተዘውታሪ ቃላትን ይጠቅሳሉ፡፡
- አዳዲስ ድምጾችን/ፊደላትን(ሀ፣ለ፣መ) ከነዝርያቸው ይለያሉ፡፡
- ሁሉንም ፊደላት በቅደም ተከተላቸው አስተካክለው ያስቀምጣሉ፡፡
- የእርሳስና የብዕር አያያዝን ይማራሉ፡፡

## 2. ዝርዝር ይዘቶች

- የህትመት ግንዛቤን አዳምጦ መናገር
- የተመረጡ ሶስት ድምጾች (ሀ፤ለ፤መ) እና የፊደሉ ግንኙነት
- ተዘውታሪ ቃላት ( የቃላት ትምህርት )
- ድምጾችን ማንበብና መጻፍ
- በተገቢ አገላለጽ፣ በፍጥነት፣ በትክክለኛነትና በመረዳት ማንበብ
- ዘወትር የሚታወቁ ድምፆችን መጻፍ

## 3. የማስተማሪያ ብልሀቶችና መሳሪያዎች

መምህር የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ይፈትሻል (ከማዳመጣቸው በፊት መምህር የህትመት ግንዛቤ ጥያቄዎችን ማቅረብ)፡፡

**ተማሪዎች፡** የቀደመ ዕውቀታቸውን ያንጸባርቃሉ፡፡

**መምህር፡** ተማሪዎች የተመለከቱትን ርዕስ፣ ስዕሎችና ቁልፍ ቃላትን መሰረት አድርገው ስለምን እንደሚያዳምጡ እንዲገምቱ መጠየቅ እና የተማሪዎችን የመማሪያ መጽሀፍ በመያዝ ስለመጽሃፉ ክፍሎች የሚያስረዱ ቃላት (ርዕስ፣ሽፋን) መናገር፡፡

**ተማሪዎች፡**የጽህፈትን አቅጣጫ ይከተላሉ (ከግራ ወደ ቀኝ፣ ከላይ ወደታች፣ ስለመጽሀፍ፣ ስለብእርና እርሳስ አያያዝ ይለማመዳሉ)፡፡ ስለህትመት ግንዛቤ ለመጨበጥ ከጓደኞቻቸው

ጋር ይሰራሉ፤ ስለቤተሰቦቻቸው የሚያስረዱ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፡፡ የቤተሰብ አባላትን በዛፍ ስዕል መልክ ስለው ያስቀምጣሉ (የተማሪዎችን የመማሪያ መጽሃፍ ተጠቀም)፡፡

**መምህር፡** በተመሳሳይ ድምጾች የሚጀምሩ ቃላትን እንዲናገሩ ይጠይቃል፡፡ (ድምጾችን/ ፊደላትን፣ የቃላት ካርዶችን፣ ባለቀለም ወረቀቶችን፣ ካርቱን ምስሎችን እና ወዘተ ምስሎችን መጠቀም፡፡

**ተማሪዎች፡** ሁለት ቃላት በተመሳሳይ ድምጽ በመነሻ ወይም በመድረሻ የሚጀምሩ ወይም የሚጨርሱ መሆናቸውን መለየት፡፡

**መቁጠር፡** ተማሪዎች በቃላት ውስጥ ባሉት ድምጾች ብዛት መጠን ያጨበጭባሉ፡፡ (የቃላት ካርድና ጥቁር ሰሌዳን ተጠቀም)

**ተመሳሳይ የድምጽ ቃና፡** ተማሪዎች ተመሳሳይ የድምጽ ቃና ያላቸውን ቃላት ይፈጥራሉ፤ መምህር ተማሪዎችን ምላሽ በሰሌዳ ላይ ይጽፋል (የቃላት ካርድና ሰሌዳ ተጠቀም)

**ተዘውታሪ ቃላት፡** መምህር ተዘውታሪ ቃላትን ትርጉም በቡድን በማወያየት ይሰጣሉ፡፡ ተማሪዎች ከሚደመጡ ጽሁፎች ጋር ለማዛመድ በመሞከር ይፈልጋሉ፡፡

**ቀስ በቀስ ማብቃት፡** ሀ. መምህር ፊደላትን ይጠራል፡፡

ለ. መምህር ተማሪዎችን ፊደላቱን እንዲጠሩ ይጠይቃል፡፡

ሐ. ተማሪዎች ድምጾችንና ፊደላትን ማገናኘት ይለማመዳሉ፡፡

**እንቅስቃሴ፡** በእንቅስቃሴ ድምጾችን ያገናኛሉ፡፡ ይህ ተማሪዎች አካላቸውን እንዲያንቀሳቅሱ ይጠይቃል፡፡

**የአፍ እንቅስቃሴ፡** ይሄ ተማሪዎች ድምጾች እንዴት እንደሚፈጠሩ ያስተምራቸዋል፡፡

**መጻፍ፡** ሀ. መምህር ድምጾችን ይጠራል ከዚያም ያጣምራል፡፡(የታወቁ የፊደላት ድምጾችን) ተማሪዎች፡ ፊደላትን ከድምጾቻቸው ጋር (በጥቁር ሰሌዳ፣ በቃላት ካርድ ላይ) ያገናኛሉ፡፡

**አርአያ መሆን፡** ሀ. መምህር ከተማሪዎች በተሸለ ሁኔታ ድምጹን ከፍ አድርጎ በትክክል ለተማሪዎች ያነባል፡፡

**ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ፡** ተማሪዎች ቃላዊ ንባብን እንዲከውኑ እድል ይሰጣል፡፡

**አርአያ በመሆን ማንበብን ለተማሪዎች ቀስበቀስ መተው፡** ጣትን በመጠቆም በገደል ማሚቶ፣ በጋራ በማንበብ፣ በጥንድ ድምጽን ከፍ አድርጎ ማንበብ፣ ድምጸችንና ፊደላትን በመንካት ማገናኘት፤

**የተመረጡ ፊደላትን ማሳየት**

**በአየር ላይ መጻፍ፡** ተማሪዎች ፊደላትን በአየር ላይ ወይም በወረቀት ላይ በአመልካች ጣታቸው ይጽፋሉ፡፡ መምህር የፊደላትን ወይም የድምጸችን ስም ይናገራል፡፡ ተማሪዎች ደግሞ በአየር ላይ ወይም በወረቀት ላይ በጣታቸው ይጽፋሉ፡፡

ተማሪዎች ቤተሰባዊ ዝምድና ያላቸውን ቃላት ይጠራሉ፤ የቃላትን ቤተሰብ በዛፍ ስዕል መልክ ጽፈው ያሳያሉ፡፡

**ቅድመ መጻፍ ተግባራት፡** ከመጻፍ በፊት የሚከሰቱ ተግባራትን ማስቀመጥ

**መምህር፡** ድምጸችን ወይም ፊደላትን ለልምምድ በርካታ ቃላትን ቃላዊ በሆነ መንገድ ያቀርባል፡፡

**ተማሪዎች፡** መምህር ያቀረበውን በርካታ መንገድ ተጠቅመው ፊደላትን ወይም ድምጸችን ይለያሉ፡፡

## 4.ምዘና

- በህትመት ግንዛቤ ላይ የቃል ጥያቄዎችን መጠየቅና ምላሽ መስጠት፡፡
- ድምጽን/ ፊደላትን የመለየት ጥያቄ፤
- የቃላት የማውጫ ካርዶች መጠቀም፤
- አካላዊ ምላሽ፣ ተማሪዎች በግል የሚሰጡት አካላዊ ምላሽ፣
- ኢ-መደበኛ ቁጥጥር፣
- ምልከታ፣ በሚታይ ነገር መወከል፣ ሚና መለዋወጥ፣
- ጽብረቃ፣

**ክፍለጊዜ፡አንድ**

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

## ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄ

መምህር ከትምህርቱ ጋር የሚገናኝ አጫጭር ጭውውቶች፣ ቀልዶች ፣ መዝሙሮች ፣ እንቆቅልሾች የመሳሰሉትን በማቅረብ ተማሪዎችን ያነቃቋቸው፡፡ በመቀጠል ከዚህ በታች የቀረቡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ተማሪዎችን በቃል በመጠየቅ የቀደመ እውቀታቸውን ይቀስቅሱ፡፡ በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ያሉትን ስዕሎች አይተው በቀጣይ የሚማሩትን እንዲገምቱ ያድርጉ፡፡

1. መፅሐፍ ቤታችሁ አለ?
2. መጽሀፋችሁን አሳዩኝ!
3. ደብተራችሁን አውጡ!
4. እርሳሳችሁን አሳዩኝ፡፡

## የማዳመጥ ጊዜ

መምህር መፅሐፍ በእጅዎ ከፍ አድርገው ይዘው በማሳየት በእርጋታ የፊት ሽፋን (ለምሳሌ ርዕስን) ፣ የኋላ ሽፋን፣ ገፅ (የተወሰኑ)፣ ስዕሎችን… ያሳዩአቸው፡፡ መጽሀፍ ከግራ ወደ ቀኝ ፣ ከላይ ወደታች እንደሚነበብ ያመልክቷቸው፡፡ በእያንዳንዱ የመፅሐፍ ክፍል ላይም በቂ ገለፃ ይስጧቸው፡፡

በመቀጠል ተማሪዎቹ የየራሳቸውን መፅሐፍ እንዲይዙና እርስዎ በገለፃ ያቀረቡላቸውን የመፅሐፍ ክፍሎች ተራ በተራ እያሳዩ እንዲናገሩ ያድርጓቸው፤ ማበረታቻም ይስጧቸው::

## ድህረ ማዳመጥ

የተማሪ መፅሐፍ ላይ ያሉ ስዕሎችን እየጠቆሙ ስህተት ያለባቸውንና ትክክለኞቹን እንዲለዩ ይጠይቋቸው፤ ለምላሻቸውም ምክንያት እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡

**(ለዚህም እባክዎ በሁሉም ተግባራት ላይ ሳይሰለቹ ሰፋ ያለ ጊዜ ይስጧቸው)**

### ክፍለጊዜ፡ ሁለት

መምህር በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ቤተሰብ ስለ መጽሀፍ አጠቃቀም ለልጆች ሲያስረዱ ስለሚያሳየው ምስል አጭር ገለጻ ይስጧቸው፡፡ በመቀጠልም የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡

1. ምስሉላይ ስንት ሰዎች አሉ?
2. ልጁን ስለ መጽሀፍና እርሳስ አያያዝ እያሳየው ያለው ማን ነው?
3. በምስሉ ላይ ልጁ መጽሀፉን በትክክል ይዟል?
4. በምስሉ ላይ ልጁ እርሳሱን እንዴት ይዟል?

### ክፍለጊዜ፡ ሦስት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

መምህር ያለፈውን ክፍለ ጊዜ ባጭሩ ከገለፁ በኋላ፣ በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የቀረበውን ምስል ተንተርሰው ሁለት ተማሪዎችን (ሴትና ወንድ) በማስነሳት በሞዴልነት የመፅሐፍ ክፍሎችን እየለዩ እንዲናገሩ ይጋብዟቸው፤ ተማሪዎቹ ተራ በተራ እጅ እያወጡ እንዲናገሩ አድርጓቸው፡፡ ስህተት እንኳን ቢናገሩ ዋናው የንግግር ክሂል ማዳበራቸው ስለሆነ ያድንቋቸው፡፡ እርስዎም እገዛ ያድርጉላቸው፡፡ ከሞዴሉ በኋላ ሌሎች ተማሪዎችን በመጋበዝ ወይም እንደአቀማመጣቸው በጥንድ ጥንድ እየሆኑ ስለመፅሐፍ ክፍሎች ተመሳሳይ ገለፃ እንዲሰጡ ያትጓቸው፡፡

እባክዎ መምህር ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ሲያጋጥሙዎት ተገቢውን እገዛ ያድርጉላቸው፤ ተጨማሪ መለማመጃ ጊዜም ይስጧቸው፡፡

### ክፍለጊዜ ፡ አራት

መምህር በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ስለቤተሰብ አባላትን የሚያሳየውን ምስል መሰረት አድርገው የቤተሰብ አባላትን እንዲለዩ ያድርጉ፡፡ይህን ሲተገብሩ አስቀድመው በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያለውን ምስል ከፍ አድርገው እናት፣አባት፣እህት ወንድም …በጣቶ እየጠቆሙ ያመልክቷቸው፡፡በመቀጠልም ተማሪዎች ተራ በተራ እየወጡ እያንዳንዱን የቤተሰብ አባላት እየጠሩና በጣት እየጠቆሙ እንዲያመለክቱ ሳይታክቱ ያግዟቸው፡፡ ሙከራቸውንም ያድንቁላቸው፡፡ ለእያንዳንዱ ተማሪ ሙከራ ሌሎች ተማሪዎች እንዲያጨበጭቡላቸው ያድርጉ፡፡

### ከክፍለጊዜ አምስት እስከ አስር

## ትምህርት ሶስት፡ማንበብ

መምህር ከክፍለጊዜ አምሰት እስከ አስር የቀረቡ ተተኳሪ ፊደሎችን (ሀ፣ለ፣መ ከነዘሮቻቸው) ከፍ ባለ ድምጽ ደጋግመው በሞዴልነት ይጥሩ፡፡ ቀጥለው እርስዎና ተማሪዎችዎ ድምጸቹን አንድ ላይ በትክክል እየጠራችሁ ያለማምዷቸው፡፡ ከዚያም ተማሪዎቹ ራሳቸውን ችለው ስዕሎችን በማየት የቃሉን መነሻ ፊደልና ቃሉን እንዲጠሩ ያድርጉ፡፡ እባክዎ መምህር ተማሪዎቹ ይህንኑ ለተወሰነ ጊዜ እየደጋገሙ እንዲለማመዱ ያትጓቸው፡፡ ተተኳሪ ድምፆች በቃል መነሻ፣ በቃል መሀከልና በቃል መድረሻ ላይ ሊመጡ እንደሚችሉ ግንዛቤ በመፍጠር ድምፆቹ ያሉባቸውን ቃላት በቃል እያቀረቡ እንዲለማመዱ ይሁን፡፡ ለምሳሌ “ሀ” በቃል መነሻ “ሀይል” በቃል መሃል “መሀል” በቃል መጨረሻ “ ውሀ” እንደሚገኙ በሁለም ተተኳሪ ድምጾች በቂ ምሳሌ በመስጠት ያለማምዱ፡፡ ተማሪዎች የሚያውቋቸው በተተኳሪ ድምጾች የተመሰረቱ ቃላት እንዲጠሩልዎት ያድርጉና የተወሰኑትን ይምረጡላቸው፡፡ ከዚያም የተመረጡትን ቃላት በጋራና በተናጠል ያለማምዷቸው፡፡መምህር ድምፆቹን በትክክል ያልጠሩና ድጋፍ የሚያስፈላጋቸው ተማሪዎች ካሉ እባክዎ ይርዷቸው!

ይህንን ሲተገብሩ የተማሪዎቹዎን ትኩረት ከፍ ለማድረግ የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ እያንዳንዱን ድምጽ ሲጠሩ እንዲያጨበጭቡ ወይም ጠረጴዛ እንዲመቱ፣ ከተቻለም ለፊደሎቹ ዜማ በመፍጠር እንዲዘምሩ ማድረግ ይችላሉ፡፡ መጽሀፍ ውስጥ ከቀረቡት ቃላት በተጨማሪ ተማሪዎች እንዲያፈልቁ ማበረታታት ይችላሉ፡፡

### ከክፍለጊዜ አስራአንድ እስከ አስራስድስት

መምህር ከክፍለጊዜ 11-16 ድረስ የቀረቡ ተተኳሪ ፊደላትን (ሀ፣ ለ፣ መ እና ዘሮቻቸው) ድምጽና ቅርጽ አዋህዶ ለማስለየት በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡትን የፊደላት ቅርጽና ምስል ድምጽንም በመጨመር እንዲያዛምዱ ይርዷቸው፡፡ ይህንን ሲተገብሩ በቅድሚያ እርሶ ይስሩ፤ በመቀጠልም ከተማሪዎችዎ ጋር አብረው ይስሩ፤ በመጨረሻም ተማሪዎችዎ እራሳቸውን ችለው በተናጠል እንዲሰሩ ይርዷቸው፡፡ ተማሪዎች የሚያውቋቸው በተተኳሪ ድምጾች የተመሰረቱ ቃላት እንዲጠሩልዎት ያድርጉና የተወሰኑትን ይምረጡላቸው፡፡ ከዚያም የተመረጡትን ቃላት በጋራና በተናጠል

ያለማምዷቸው፡፡ ተማሪዎች ተተኳሪ ፊደሎች ያሉበትን ቃላት ሲጠሩ በማጨብጨብ ተተኳሪ ፊደሉን እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡ በተጨማሪም በየክፍለጊዜው የሚማሩትን ፊደላት ቅርጽ በባለቀለም ወረቀት ግድግዳ ላይ መለጠፍ ፣ ፊደላትን ጎላ አድርጎ በሰንጠረዥ ማቅረብ፣ በካርቶን ላይ ፍላሽ ካርዶችን አዘጋጅቶ መጠቀም ፣ፍላሽ ካርዶችን ጠረጴዛ ላይ በታትኖ በማሰቀመጥ እንዲመርጡ ማድረግ፣ በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ከቀረቡት ቃላት በተጨማሪ ተማሪዎች ሌሎችን እንዲያፈልቁ ማበረታታት፣ አንድ ተማሪ ከሳጥን ውስጥ ተራ በተራ ፍላሽ ካርድን እንደ እጣ በማውጣት፣ ያወጣውን ከፍ አድርጎ በማሳየት ሌሎች ተማሪዎች እንዲጠሩ በማድረግ ትምህርቱን ማቅረብ፡፡

መምህር ትምህርቱን ተጨባጭ ለማድረግ ፊደላቱን ለየብቻ በፍላሽ ካርድ አዘጋጅተው በቀኝና በግራ እጅ ወደ ላይ ከፍ አድርገው በመያዝ እየነጠሉና እያገጣጠሙ ያመልክቷቸው፡፡ ተማሪዎችም ይህንኑ ተግባር ተራ በተራ እየገጠሙና እየነጠሉ እንዲያመለክቱ ይርዷቸው፡፡ ፊደላቱን በአካባቢ በሚገኙ ቁሳቁሶች ሰርተው እንዲመጡ የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡

መምህር የተተኳሪ ድምፆቹን ምልክት በትክክል ለመለየት ለተቸገሩ ተማሪዎች የተለመደውን ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

# ትምህርት አራት፡ ቃላት

መምህር በዚህ ትምህርት ክፍል ስር ተማሪዎች በዕለት ተዕለት ህይወታቸው የሚጠቀሟቸውን ቃላት ያስተምራሉ፡፡ ይህንን ሲተገብሩ በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ለናሙና የቀረቡ ምስሎችን በመጠቀም ተዘውታሪ ቃላትን ተማሪዎች ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እንዲጠሯቸው በቅድሚያ እርሶ ቃላቱን ይጥሩላቸው፤ በመቀጠል ከተማሪዎች ጋር በህብረት ይጥሯቸው፤ በመጨረሻም ተማሪዎች በተናጠል እራሳቸውን ችለው እንዲጠሯቸው ይርዷቸው፡፡ ተማሪዎችዎን በተለያየ ዘዴ ማበረታታትዎን አይዘንጉ፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች ሌሎች ተዘውታሪ ቃላትን እንዲያፈልቁ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ያግዟቸው፡፡ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች (ምስል፣ ፍላሽ ካርድ…) መጠቀም እንዳለብዎ አይዘንጉ፡፡

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

## ትምህርት አምስት፡ በአየር ላይ መፃፍ

መምህር ይህ ትምህርት ክፍል ተማሪዎችዎ ለመጀመሪያ ጊዜ የጽህፈት ሂደት እንዲያግዛቸው እጃቸውን እንዲያፍታቱ የሚማሩበት ነው፡፡ በዚህም ተማሪዎች እርሳስና ወረቀት ከማገናኘታቸው በፊት በእጃቸው በአየር ላይ እንዲጽፉ ይርዷቸው፡፡ ይህን ሲተገብሩ በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረበውን ምስል መሰረት አድርገው ተማሪዎችን የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ስዕሉን እንዲገነዘቡና በስዕሉ መሰረት እንዲጽፉ አሰቀድመው እርሶ ሞዴል ሆነው ያመልክቷቸው፡፡ በመቀጠልም ተተኳሪ ፊደላትን በተናጥል በአየር ላይ እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡ ተማሪዎችዎን ማበረታታት አይዘንጉ፡፡ በተጨማሪም ግርግዳላይ፣ ወንብርላይ፣ ሰሌዳ ላይ በጣታቸው እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ቤት

(18ክፍለ ጊዜ)

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ምንባቡን አዳምጠው መልዕክቱን ይረዳሉ፡፡
- በቤታቸው ያሉ የተለያዩ ቁሳቁሶችን ጠርተው ቅርጻቸውን ያሳያሉ(ይረስሳሉ)፡፡
- መሰረታዊ ቅርጾችን ይረስሳሉ፡፡
- አዳዲስ ድምጾችን/ፊደላትን ( ሠ፣ ረ፣ ሸ፣ ቀ፣ በ) ያነባሉ፡፡
- ድምጾችን ከመልክቶቻቸው ጋር ያዛምዳሉ፡፡
- ባለሁለት ቀለም ቃላትን ይጽፋሉ፡፡

## 2. ዝርዝር ይዘቶች

- ለምዕራፍ ሁለት አምስት ድምጾችን መምረጥ(ሠ፣ረ፣ሸ፣ቀ፣በ)
- የተመረጡ የፊደል ድምጾች ግንኙነት፡ ተመሳሳይ ቀለሞች ያሏቸውን ቃላት ሲጠሩ ያጨበጭባሉ፡፡
- ተዘውታሪ ቃላት(የትምህርት ቃላት) የቃላት እድገት
- ድምጾችን ማንበብና መጻፍ
- ድምጾችን ከሚወክሏቸው ፊደላት ጋር በማገናኘት በትክክል ማንበብ
- መሰረታዊ ምልክቶችና ቅርጾች መጻፍ

## 3. የማስተማሪያ ብልሀቶችና መሳሪያዎች

መምህር ስለመሰረታዊ ቅርጾች ምልክት ጥያቄ መጠየቅ

**መገመት፡** ተማሪዎችን ርዕሱን፣ ስዕሎችን፣ ቁልፍ ቃላትን ተመልክተው ስለምን እንደሚያዳምጡ መጠየቅ፣ መምህር መሰረታዊ ቅርጾችን በሰሌዳ ላይ መጻፍ፡፡ ከዚያም በአየር ላይ ቅርጾችን በመጻፍ ማሳየት፡፡ (ስዕሎችን የድምጾችን/ ፊደላትን ቅርጽ፣ የቃላት ካርድ፣ ባለቀለም ወረቀት፣ ካርቱን ምስሎች፣ ሰሌዳ ወዘተ መጠቀም)

ከዚያም ቅርጾችን በአየር ላይ ጣቶቹን በአየር ላይ ማመልከት፡፡ (እራስን የማስቻል ሞዴል መከተል)

*መምህሩ፡ ተማሪዎች ሶስት በተመሳሳይ ድምጽ የሚጀምሩ ወይም የሚጨርሱ ቃላትን እንዲያቀርቡ መጠየቅ፡፡ (የድምጾችን ወይም ፊደላትን ቅርጾች ወይም የቃላት ካርድ፣ ባለቀለም ወረቀት፣ ካርቶን ስዕሎች፣ ሰሌዳ ወዘተ)*
*ተማሪዎች በተመሳሳይ ድምጽ የሚጀምሩ ወይም የሚጨርሱ ሶስት ቃላትን መለየት*

**መቁጠር፡** *ተማሪዎች በቃላት ውስጥ ባሉ የድምጾች መጠን ያህል ያጨበጭባሉ፡፡*

**መምህር፡** *መምህር ተማሪዎች በተመሳሳይ ድምጽ የሚጨርሱትን ቃላት እንዲናገሩና ዜማ እንዲኖረው ማድረግ፡፡*

**ተማሪዎች፡** በተመሳሳይ ድምጽ የሚጨርሱትን ቃላት ቤተሰብ ማመንጨትና መምህር ደግሞ የተማሪዎችን ምላሽ በሰሌዳ ላይ መጻፍ (በግድግዳ ላይ የተጻፉ ቃላት)

**ቀስበቀስ ማብቃት፡** ሀ. *መምህር ፊደላትን አድምቆ በማሳየት ድምጸታቸውን ይጠራል፡፡*
ለ. *መምህር ተማሪዎቹ የደመቁትን ፊደላት በማሳየት የፊደላቱን ድምጸት እንዲለዩ ይጠይቃል፡፡*
ሐ. *ተማሪዎች የደመቁትን ፊደላትና የሚወክሏቸውን ድምጾች ማዛመድ ይለማመዳሉ፡፡*

**የመምህር እርእያነት፡** ድምጾችን ከእንቅስቃሴዎች ጋር ማዋሀድ፡፡ ይህ ተማሪዎች አካላዊ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ድምጾችንና ፊደላትን እንዲያስታውሱ ይረዳል፡፡

**የአፍ እንቅስቃሴ፡** ተማሪዎች በአንደበት አካላቸው ውስጥ ድምጾች እንዴት እንደሚፈጠሩ ይማራሉ፡፡

**ቃላትን መመስረት፡** ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን ከአዳዲስ የቃል ክፍሎች ጋር ማንበብ ይለማመዳሉ፡፡

**ተዘውታሪ ቃላት፡** *መምህር በምንባቡ ውስጥ ተዘውታሪ ቃላትን በማሳየት ተማሪዎቹ የቃላቱን ትርጉም በቡድን ሆነው ይሰጣሉ፡፡*

**ማንበብ፡** ሀ. መምህር ቃላትን በማሳየት፣ በቃላት ውስጥ ያሉትን ድምጾች ይጠራል፡፡ ከዚያም ድምጾችን ይነጥላል፡፡ (በጉልህ የታወቁ ድምጾችን መጠቀም) ተማሪዎች ሁሉንም ድምጾች በመነጠልና በማጣመር ይለያሉ፡፡

**አርአያ፡** መምህር ከተማሪዎች በተሻለ ደረጃ ምንባብን ጮክ ብሎ ያነባል፡፡

**ተደጋጋሚ የቃል ንባብ፡** ተማሪዎች ለተደጋጋሚ የቃል ንባብ በመጋለጥ በትክክል የማንበብ ችሎታቸውን ያሳድጋሉ፡፡

**ቀስበቀስ ማብቃት፡** በጣታቸው በማመልከት የገደል ማሚቶ የጋራ ንባብ፣ ግላዊ ንባብ እና በመጋራት ማንበብ

**መምህር፡** ቃላትን በመጠቀም ድምጾችን /ፊደላትን ለመለማመድ በርካታ እድሎችን መፍጠር

**ተማሪዎች፡** በርካታ ድምጾችን /ፊደሎችን ለመለየት በርካታ ዕድሎችን መጠቀም፡፡

ፊደላትን/ድምጾችን መቅረጽ

የተመረጡ ድምጾችን መቅረጽ

**በአየር ላይ መጻፍ :** መምህር የፊደላቱን ስም መጥራት፡፡ ተማሪዎች በጣታቸው በአየር ላይ ወይም በመጻፊያ ነገር ላይ ፊደላትን መቅረጽ፡፡ ከዚያም ተማሪዎች በአመልካች ጣታቸው በአየር ላይ ወይም በመጻፊያ ነገር ላይ ፊደላቱን መጻፍ፡፡

## 4. ምዘና

- የማዳመጥ ምንባቡን ዋና ይዘት በቃል /በጽሁፍ ጥያቄዎችን በመጠየቅ፣ ግብረ መልስ መስጠት፡፡
- መሰረታዊ ቅርጾችን እንዲጽፉ መጠየቅ፡፡
- አካላዊ ምላሽ
- ተማሪዎች በግላቸው ለጥያቄዎች የሚሰጡት ምላሽ
- መሰረታዊ ቅርጾችን ሲጽፉ ኢመደበኛ ቁጥጥር ማድረግ፡፡
- ምልከታ፣
- በሚታይ ነገር መወከል፣
- ተራ በተራ ማቅረብ
- ስልታዊ ልምምድ

**ክፍለጊዜ፡አንድ**

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

## ቅድመ ማዳመጥ

መምህር ከትምህርቱ ርዕስ ጋር የሚገናኝ አጫጭር ጭውውቶች፣ ቀልዶች ፣ መዝሙሮች ፣ እንቆቅልሾች የመሳሰሉትን በማቅረብ ተማሪዎችን ያነቃቋቸው:: ተማሪዎች በመጽሀፉ ላይ ያሉትን ስዕሎች አይተው ስለምን እንደሚማሩ እንዲገምቱ መጠየቅ፣ ግምታቸውን ማጠናከር ወይም መለወጥ እንደሚችሉ ይንገሯቸው:: በመቀጠል ከዚህ በታች የቀረቡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ተማሪዎችን በቃል በመጠየቅ የቀደመ እውቀታቸውን ይቀስቅሱ::

1. የምታደምጡት ስለምን ይመስላችኋል?
2. የማብሰያ ቤታችሁ ምን ምን እቃዎች ይዟል? ዘርዝሩ ::

| |
|---|
| መምህር የሚደመጠውን ታሪክ በዝግታ ሁለቴ ደጋግመው ያንብቡላቸው:: በጽሁፉ ውስጥ ከቀረቡት ቃላት ውስጥ አዳዲስ ወይም ከባድ ቃላትና ሀረጋት ናቸው የሚሏቸውን በቅድሚያ ፍቺ ይስጧቸው:: በምንባቡም መሃል ንባቦትን ገታ አድርገው የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎችን ያቅርቡላቸው:: |

### “ማብስያ ቤት”

የነኬና ቤት ሰፊና ትልቅ ነው:: የተለያዩ ክፍሎችም አሉት:: ኬናም የሚወደው አሻንጉሊት አቅፏል መኝታ ቤት ጋደም ብሏል:: ድንገት ከማብሰያ ቤት ሆና እናቱ ስትጠራው ሰማ :: አሻንጉሊቱን ይዞም ጥሪ ወደ ሰማበት ቁልቁል በደረጃ ወረደ:: ከዚያ በቀጥታ ወደ ምግብ ማብሰያ ክፍል ገባ::

**(የማዳመጥ ጊዜ)** ኬና ምግብ ማብሰያ ቤት ውስጥ ምን ያጋጥመው ይሆን?

ምግብ ማብሰያ ቤቱ በምግብ ማብሰያ ቁሳቁሶች ተሞልቷል:: እቃዎችም ሳህን፣ ድስት፣ ማንቆርቆሪያ ወዘተ ናቸው:: በምግብ ጠረጴዛው ላይ ምግቦች ተቀምጠዋል:: ኬና የሚወደውን ምግብ ወተትና ብስኩት አየ:: እናቱን እያመሰገነ መመገብ ጀመረ::

**ድህረ ማዳመጥ**

*መምህር ተማሪዎች ማዳመጣቸውን የሚፈትሹ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡ ጥያቄዎችን በተናጥልና በተራ በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡*

1. ኬና ለምን እናቱን አመሰገነ?
2. በማብሰያ ቤት ውስጥ ያሉትን እቃዎች ዘርዝሩ፡፡

**ክፍለጊዜ፡ ሁለት**

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

*መምህር በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የቀረበውን ምስል ተንተርሰው ተማሪዎች ባህላዊና ዘመናዊ ቤቶችን እያነጻጸሩና በቤት ወስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች፡ አልጋ፣ ሳጥን፣ መደርደሪያ፣ ጠረጴዛ ፣ ድስት፣ ብርጭቆ ፣ ሳህን እያሉ እንዲዘረዝሩ ያበረታቷቸው፡፡ ተማሪዎቹ ተራ በተራ እጅ እያወጡ እንዲናገሩ አድርጓቸው፡፡ ስህተት እንኳን ቢናገሩ ዋናው ጉዳይ የንግግር ክሂል ማዳበራቸው ስለሆነ ያድንቋቸው፡፡ በብልህትም ስህተታቸውን አርመው ይለፉ፡፡ እርስዎም እገዛ ያድርጉላቸው፡፡ ለያንዳንዱ ተማሪ ሙከራ ሌሎች ተማሪዎች እንዲያጨበጭቡላቸው ያድርጉ፡፡*

*እባክዎ መምህር ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ሲያጋጥሙዎት ተገቢውን እገዛ ያድርጉላቸው፤ ተጨማሪ መለማመጃ ጊዜም ይስጧቸው፡፡*

**ክፍለጊዜ፡ ሶስት እስከ አስራ ስድስት**

# ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

*መምህር ከክፍለጊዜ 3-16 ድረስ የቀረቡ ተተኳሪ ፊደላትን (ሠ፣ ረ፣ ሸ፤ ቀ፣ በ እና ዘሮቻቸው) ድምጽና ቅርጽ አዋህዶ ለማስለየት በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡትን የፊደላት ቅርጽና ምስል ድምጽንም በመጨመር እንዲያዛምዱ ይርዷቸው፡፡ ይህንን ሲተገብሩ በቅድሚያ እርሶ ይስሩ፤ በመቀጠልም ከተማሪዎችዎ ጋር አብረው ይስሩ፤ በመጨረሻም ተማሪዎችዎ እራሳቸውን ችለው በተናጥል እንዲሰሩ ይርዷቸው፡፡ ተማሪዎች የሚያውቋቸው በተተኳሪ ድምጾች የተመሰረቱ ቃላት እንዲጠሩልዎት ያድርጉና የተወሰኑትን ይምረጡላቸው፡፡ ከዚያም የተመረጡትን ቃላት በጋራና በተናጠል ያለማምዷቸው፡፡ ተማሪዎች ተተኳሪ ፊደሎች ያሉበትን ቃላት ሲጠሩ በማጨብጨብ ተተኳሪ ፊደሉን እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡ እባክዎ መምህር ተማሪዎቹ ይህንኑ ለተወሰነ ጊዜ እየደጋገሙ እንዲለማመዱ ያትጓቸው፡፡*

ተተኳሪ ድምፆች በቃል መነሻ፣ በቃል መሀከልና በቃል መድረሻ ላይ ሊመጡ እንደሚችሉ ግንዛቤ ለመፍጠር ድምፆቹ ያሉባቸውን ቃላት በቃል እያቀረቡ እንዲለማመዱ ይሁን፡፡ ለምሳሌ "ሠ" በቃል መነሻ "ሠበረ" በቃል መሃል "መሠለ" በቃል መጨረሻ "ገመሠ" እንደሚገኙ በሁለም ተተኳሪ ድምጾች በቂ ምሳሌ በመስጠት ያለማምዱ፡፡ በተጨማሪም በየክፍለጊዜው የሚማሩትን ፊደላት ቅርጽ በባለቀለም ወረቀት ግድግዳ ላይ መለጠፍ ፣ ፊደላትን ጎላ አድርጎ በሰንጠረዥ ማቅረብ፣ በካርቶን ላይ ፍላሽ ካርዶችን አዘጋጅቶ መጠቀም፣ ፍላሽ ካርዶችን ጠረጴዛ ላይ በታትኖ በማስቀመጥ እንዲመርጡ ማድረግ፣ በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ከቀረቡት ቃላት በተጨማሪ ተማሪዎች ሌሎችን እንዲያፈልቁ ማበረታታት፣ አንድ ተማሪ ከሳጥን ውስጥ ተራ በተራ ፍላሽ ካርዱን እንደ እጣ በማውጣት፣ ያወጣውን ከፍ አድርጎ በማሳየት ሌሎች ተማሪዎች እንዲጠሩ በማድረግ ትምህርቱን ማቅረብ ይቻላል፡፡

ከመልመጃ አንድ እስከ ስድስት የቀረቡትን መልመጃዎች የመማሪያ መጽሀፉን አይተው ተማሪዎቹ በደብተራቸው ላይ እንዲሰሩ ይንገሯቸው፡፡ ሙከራቸውንም እያደነቁ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡

መምህር ትምህርቱን ተጨባጭ ለማድረግ ፊደላቱን ለየብቻ በፍላሽ ካርድ አዘጋጅተው በቀኝና በግራ እጅ ወደ ላይ ከፍ አድርገው በመያዝ እየነጠሉና እያገጣጠሙ ያመልክቷቸው፡፡ ተማሪዎችም ይህንኑ ተግባር ተራ በተራ እየገጠሙና እየነጠሉ እንዲያመለክቱ ይርዷቸው፡፡ ፊደላቱን በአካባቢ በሚገኙ ቁሳቁሶች ሰርተው እንዲመጡ የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡

መምህር የተተኳሪ ድምፆቹን ምልክት በትክክል ለመለየት ለተቸገሩ ተማሪዎች የተለመደውን ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

# ትምህርት አራት፡ ቃላት

መምህር በዚህ ትምህርት ክፍል ስር ተማሪዎችዎን የትምህርት ቃላትን ያስተምራሉ፡፡ እነዚህ ቃላት በመማር ማስተማር ሂደት በብዛት የምንገለገልባቸው ናቸው ተብለው የተመረጡ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ክፍሉን ለመቆጣጠር፣ የመማር ማስተማሩን የሚረዱ ተጨማሪ ቃላትን አክለው ማስተማር ይችላሉ፡፡ ትምርቱን ሲተገብሩ በመማሪያ

መጽሀፍ ውስጥ ለናሙና የቀረቡ ምስሎችን በመጠቀም ትምህርታዊ ቃላትን ተማሪዎች ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እንዲጠሯቸው በቅድሚያ እርሶ ቃላቱን ይጥሩላቸው፤ በመቀጠል ከተማሪዎችዎ ጋር በህብረት ይጥሯቸው፤ በመጨረሻም ተማሪዎች በተናጥል እራሳቸውን ችለው እንዲጠሯቸው ይርዷቸው፡፡ ተማሪዎችዎን በተለያየ ዘዴ ማበረታታትዎን አይዘንጉ፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች ሌሎች የትምህርት ቃላትን እንዲያፈልቁ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ያግዟቸው፡፡ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች (ምስል፣ ፍላሽ ካርድ…) መጠቀም እንዳለብዎ አይዘንጉ፡፡

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

# ትምህርት አምስት፡ ጽሕፈት

መምህር በዚህ ክፍል ውስጥ ለመጻፍ መሰረት የሚሆኑትን መሰረታዊ መስመሮች የሚቀርቡበት ነው፡፡ ተማሪዎችዎ ቀጥታ መስመር፣ አግድም መስመር፣ ክብ፣ ግራ የክብ ግማሽ፣ ቀኝ የክብ ግማሽ እና የመሳሰሉትን ለመጻፍ የሚረዱትን መስመሮች ደጋግመው ተማሪዎች እንዲረስሱ ያትጓቸው፡፡ የመስመር አጠባበቃቸውን፣ የእርሳስ አያያዛቸውን ተዘዋውርው እየተመለከቱ የተማሪዎችን ሙከራ ያድንቁላቸው፡፡ እገዛ ለሚሹ ተማሪዎች እገዛዎት አይለያቸው፡፡ የእርሳሳ አያያዛቸው ፊደልን ለመቅረጽ ወሳኝ መሆናቸውን ትኩረት በመስጠት፣ ተማሪዎችዎ ተግባሩን እየደጋገሙ እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡ የተማሪዎቹንም ጥረትና ለውጥ ያድንቁላቸው፡፡ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡትን መሰረታዊ መስመሮች ደብተራቸው ላይ እየጻፉ እንዲለማመዱ ያድርጓቸው፡፡ መስመሮችን በባለ ቀለም ወረቀት፣ በቻርት እና በፍላሽ ካርድ በማሳየት ትምህርቱን ተጨባጭ ያድርጉት ፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# ትምህርት ቤት

(18ክፍለ ጊዜ)

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ምንባቡን በማዳመጥ ተዘውታሪ ቃላትን ይጠራሉ፡፡
- አዳዲስ ድምጾችን/ፊደላትን( ተ፣ ቸ፣ ነ፣ ኘ፣ አ) ያነባሉ፡፡
- አዲስ የድምጽ- ፊደል ተዛምዶን ይፈጥራሉ፡፡
- ተዘውታሪ ባለሶስት ቀለም ቃላትን ይጽፋሉ፡፡

## 2. ዝርዝር ይዘቶች

- ✓ ምንባቡን አድምጦ ሀሳቡን መረዳት
- ✓ የተመረጡ አምስት ድምጾች/ ከምእራፍ ሁለት በኋላ ተከትለው የሚመጡ ፊደላት (ተ፣ ቸ ፣ ነ፣ ኘ፣ አ)
- ✓ የተመረጡ የፊደል ድምጽ ግኑኝነት
- ✓ ተዘውታሪ (የትምህርት) ቃላት
- ✓ የቃላት እድገት
- ✓ የጽንሰ ሀሳብ ስያሜ፡ ድምጾችን ማንበብና መጻፍ
- ✓ ድምጾችን ከፊደላት ጋር አዛምዶ ፣ በፍጥነትና በጥሩ አገላለጽ ማንበብ
- ✓ በተደጋጋሚ የሚመጡ ፊደላትን መቅረጽ

## 3. የማስተማሪያ ብልሀቶችና መሳሪያዎች

በድምጽ የሚጀምሩና የሚጨርሱ መሆናቸውን በማረጋገጥ የድምጾቹን አጠራር መለየት፡፡

**መቁጠር፡** መምህር ርዕሶችን፣ ስዕሎችንና ቁልፍ ቃላትን በመጠቀም ምንባቡ ስለምን እንደሚያወሳ እንዲገምቱ የተማሪዎችን የቀደመ ዕውቀት ለመቀስቀስ መጠየቅ፡፡ እንዲሁም ከትምህርት ቤት ቁሳቁሶች ጋር የተገናኙ ቃላትን ትርጉም መለየት፡፡ መምህር ተማሪዎች በተመሳሳይ ድምጽ የሚጀምሩና የሚጨርሱ ቃላትን እንዲዘረዝሩ ማድረግ፡፡

ተማሪዎች በቃላት ባሉ ድምጾችና ቀለማት ልክ ያጨበጭባሉ (ስዕሎችን፣ የፊደል ካርዶችን፣ ቀለማዊ ወረቀቶችን፣ የካርቱን ምስሎችንና ጥቁር ሰሌዳን ወዘተ መጠቀም፡፡

**ተመሳሳይ ዜማ** መምህር ለተማሪዎች በተመሳሳይ ቀለም የሚጨርሱ ቃላትን ማቅረብ:: ከዚያም መዝሙሮችን በቃላት መፍጠር፡፡

ተማሪዎች ተመሳሳይ የመጨረሻ ቀለሞች ያሏቸውን ቃላት ቤተሰብ መፍጠር፡፡ ከዚያም መምህር ሰሌዳው ላይ ግብረመልስ መስጠት፡፡

**መነጠልና ማጣመር** መምህር በቃላት ውስጥ ያሉትን ድምጾች ምሳሌ በመሆን:: መምህር በቃላት ውስጥ ያሉትን ድምፆች በነጠለው መንገድ ተማሪዎችም በቃላት መካከል ያሉትን ድምጾች በፍጥነት ይነጥላሉ፡፡ ተማሪዎች ቃሉን መጥራት፡፡ እንዲሁም እያንዳንዱን ድምጽ መጥራት፡፡

**ቀስበቀስ ማብቃት፡**

ሀ. መምህር ፊደላትን አድምቆ በማሳየት ድምጸታቸውን መጥራት፡፡

ለ. መምህር ምልክቱን ለተማሪዎች ሲያሳይ ተማሪዎች ድምጸቱንና ስሙን መናገር፡፡

ሐ. ተማሪዎች ድምጸቱንና ምልክቱን የማዛመድ ተግባር መለማመድ፡፡

**እንቅስቃሴ፡** ድምጽን ከእንቅስቃሴ ጋር ማገናኘት፡፡ ይህም ተማሪዎች አካላቸውን እንዲያንቀሳቅሱ ይረዳቸዋል፡፡ ይህ ደግሞ ፊደሉንና ድምጹን እንዲያስታውሱ መርዳት፡፡

**የድምጾች /የፊደላት ምልክት**

**የአፍ እንቅስቃሴዎች፡** ተማሪዎች እንዴት ድምጽ በአፍ ውስጥ እንደሚፈጠር መማር፡፡

**የድምጾች /ፊደላት ምልክት**

**በአየር ላይ መጻፍ፡** መምህር የፊደላትን ድምጽ በሚጠራበት ወቅት ተማሪዎች ፊደላቱን በጣታቸው በአየር ላይ ወይም በመጻፊያ ላይ መጻፍ፡፡

**ምልክቶችን መተርጎም፡** ሀ. መምህር ቃላትን በማሳየት፣ እያንዳንዱን ድምጽ በማለትና በመነጠል መረዳት፡፡ (በሚታወቁ ስዕላዊ ድምጾች በመጠቀም)

ተማሪዎች የመምህሩን ገለጻ በመከተል እያንዳንዱን ድምጽ ማለትና መነጠል፡፡

**ቃልን መገንባት፡** ተማሪዎች የቃል ክፍሎችን በመጠቀም ለአዳዲስ ቃላት ትርጉም መስጠት ይለማመዳሉ፡፡ ወይም የቃል ክፍሎችን በመጠቀም አዳዲስ ቃላትን መመስረት፡፡

**ማንበብ፡** መምህር የሚነበቡ ቃላትን በሰሌዳ ላይ በመጻፍና ተማሪዎች በቡድን ሆነው በመመካከር ለቃላት ከፍተኛ ትርጉም እንዲሰጡ ስራ መስጠት፡፡

**አርአያ፡** መምህር ከማስተማሪያ መጽሀፉ ላይ ደምጹን ከፍ በማድረግ ምሳሌ በመሆን ያነባል፤ ይህ ደግሞ ተማሪዎች የማንበብ ችሎታቸው ከፍ እንዲል ያግዛል፡፡

**ተደጋጋሚ የቃል ንባብ፡** መምህር ተማሪዎች በተደጋጋሚ የቃል ንባብ እንዲያደርጉ መወሰን፡፡

**ቀስበቀስ ማብቃት፡** በጣታቸው እያመለከቱ ማንበብና በገደል ማሚቶ ምንባብ መማር፣ በህብረት ማንበብ፣ ከጓደኞቻቸው ጋር ተባብረው ማንበብ በማንሾካሾክ ከሌላ አንባቢ ጋር ማንበብ፡፡

## 4.ምዘና

- ቃላዊ ጥያቄዎችን መጠየቅና ግብረመልስ መስጠት
- አካላዊ ምላሽ
- ተማሪዎች በግላቸው ለጥያቄዎች የሚሰጡት ምላሽ
- ኢመደበኛ ቁጥጥር
- ምልከታ
- በምስል መወከል
- በሚታይ መወከል
- ተራ በተራ ማቅረብ
- ስልታዊ ልምምድ

**ክፍለጊዜ፡ አንድ**

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

## ቅድመ ማዳመጥ

መምህር ከትምህርቱ ርዕስ ጋር የሚገናኝ አጫጭር ቀልዶች፣ መዝሙሮች፣ እንቆቅልሾች የመሳሰሉትን በማቅረብ የሚደመጠውን ታሪክ በንቃት እንዲከታተሉ ያድርጓቸው፡፡ ተማሪዎች በመጽሀፉ ላይ ያሉትን ስዕሎች አይተው ስለምን እንደሚማሩ እንዲገምቱ መጠየቅ፣ ግምታቸውን ማጠናከር ወይም መለወጥ እንደሚችሉ ይንገሯቸው፡፡ በመቀጠል ከዚህ በታች የቀረቡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ተማሪዎችን በቃል በመጠየቅ የቀደመ እውቀታቸውን ይቀስቅሱ፡፡

1. የምታዳምጡት ስለምን ይመሰላችዋል?
2. ትምህርት ቤታችሁ ከመኖሪያ ቤታችሁ ምን ያህል ይርቃል?
3. የመማሪያ ክፍላችሁ ምን ምን ይዟል?

| |
|---|
| መምህር የሚደመጠውን ታሪክ በዝግታ ሁለቴ ደጋግመው ያንብቡላቸው፡፡ በጽሁፉ ውስጥ ከቀረቡት ቃላት ውስጥ አዳዲስና ከባድ ቃላትና ሀረጋት ይሆናሉ ብለው ያሰቧቸውን በቅድሚያ ፍቺ ይስጧቸው፡፡ በምንባቡም መሃል ንባቦትን ገታ አድርገው የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎችን ያቅርቡላቸው፡፡ |

## "ትምህርት ቤቴ"

ትምህርት ቤቴ ከመኖሪያ ቤቴ ሩቅ አይደለም፡፡ ከ20 ደቂቃ በላይ በእግር አያስኬድም፡፡ በትምህርት ቀናት ከጓደኞቼ ጋር እየተጫወትን እንሄዳለን፡፡ ስንመለስም አንድ ላይ ነው፡፡ ትምህርት ቤታችን ትልቅ የኳስ ሜዳ አለው፡፡ በክፍላችን ውስጥም ሠሌዳ፣ ጠረጴዛ፣ ወንበር አሉ ፡፡ እንዲሁም ማጥፊያና ጠመኔ አሉት፡፡ ግድግዳው ላይም ልዩ ልዩ ስዕሎች ተለጥፈዋል፡፡

( **የማዳመጥ ጊዜ**) የተለጠፉት ስዕሎቹ ምን ምን ይመስላችኋል?

ከተለጠፉት ስዕሎች ውስጥ በጣም የምወደው የአማርኛን ፊደል ገበታ ያለው ነው፡፡ ምክንያቱም አንዳንድ የሚያስቸግሩኝን ፊደሎች ቀና ብዬ በማየት እረዳለሁ፡፡ ሆኖም

በክፍላችን የተሰቀሉት ስዕሎች ረጅም ጊዜ ስላገለገሉ አርጅተው እየተበላሹ ነው፡፡ ስለዚህም እኛ ተማሪዎች ከመምህራችን ጋር በመሆን በአዲስ ለመተካት ተስማምተናል::

### ድህረ ማዳመጥ

መምህር ተማሪዎች ማዳመጣቸውን የሚፈትሹ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡ ጥያቄዎችን በተናጠል በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡

1. ከተለጠፉት ስዕሎች ልጁ/ልጅቷ የምትወደው የቱን ነው? ለምን?
2. ተማሪዎች ያረጁትን ምስሎች ከማን ጋር በመሆን ለመተካት ተስማሙ?

**ክፍለጊዜ፡ሁለት**

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

መምህር በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የቀረበውን ምስል ተማሪዎች አይተው ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ትምህርት ቤት ሲመጡ የተሰማቸውን ነገር ለክፍል ጓደኞቻችው በንግግር እንዲያቀርቡ ያበረተቷቸው፡፡ እያንዳንዱም ተማሪ የተሰማውን ስሜት እንዲናገር ለተማሪዎች በየተራ እድል ይስጧቸው ፡፡ ተማሪዎችዎ ሳይፈሩ እንዲናገሩ መበረታቻ ያድርጉላቸው፡፡ በንግግራቸው ውስጥ ስህተት እንኳን ቢናገሩ በብልሀት በማስተካከል ይለፏቸው፡፡ ዋናው ጉዳይ የንግግር ክሂል ማዳበራቸው ስለሆነ ያድንቋቸው፡፡ እርስዎም እገዛ ያድርጉላቸው፡፡ ለያንዳንዱ ተማሪ ሙከራ ሌሎች ተማሪዎች እንዲያጨበጭቡላቸው ያድርጉ፡፡

እባክዎ መምህር ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ሲያጋጥሙዎት ተገቢውን እገዛ ያድርጉላቸው፣ ተጨማሪ መለማመጃ ጊዜም ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ፡ ሶስት እስከ አስራ ስድስት**

## ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

መምህር ከክፍለጊዜ 3-16 ድረስ የቀረቡ ተተኳሪ ፊደላትን ((ተ፣ ቸ ፣ነ፣ ኘ፣ አ እና ዘሮቻቸው) ድምጽና ቅርጽ አዋህዶ ለማስለየት በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡትን የፊደላት ቅርጽና ምስል ድምጽንም በመጨመር እንዲያዛምዱ ይርዷቸው፡፡ ይህንን ሲተገብሩ በቅድሚያ እርሶ ይስሩ፣ በመቀጠልም ከተማሪዎችዎ ጋር አብረው ይስሩ፣ በመጨረሻም ተማሪዎችዎ እራሳቸውን ችለው በተናጥል እንዲሰሩ ይርዷቸው፡፡ ተማሪዎች የሚያውቋቸው በተተኳሪ ድምጾች የተመሰረቱ ቃላት እንዲጠሩልዎት

ያድርጉና የተወሰኑትን ይምረጡላቸው፡፡ ከዚያም የተመረጡትን ቃላት በጋራና በተናጠል ያለማምዷቸው፡፡ ተማሪዎች ተተኳሪ ፊደሎች ያሉበትን ቃላት ሲጠሩ በማጨብጨብ ተተኳሪ ፊደሉን እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡ እባክዎ መምህር ተማሪዎቹ ይህንኑ ለተወሰነ ጊዜ እየደጋገሙ እንዲለማመዱ ያትጓቸው፡፡ ተተኳሪ ድምፆች በቃል መነሻ፣ በቃል መሀከልና በቃል መድረሻ ላይ ሊመጡ እንደሚችሉ ግንዛቤ ለመፍጠር ድምፆቹ ያሉባቸውን ቃላት በቃል እያቀረቡ እንዲለማመዱ ይሁን፡፡ ለምሳሌ "ተ" በቃል መነሻ "ተማረ" በቃል መሃል "ገተረ" በቃል መጨረሻ "ገመተ" እንደሚገኙ በሁለም ተተኳሪ ድምጾች በቂ ምሳሌ በመስጠት ያለማምዱ፡፡ በተጨማሪም በየክፍለጊዜው የሚማሩትን ፊደላት ቅርጽ በባለቀለም ወረቀት ግድግዳ ላይ መለጠፍ ፣ ፊደላትን ጎላ አድርጎ በሰንጠረዥ ማቅረብ፣ በካርቶን ላይ ፍላሽ ካርዶችን አዘጋጅቶ መጠቀም ፣ ፍላሽ ካርዶችን ጠረጴዛ ላይ በታትኖ በማሰቀመጥ እንዲመርጡ ማድረግ፣ በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ከቀረቡት ቃላት በተጨማሪ ተማሪዎች ሌሎችን እንዲያፈልቁ ማበረታታት፣ አንድ ተማሪ ከሳጥን ውስጥ ተራ በተራ ፍላሽ ካርድን እንደ እጣ በማውጣት፣ ያወጣውን ከፍ አድርጎ በማሳየት ሌሎች ተማሪዎች እንዲጠሩ በማድረግ ትምህርቱን ማቅረብ ይቻላል፡፡

መምህር ከመልመጃ አንድ እስከ አስራ አራት ያሉት መልመጃዎች በቃል ውስጥ ያሉ ድምጾች(ፊደሎች) እየነጣጠሉ እና እያጣመሩ ያለማምዷቸው፡፡ ይህን ሲተገብሩ አስቀድመው እርሶ በሞዴልነት ነጥለውና አጣምረው ያመልክቷቸው፡፡ በመቀጠልም ይህንኑ ተግባር ከተማሪዎችዎ ጋር በህብረት ይስሩ፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎች በተናጠል እራሳቸውን ችለው እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡ በምሳሌው መሰረትም ተማሪዎች ድምጾችን እየነጣጠሉና እያጣመሩ ቃሉን በትክክልና በፍጥነት እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡ በቃል ውስጥ ያሉትን ድምጾች(ፊደሎች) ሲነጥሉ እንዲያጨበጭቡ ያድርጓቸው፡፡ ተማሪዎቹም በመማሪያ መጽሀፉ ላይ ያሉትን ተግባራት እየሰሩ እንዲለማመዱ ይርዷቸው፡፡ እያንዳንዱን ድምጽ በፍጥነት እየጠሩ የንባብ ፍጥነታቸው እንዲጨምር ያድርጓቸው፡፡ ይህንንም ተግባር በመደጋገም ያሰሯቸው፡፡ እገዛ ለሚፈልጉ ተማሪዎች እገዛ በማድረግ በትክክልና በተገቢው ፍጥነት እንዲያነቡ ይርዷቸው፡፡ መልመጃዎችንም በደብተራቸው ላይ ጽፈው እንዲለማመዱ ይዘዟቸው፡፡ የተማሪዎችን ተሳትፎ ለማሳደግ ያበረታቷቸው፡፡

መምህር ትምህርቱን ተጨባጭ ለማድረግ ፊደላቱን ለየብቻ በፍላሽ ካርድ አዘጋጅተው በቀኝና በግራ እጆ ወደ ላይ ከፍ አድርገው በመያዝ እየነጠሉና እያገጣጠሙ

ያመልክቷቸው፡፡ ተማሪዎችም ይህንኑ ተግባር ተራ በተራ እየገጠሙና እየነጠሉ እንዲያመለክቱ ይርዷቸው፡፡ ፊደላቱን በአካባቢ በሚገኙ ቁሳቁሶች ሰርተው እንዲመጡ የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

# ትምህርት አራት፡ ቃላት

መምህር በትምህርት አራት፡ ውስጥ ተማሪዎች ስለትምህርት ቃላት ይማራሉ፡፡ የትምህርት ቃላት ተብለው የተመረጡት ተማሪዎች ትምህርታቸውን ሲከታተሉ መምህራን የተለያዩ የመማር ማሰተማር ተግባራትን ሲያከናውኑ የሚገለገሉባቸው ናቸው ተብለው የተመረጡ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ክፍሉን ለመቆጣጠር፣ የመማር ማስተማሩን የሚረዱ ተጨማሪ ቃላትን አክለው ማስተማር ይችላሉ፡፡ትምርቱን ሲተገብሩ በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ለናሙና የቀረቡ ምስሎችን በመጠቀም ትምህርታዊ ቃላትን ተማሪዎች ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እንዲጠሯቸው በቅድሚያ እርሶ ቃላቱን ይጥሩላቸው፣ በመቀጠል ከተማሪዎችዎ ጋር በህብረት ይጥሯቸው፤ በመጨረሻም ተማሪዎች በተናጠል እራሳቸውን ችለው እንዲጠሯቸው ይርዷቸው፡፡ ተማሪዎችዎን በተለያየ ዘዴ ማበረታታትዎን አይዘንጉ፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች ሌሎች የትምህርት ቃላትን እንዲያፈልቁ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ያግዟቸው፡፡ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች (ምስል፣ ፍላሽ ካርድ…) መጠቀም እንዳለብዎ አይዘንጉ፡፡

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

# ትምህርት አምስት፡ መጻፍ

መምህር በትምህርት አምስት ውስጥ ተማሪዎች ባለሶስት ፊደሎች የያዙ ቃላትን የሚጽፉበት ነው፡፡ ተማሪዎች በጽህፈት ክሂል የዳበረ ልምምድ ስለሌላቸው የመምህሩ ክትትልና እገዛን በጣም ይፈልጋሉ፡፡ መምህርም ይህን ተገንዝበው የቅርብ ክትትልና እገዛ ያድርጉላቸው፡፡ይህን ተግባር ተማሪዎች ከመተግበራቸው በፊት እርሶ ተዘበራርቀው የተቀመጡት ድምጾች አሰተካክለው በመጻፍ ያሳይዋቸው፡፡ በመቀጠል ሌሎችን ቃላት ከተማሪዎች ጋር ሆነው በመስራት ተማሪዎችዎ በራሳቸው የመተማመን መንፈስ አዳብረው ለየብቻቸው እንዲጽፍ ያለማምዷቸው፡፡ ቃላቱንም ሲመሰርቱ ፍቺ የሚሰጡ መሆን እንዳለባቸው ያስገንዝቧቸው፡፡ ቃላቱንም ሲጽፉ የፊደሎችን ቅርጽ፣ ቃላቱ

ትክክለኛ ፍቺ መስጠታቸውን እና መስመር መጠበቃቸውን ያረጋግጡ፡፡ ተማሪዎቹ በሚያደርጉት ሙከራ ሁሉ ያበረታቷቸው፡፡

በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ በመልመጃ አስራ አምስት ላይ የተሰጠውን ሰንጠረዥ ተማሪዎችዎ በደብተራቸው ላይ እንዲጽፉ በማድረግ እንዲለማመዱ ያድርጓቸው፡፡ ሰንጠረዡንም በሚከተለው መልክ ያስሞሏቸው፡፡

የፍደሎቹን ቦታ በማቀያየር ባለሶስት እግር ቃላት መመስረት

| | |
|---|---|
| ማ ተ ሪ | ተማሪ |
| ዳ ሌ ሰ | ሰሌዳ |
| ጠ አ ና | አጠና |
| ደ ል ፊ | ፊደል |
| ተ ና ፈ | ፈተና |
| ፍ ክ ል | ክፍል |
| የ ጠ ቀ | ጠየቀ |
| ሥ ር ዕ | ርዕሥ |

# ምዕራፍ አራት

# ጓደኞሞች

(18 ክፍለ ጊዜ)

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ምንባቡን ካዳመጡ በኋላ መልእክቱን ይገነዘባሉ፡፡
- የሚታወቁ ቃላትን ይለያሉ፡፡
- አዳዲስ ፊደላትን/ድምጾችን (ከ፣ ሠ፣ ዘ፣ ዠ) ያነባሉ፡፡
- ደምጽንና ፊደላትን ያዛምዳሉ፡፡

## 2. ዝርዝር ይዘቶች

- ከምእራፍ ሶስት የሚቀጥሉ አምስት የተመረጡ ድምጾች/ፊደላት ማዛመድ
- ተመሳሳይ ድምጽ ያላቸውን ቃላት መለየት
- ተዘውታሪ ቃላት መለየት
- የቃላት ችሎታ ማዳበር
- ድምጾችን ማዳመጥና መናገር
- ጽንሰሀሳባዊ ስያሜ
- ድምጾችን ከሚወክሏቸው  በትክክል፣ በፍጥነት፣ በጥሩ አገላለጽ አንብቦ መረዳት

## 3.የመማር ብልሀቶችና መሳሪያዎች

መምህር ተማሪዎችን ማነሳሳት  የቀደመ ዕውቀታቸውን የማዳመጥ እውቀታቸውን በጥያቄ መልክ በማቅረብ ቀጥለው ምን እንደሚያዳምጡ እንዲገምቱ ማድረግ

መምህር ምንባቡን ማንበብ

ተማሪዎች፡ ሀሳብን ማድመጥና መለየት ከርዕሱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ቃላት መለየት

(የድምጾችን/ የፊደላትን ቅርጽ፣ የባለቀለም ወረቀት ፣ የካርቱን ስዕሎች ፣ የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ ተጠቀም)

**መለየት፡** መምህር አስር በተመሳሳይ ድምጾች የሚጀምሩ /የሚጨርሱ ቃላትን አቅርቦ ተማሪዎች ደግሞ አምስት በትክክል የሚመሳሰሉ ቃላትን መለየት፡፡
ተማሪዎች በተመሳሳይ ድምጾች የሚጀምሩ/የሚጨርሱ አዳዲስ ቃላትን ይለያሉ፡፡

**መቁጠር፡** ተማሪዎች በቃላት ውስጥ ባሉ ድምጾች መጠን ያህል ያጨበጭባሉ፡፡ (የድምጾችን/ የፊደላትን ቅርጽ፣ የባለቀለም ወረቀት ፣ የካርቱን ስዕሎች ፣ የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ ተጠቀም)

**ተዘውታሪ** ቃላት መምህር ለተወሰኑ ቃላት ትርጉም ይሰጣል፡፡ ተማሪዎች ለተቀሩት ቃላት ትርጉም ይሰጣሉ፡፡

**ተመሳሳይ ዜማ** መምህርተማሪዎች ተመሳሳይ ቀለም ያላቸው የአንድ ቤተሰብ ቃላት እንዲፈጥሩ ይፈቅድና ሰሌዳ ላይ መጻፍ፡፡
ተማሪዎች ተመሳሳይ ቀለም ያላቸውን ቤተሰባዊ ቃላት ይጠራሉ (ቀስበቀስ ራስን የማብቃት ሞደልን ተጠቀም)
**ማጣመርና መነጠል፡** መምህርበቃላት ውስጥ ያሉትን ድምጾች ይጠራል፤ ተማሪዎችም መምህር የጠራቸውን ድምጾች በፍጥነት መጥራት፡፡
መምህር፡ ፊደላትን በማሳየት መነጠል
**ቀስበቀስ ማብቃት፡** ሀ. መምህር ፊደላትን እያሳየ መጥራት፡፡
ለ. መምህር ፊደላትን እያሳየ ተማሪዎች እንዲጠሩ ይጠይቃል፡፡
ሐ. ተማሪዎች ፊደላትን እያሳዩ መጥራት፡፡
**እንቅስቃሴ፡** መምህር ድምጾችን ከእንቅስቃሴ ጋር እንዴት እንደሚገናኙ ያሳያል፡፡ይሄ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን ማድረግ ድምጾችንና ፊደላትን እንዲያስታውሱ መርዳት፡፡

**የአፍ እንቅስቃሴ፡** ተማሪዎች ድምጾች በአንደበት ውስጥ እንዴት እንደሚፈጠሩ ማስተማር፡፡

**ቃላትን መመስረት፡** ተማሪዎች የተለያዩ የቃል ክፍሎችን ተጠቅመው አዳዲስ ቃላትን መመስረት፡፡

**ድምጾችን/ፊደላትን በአየር ላይ መጻፍ፡**

መምህር ድምጾችን ወይም የፊደል ስሞችን ሲጠራ ተማሪዎች በአየር ላይ ወይም በሚጻፍ ነገር ላይ ፊደላትን በአመልካች ጣታቸው ይጽፋሉ፡፡ ተማሪዎች ፊደላትን በአየር ላይ ወይም በሚጻፍ ነገር ላይ መጻፍ፡፡

**መጻፍ፡** ሀ. መምህር በቃላት ውስጥ ያሉትን ድምጾች በማሳየት እያንዳንዳቸውን ይጠራል ከዚያም ድምጾቹን ማጣመር፡፡ (በታወቁ ትዕምርተ ድምጻዊ ድምጾች መጠቀም)

**አርአያ** መምህር ተማሪዎች ማንበብ ከሚጠበቅባቸው ደረጃ በላይ ድምጹን ከፍ አድርጎ ማንበብ፡፡

**ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ** መምህር ተማሪዎች ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ የሚያደርጉበትን እድል ያቀርባል፡፡ ተማሪዎች በተደጋጋሚ ማንበብ

**ቀስበቀስ የማብቃት ሞዴል፡** በጣታቸው እያመለከቱ ማንበብና በገደል ማሚቶ ምንባብ መማር፣ በህብረት ማንበብ፣ ከጓደኞቻቸው ጋር ተባብረው ማንበብ፣
ቀስ ብሎ ከሌላ አንባቢ ጋር ማንበብ

**ድምጾችን/ፊደላትን በአየር ላይ መጻፍ**

## 4. ምዘና

- በቃል/በጽሁፍ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- አካላዊ ምላሽ
- ተማሪዎች በግላቸው ለጥያቄዎች የሚሰጡት ምላሽ
- ኢመደበኛ ቁጥጥር
- ምልከታ
- በሚታይ ነገር መወከል
- ተራ በተራ ማቅረብ
- መውጫ ካርዶች
- ስልታዊ ልምምድ

**ክፍለጊዜ፡ አንድ**

# ትምህርት አንድ፡ማዳመጥ

## ቅድመ ማዳመጥ

መምህር ወደ ንባብ ተግባር ከመግባቶ በፊት ተማሪዎች በመጽሀፉ ላይ ያሉትን ስዕሎች አይተው ስለምን እንደያዳምጡ እንዲገምቱ መጠየቅ፡፡ ግምታቸውን ማጠናከር ወይም መለወጥ እንደሚችሉ ይንገሯቸው፡፡ የዛሬው የሚደመጠው ታሪክ "ብሩክና ኦላና" የሚለውን ሰሌዳ ላይ በመጻፍ፣ በዚህ ርዕስ ስር ምን የሚጻፍ እንደሚመስላቸው ተማሪዎች እንዲገምቱ ያድርጉ፡፡ የተማሪዎቹን የቀደመ እውቀት መቀስቀስ እንደሚያስፈልግ አይዘንጉ፡፡ ለዚህም የሚከተሉትንና የመሳሰሉትን ቅድመ ማዳመጥ ቀስቃሽ ጥያቄዎች ይጠይቁ፡፡

1. የምትወዱት ጓደኛ ስም ማን ነው?
2. ከጓደኞቹ ጋር ምን ማድረግ ያስደስታችኋል?

| |
|---|
| መምህር የሚደመጠውን ታሪክ በዝግታ ሁለቴ ደጋግመው ያንብቡላቸው፡፡ በጽሁፉ ውስጥ ከቀረቡት ቃላት ውስጥ አዳዲስና ከባድ ቃላትና ሀረጋት ይሆናሉ ብለው ያሰቧቸውን በቅድሚያ ፍቺ ይስጧቸው፡፡ በምንባቡም መሃል ንባቦትን ገታ አድርገው የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎችን ያቅርቡላቸው፡፡ |

### "ብሩክና ኦላና"

ብሩክና ኦላና ጓደኛሞች ናቸው፡፡ አብረው ወደ ት/ቤት ይሄዳሉ፡፡ ትምህርታቸውን በጋራ ያጠናሉ፡፡ በመሆኑም በትምህርታቸው ጎበዞች ናቸው፡፡ ሲጫወቱም አንድ ላይ ነው፡፡ብሩክና ኦላና እየተሽቀዳሙ መሮጥ ይወዳሉ፡፡ አንድ ቀን ሲሮጡ ብሩክ ወደቀ፡፡ ኦላናም በጣም ደነገጠ፡፡

**(ማዳመጥ ጊዜ)** ብሩክ ተጎድቶ ይሆን?

የመንደሩ ሰዎች ተሯሩጠው አነሱት፡፡ ብሩክም እግሩ ተላጠ፡፡ ኦላናም ጓደኛው በመጎዳቱ ከልብ አዘነ፤፡ አቅፎት አባበለው፡፡ ወደቤትም ተቃቅፈው ሄዱ፡፡ ከዚህ በኋላ ግን ብሩክ ሲሮጥ ተጠንቅቆ ነው፡፡

**ድህረ ማዳመጥ**

**መምህር/ት** ማዳመጣቸውን የሚፈትሹ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡ ጥያቄዎችን በተናጠልና በተራ በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡

1. ኦላና ለምን አዘነ?
2. ኦላና ማንን አቀፈ?
3. ብሩክና ኦላና በጋራ የሚሰሯቸውን ነገር ዘርዝሩ፡፡

**ክፍለጊዜ፡ ሁለት**

## ትምህርት ሁለት ፡ መናገር

መምህር በትምህርት ሁለት ውስጥ ተማሪዎች የንግግር ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ልምምድ የሚያደርጉበት ተግባር የተቀረጸበት ነው፡፡ተማሪዎችዎም በመማሪያ መጽሀፋቸው ላይ የተሳሉትን ምሥሎች መሰራት አድርገው ንግግር እንዲያደርጉ በቅድሚያ ሞዴል የሚሆን ንግግር አድርገው በማሳየት፣ ተማሪዎችዎ ሳይፈሩ ንግግር እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው፡፡እያንዳንዱ ተማሪ በየተራ ንግግር እንዲያደርግ እድል ስጧቸው፡፡ተማሪዎች የሚያደርጉትን ንግግር ሌሎች ተማሪዎች በጥሞና እንዲያዳምጡ ካደረጉ በኋላ ፣ንግግር አድርገው ተማሪዎችዎ ሲጨርሱ እንዲያጨበጭቡላቸው ያስደርጉ፡ በንግግር ወቅትም ተማሪዎች የሚፈጽሙትን ስህተት በብልሃት እያሳይዋቸው ተማሪዎች ስህተታቸውን አውቀው ራሳቸው እንዲያርሙ ያድርጉ፡፡ የንግግር ክሂል በመደጋገም የሚዳብር ስለሆነ በመደጋገም ተማሪዎች ንግግር እንዲያደርጉ ይርዷቸው፡፡

**ክፍለጊዜ፡ ሶስት እስከ አስራ ስድስት**

## ትምህርት ሶስት፡ማንበብ

መምህር ከክፍለጊዜ 3-16 ድረስ የቀረቡ ተተኳሪ ፊደላትን ((ከ፣ወ ፣ዘ፣ገ፣ እና ዘሮቻቸው) ድምጽና ቅርጽ አዋህዶ ለማስለያት በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡትን የፊደላት ቅርጽና ምስል ድምጽንም በመጨመር እንዲያዛምዱ ይርዷቸው፡፡ይህንን ሲተገብሩ በቅድሚያ እርሶ ይስሩ፤ በመቀጠልም ከተማሪዎችዎ ጋር አብረው ይስሩ፤በመጨረሻም ተማሪዎችዎ እራሳቸውን ችለው በተናጠል እንዲሰሩ ይርዷቸው፡፡ተማሪዎች የሚያውቋቸው በተተኳሪ ድምጾች የተመሰረቱ ቃላት እንዲጠሩልዎት ያድርጉና የተወሰኑትን ይምረጡላቸው፡፡ ከዚያም የተመረጡትን ቃላት በጋራና በተናጠል ያለማምዷቸው፡፡ ተማሪዎች ተተኳሪ ፊደሎች ያሉበትን ቃላት ሲጠሩ በማጨብጨብ

ተተኳሪ ፊደሉን እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡እባክዎ መምህር ተማሪዎቹ ይህንኑ ለተወሰነ ጊዜ እየደጋገሙ እንዲለማመዱ ያትጓቸው፡፡ ተተኳሪ ድምፆች በቃል መነሻ፣ በቃል መሀከልና በቃል መድረሻ ላይ ሊመጡ እንደሚችሉ ግንዛቤ ለመፍጠር ድምፆቹ ያሉባቸውን ቃላት በቃል እያቀረቡ እንዲለማመዱ ይሁን፡፡ ለምሳሌ "ከ" በቃል መነሻ "ከመረ" በቃል መሃል "አከመ" በቃል መጨረሻ "ባረከ" እንደሚገኙ በሁለም ተተኳሪ ድምጾች በቂ ምሳሌ በመስጠት ያለማምዱ፡፡ በተጨማሪም በየክፍለጊዜው የሚማሩትን ፊደላት ቅርጽ በባለቀለም ወረቀት ግድግዳ ላይ መለጠፍ ፣ፊደላትን ጎላ አድርጎ በሰንጠረዥ ማቅረብ፣ በካርቶን ላይ ፍላሽ ካርዶችን አዘጋጅቶ መጠቀም ፣ፍላሽ ካርዶችን ጠረጴዛ ላይ በታትኖ በማሰቀመጥ እንዲመርጡ ማድረግ፣ በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ከቀረቡት ቃላት በተጨማሪ ተማሪዎች ሌሎችን እንዲያፈልቁ ማበረታታት፣ አንድ ተማሪ ከሳጥን ውስጥ ተራ በተራ ፍላሽ ካርድን እንደ እጣ በማውጣት፣ ያወጣውን ከፍ አድርጎ በማሳየት ሌሎች ተማሪዎች እንዲጠሩ በማድረግ ትምህርቱን ማቅረብ ይቻላል፡፡

መምህር ከመልመጃ አንድ እስከ አስራ አራት ያሉት መልመጃዎች በቃል ውስጥ ያሉ ድምጾች(ፊደሎች) እየነጣጠሉና እያጣመሩ ያለማምዷቸው፡፡ይህን ሲተገብሩ አስቀድመው እርሶ በሞዴልነት ነጥለውና አጣምረው ያመልክቷቸው፡፡ በመቀጠልም ይህንኑ ተግባር ከተማሪዎችዎ ጋር በህብረት ይስሩ፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎች በተናጠል እራሳቸውን ችለው እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡ በምሳሌው መሰረትም ተማሪዎች ድምጾችን እየነጣጠሉና እያጣመሩ ቃሉን በትክክልና በፍጥነት እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡በቃል ውስጥ ያሉትን ድምጾች(ፊደሎች) ሲነጥሉ እንዲያጨበጭቡ ያድርጓቸው፡፡ ተማሪዎቹም በመማሪያ መጽሀፉ ላይ ያሉትን ተግባራት እየሰሩ እንዲለማመዱ ይርዷቸው፡፡ እያንዳንዱን ድምጽ በፍጥነት እየጠሩ የንባብ ፍጥነታቸው እንዲጨምር ያድርጓቸው፡፡ ይህንንም ተግባር በመደጋገም ያሰሯቸው፡፡እገዛ ለሚፈልጉ ተማሪዎች እገዛ በማድረግ በትክክልና በተገቢው ፍጥነት እንዲያነቡ ይርዷቸው፡፡ መልመጃዎችንም በደብተራቸው ላይ ጽፈው እንዲለማመዱ ይዘዟቸው፡፡ የተማሪዎችን ተሳትፎ ለማሳደግ ያበረታቷቸው:: መምህር ትምህርቱን ተጨባጭ ለማድረግ ፊደላቱን ለየብቻ በፍላሽ ካርድ አዘጋጅተው በቀኝና በግራ እጅ ወደ ላይ ከፍአድርገው በመያዝ እየነጠሉና እያገጣጠሙ ያመልክቷቸው፡፡ ተማሪዎችም ይህንኑ ተግባር ተራ በተራ እየገጠሙና እየነጠሉ እንዲያመለክቱ ይርዷቸው፡፡ ፊደላቱን በአካባቢ በሚገኙ ቁሳቁሶች ሰርተው እንዲመጡ የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

# ትምህርት አራት፡ ቃላት

መምህር በትምህርት አራት፡ ውስጥ ተማሪዎች ስለትምህርታዊ ቃላት ይማራሉ፡፡ የትምህርት ቃላት ተብለው የተመረጡት ተማሪዎች ትምህርታቸውን ሲከታተሉ መምህራን የተለያዩ የመማር ማስተማር ተግባራትን ሲያከናውኑ የሚገለገሉባቸው ናቸው ተብለው የተመረጡ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ክፍሉን ለመቆጣጠር፣ የመማር ማስተማሩን የሚረዱ ተጨማሪ ቃላትን አክለው ማስተማር ይችላሉ፡፡ ትምህርቱን ሲተገብሩ በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ለናሙና የቀረቡ ምስሎችን በመጠቀም ትምህርታዊ ቃላትን ተማሪዎች ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እንዲጠሯቸው በቅድሚያ እርሶ ቃላቱን ይጥሩላቸው፣ በመቀጠል ከተማሪዎችዎ ጋር በህብረት ይጥሯቸው፣ በመጨረሻም ተማሪዎች በተናጠል እራሳቸውን ችለው እንዲጠሯቸው ይርዷቸው፡፡ ተማሪዎችዎን በተለያየ ዘዴ ማበረታታትዎን አይዘንጉ፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች ሌሎች የትምህርት ቃላትን እንዲያፈልቁ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ያግዟቸው፡፡ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች (ምስል፣ ፍላሽ ካርድ…) መጠቀም እንዳለብዎ አይዘንጉ::

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

# ትምህርት አምስት፡ ጽሕፈት

መምህር በዚህ በጽህፈት ትምህርት ክፍል ውስጥ ተማሪዎች በ"ሀ" ስር የተዘረዘሩትን ተተኳሪ ትዕምርቶች ከ"ለ" ስር ከተደረደሩት ቃላት ጋር እያዛመዱ የትዕምርቶችን ምልክት የሚለዩበትና ከቃላት ጋር የሚያዛምዱበት ነው፡፡ ስለዚህም ይህን መልመጃ ተማሪዎች ከማከናወናቸው በፊት በቅድሚያ ለምሳሌ የሚሆኑ ትዕምርትን( ምልክትን) ከቃል ጋር እያዛመዱ ይስሩላቸው፣ በመቀጠል ተማሪዎች ከእርሶ ጋር በመሆን አብራችሁ ስሩ፡፡ ተማሪዎችዎ ከእነዚህ ሁለት ልምምዶች በኋላ እራቸውን ችለው በየግል ትዕምርቶችን ከቃላት ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጉ፡፡ በክፍል ውስጥም በመዘዋወር የተማሪዎችን ስራ እየተመለከቱ ፣ እገዛ ለሚሹ ተማሪዎች እገዛ ያድርጉላቸው፡፡ በኢመደበኛ ዘዴም የተማሪዎችን የእርሳስ አያያዝ ይቆጣጠሩ፡፡ ተገቢ ያልሆነ የእርሳስ አያያዝ ካለ እርማት በመስጠት ተግባሩን ያከናውኑ፡፡

**ፊደላቱን ከቃላት ጋር አዛምዱ**

**ምሳሌ፡** ከ → ከመረ

| ሀ | ለ |
|---|---|
| ከ | ወንድ |
| ወ | ከበደ |
| ዘ | ዠንጥላ |
| ዠ | ዘመረች |

# ምዕራፍ አምስት

# ተክሎች

(18 ክፍለ ጊዜ)

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ምንባብን አዳምጠው ይረዳሉ፡፡
- የተመረጡ ድምጾችን/ፊደላትን (የ፣ ደ፣ ጀ፣ ገ) ይለያሉ፡፡
- የፊደል ድምጽ ግንኙነትን ይሰራሉ፡፡
- ድምጾችን ከቃላት መነጠልና ማጣመር፡፡
- ቀላል አ/ነገሮችን ይመሰርታሉ፡፡
- ተዘውታሪ ቃላትን ትርጉም ይሰጣሉ፡፡

## 2. ዝርዝር ይዘቶች

- የተመረጡ አራት ድምጾች/ፊደላት (የ፣ ደ፣ ጀ፣ ገ) መለየት
- ተዘውታሪ ቃላት/የትምህርት ቃላት
- ጽንሰ ሀሳቦችን መጥራት

## 3. የማስተማሪያ ብልሀቶችና መሳሪያዎች

መምህር ተማሪዎችን የሚያዳምጡትን ምንባብ የቀደመ ዕውቀታቸውን በመጠቀም ቃላዊ ጥያቄዎችን መጠየቅ፡፡

**መገመት**፡ ስእሎችን፣ምዕራፎችንና ቁልፍ ቃላትን በመመልከት ስለምን እንደሚያዳምጡ ይገምታሉ፡፡

**መለየት**፡ መምህር ተማሪዎች አስር ቃላትን እንዲጠሩና ከጠሩት አምስት ቃላት በተመሳሳይ ድምፅ የሚጀምሩ ቃላትን እንዲለለዩ ይጠይቃል፡፡ ተማሪዎችም አምስት በድምጽ የሚመሳሰሉ ቃላትን መጥራት፡፡ (የድምጾችን /የፊደላትን ቅርጽ፣ የባለቀለም ወረቀት ፣ የካርቱን ስዕሎች ፣ የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ ተጠቀም)፡፡

**መቁጠር**፡ በቃላት ተመሳሳይ ድምጽ ሲከሰት ያጨበጭባሉ /የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣ የባለቀለም ወረቀት ፣ የካርቱን ስዕሎች ፣ የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ መጠቀም)፡፡

ተመሳሳይ ድምጸት ተመሳሳይ ቀለም ያላቸውን ቃላት መዝሙሮችን ለመፍጠር /ቤተሰባዊ ቃላትን/መፍጠር፡፡

**ማንበብ፡** ሀ መምህር በቃሉ ውስጥ ያሉትን ድምጾች ሁሉ ያሳያል ፤ ከዚያም ድምጾቹን መነጠል፡፡

**ቃላትን መመስረት፡** ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን ቃል ክፍሎችን በመጠቀም መጻፍ ይለማመዳሉ፡፡

**ተዘውታሪ ቃላት፡** መምህር የቃላትን ቀጥተኛ ትርጉም መጻፍ፡፡

ተማሪዎችን ከቀጥተኛ ትርጉማቸው ጋር ማዛመድ፡፡

ተማሪዎች መምህራቸው መዝሙር ሲመዘመር መከተል፡፡

**መነጠልና ማጣመር፡** የተለዩ ድምጾችን ይለዩና በፍጥነት መፍጠር፡፡

(መምህር ማጣመርን ለማስተማር ቃላትን ሲከፋፍል ተማሪው የተከፋፈለውን በማጣመር ቃሉን መጥራት፡፡

**ቀስ በቀስ ራስን ማስቻል፡** ሀ. መምህር ፊደላትን ቅርጻቸውን በማሳየት የሚወክሏቸውን ድምጾች መጥራት፡፡ ለ. መምህር ቅርጻቸውን በማሳየት ተማሪዎች ድምጾችን እንዲጠሩ መጠየቅ ሐ.ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው ፊደላትን ከድምጾቻቸው ጋር በማያያዝ መጥራት፡፡

**እንቅስቃሴ፡** ድምጾችን ከእንቅስቃሴ ጋር ማያያዝ፤ ይህ ተማሪዎች ድምጾችንና/ፊደላትን ለመለየት ማስቻል፡፡

**አፋዊ እንቅስቃሴ፡** ድምጾች አንደበት ውሰጥ እንዴት እንደሚፈጠሩ መማር፡፡

**አርአያነት ፡** መምህር ተማሪዎች ካላቸው የማንበብ ችሎታ በላይ በትክክል ያነባል፡፡

**ተደጋጋሚ የቃል ንባብ፡** መምህር ተደጋጋሚ ለቃል ንባብ ያጋልጣል፤ተማሪዎችም በተደጋጋሚ ትክክለኛነትን ለማጎልበት ማንበብ፡፡

**ቀስ በቀስ ራስን የማስቻል ሞዴል፤** ጣትን በመጠቆም በገደል ማሚቶ፣ የጋራ ማንበብ፣ ከጓደኛ ጋር ማንበብ ፣ ሌላውን ተከትሎ ማንበብ፤ ድምጾችን /ፊደላትን መቅረጽ፡፡

ቀላል አ/ነገሮችን መጻፍ ፤ መምህር ሞዴል በመሆን ቀላል አ/ነገሮችን ይጽፋል፤ ተማሪዎችም ቀላል አ/ነገሮችን መጻፍ መጀመር፡፡

**በአየር ላይ መጻፍ፡** ተማሪዎች ፊደላትን በአመልካች ጣታቸው በአየር ላይ ወይም በሚጻፍ ነገር ላይ መቅረጽ፤ መምህር የፊደል ድምጾችን ይጠራል፤ ተማሪዎችም በጣታቸው በአየር ላይ ፊደላትን መጻፍ፡፡

## 4. ምዘና

- በቃልና በጽሁፍ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- ከካላዊ ምላሽ
- የተማሪዎች በግል ለጥያቄዎች የሚመልሱት አካላዊ ምላሽ
- ኢ.መደበኛ ቁጥጥር
- ምልከታ
- በስዕል መወከል
- ተራ በተራ ማቅረብ
- ስልታዊ ልምምድ

**ክፍለጊዜ፡አንድ**

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### ቅድመ ማዳመጥ

መምህር ወደ ንባብ ተግባር ከመግባቶ በፊት ተማሪዎች በመጽሀፉ ላይ ያሉትን ስዕሎች አይተው ስለምን እንደሚያዳምጡ እንዲገምቱ ይጠይቋቸው፡፡ የሚሰጡትን ግምት ማጠናከር ወይም መለወጥ እንደሚችሉ ይንገሯቸው፡፡ የሚደመጠውን ታሪክ ርዕስ "የማንጎ ተክል" የሚለውን ሰሌዳ ላይ በመጻፍ፣ በዚህ ርዕስ ስር ምን የሚጻፍ እንደ ሚመስላቸው ተማሪዎች እንዲገምቱ ያድርጉ፡፡ የተማሪዎችዎን ግምት በማድነቅ ምንባቡን አድምጠው ከጨረሱ በኋላ ግምታቸው ትክክል መሆኑን ወይም አለመሆኑን ይጠይቋቸው፡፡ የተማሪዎቹን የቀደመ እውቀት መቀስቀስ እንደሚያስፈልግ አይዘንጉ፡፡ ለዚህም የሚከተሉትንና ወይም አስፈላጊ ነው የሚሉትን ቅድመ ማዳመጥ ቀስቃሽ ጥያቄዎች ይጠይቁ፡፡

1. ከፍራፍሬ ተክሎች የቱን ትወዳላችሁ?
2. የማንጎ ተክል ምን አይነት ጣዕም አለው?
2. ማንጎ የትኛው አየር ይስማማዋል?

| |
|---|
| መምህር የሚደመጠውን ታሪክ በዝግታ ሁለቴ ደጋግመው ያንብቡላቸው፡፡ በጽሁፉ ውስጥ ከቀረቡት ቃላት ውስጥ አዳዲስና ከባድ ቃላትና ሀረጋት ይሆናሉ ብለው ያሰቧቸውን በቅድሚያ ፍቺ ይስጧቸው፡፡ በምንባቡም መሃል ንባቦትን ገታ አድርገው የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎችን ያቅርቡላቸው፡፡ |

## “የማንጎ ተክል”

ፋጤ ሰፊ የማንጎ እርሻ አላት፡፡ በእርሻው ላይም መቶ ያህል ሰዎች ተሰማርተዋል፡፡ በሚያገኙት ገቢም ቤተሰቦቻቸውን ያስተዳድራሉ፡፡ የማንጎ እርሻውንም በደንብ ይንከባከቡታል፣ ይኮተኩቱታል፣ የሚያዘጋጁትንም ማዳበሪያ ይጨምሩበታል፡፡ ማንጎ ሞቃት የአየር ንብረት ይስማማዋል፡፡ ተክሉም ሲመቸው ጥሩ ምርት ይሠጣል፡፡ የማንጎ ምርት ሲደርስ ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ይውላል፤ ወደ ውጪ ሀገሮች ይላካል፡፡

( **የማዳመጥ ጊዜ**) ማንጎ ለምን ወደ ውጭ ሀገር ይላካል?

ፋጤ የማንጎ ምርትን ወደ ተለያዩ ሀገሮች በመላክ የውጭ ምንዛሪ ታስገኛለች፡፡ ከምታገኘው ገቢም በአግባቡ ቀረጥ ትከፍላለች፡፡ ሀገራችንም ከዚህና ከሌሎች የምታገኘውን የውጭ ምንዛሪ የተለያዩ መድሀኒቶችና ማሽኖች ለመግዣነት ታውለዋለች።

### ድህረ ማዳመጥ

**መምህር/ት**

ማዳመጣቸውን የሚፈትሹ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡ ጥያቄዎችን በተናጥልና በተራ በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡

1. በማንጎ እርሻው ላይ ምን ያህል ሰራተኞች አሉ?
2. የማንጎ ተክል ምን አይነት የአየር ጸባይ ይስማማዋል?
3. ፋጤ ለምን ግብር ትከፍላለች?

**ክፍለጊዜ፡ ሁለት**

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

መምህር በዚህ ትምህርት ውስጥ ተማሪዎች የንግግር ክሂላቸውን የሚያጎለብቱበት ልዩ ልዩ ተግባር የሚያከናውንበት ነው፡፡ በቅድሚያ “ተክል”ን በተመለከተ አንድ አጭር ንግግር በማድረግ በሞዴልነት ያሳይዋቸው፡፡ በመቀጠልም ተማሪዎችዎ በመማሪያ መጽሀፋቸው ውስጥ ያሉትን ምስሎች እያዩ ምን እንደተረዱ በመጠየቅ ተማሪዎችዎ ንግግር እንዲያደርጉ ያድርጓቸው፡፡ ተክሎች ለምን ውሃና እንክብካቤ እንደሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች አጭር ንግግር እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው፡፡ በመቀጠልም በቤታቸው ጓሮ ወይም በአካባቢያቸው ያሉትን የተክል አይነቶችና የሚሰጡትን ጥቅም መሰረት በማድረግ ተራ በተራ ሁሉም ተማሪ ንግግር እንዲያደርጉ

እድል ስጧቸው፡፡ ተማሪዎች ንግግር ሲያደርጉ የሚከሰቱትን ስህተቶች በብልሀት ያርሟቸው፡

# ትምህርት ሶስት፡ማንበብ

## ክፍለጊዜ፡ ሶስት እስከ አስራ ስድስት

መምህር ከክፍለጊዜ 3-16 ድረስ የቀረቡ ተተኳሪ ፊደላትን (የ፣ ደ ፣ጀ፣ ገ እና ዘሮቻቸው) ድምጽና ቅርጽ አዋህዶ ለማስለየት በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡትን የፊደላት ቅርጽና ምስል ድምጽንም በመጨመር እንዲያዛምዱ ይርዷቸው፡፡ ይህንን ሲተገብሩ በቅድሚያ እርሶ ይስሩ፤ በመቀጠልም ከተማሪዎችዎ ጋር አብረው ይስሩ፤ በመጨረሻም ተማሪዎችዎ እራሳቸውን ችለው በተናጠል እንዲሰሩ ይርዷቸው፡፡ ተማሪዎች የሚያውቋቸው በተተኳሪ ድምጾች የተመሰረቱ ቃላት እንዲጠሩልዎት ያድርጉና የተወሰኑትን ይምረጡላቸው፡፡ ከዚያም የተመረጡትን ቃላት በጋራና በተናጠል ያለማምዷቸው፡፡ ተማሪዎች ተተኳሪ ፊደሎች ያሉበትን ቃላት ሲጠሩ በማጨብጨብ ተተኳሪ ፊደሉን እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡ እባክዎ መምህር ተማሪዎቹ ይህንኑ ለተወሰነ ጊዜ እየደጋገሙ እንዲለማመዱ ያትጓቸው፡፡ ተተኳሪ ድምፆች በቃል መነሻ፣ በቃል መሀከልና በቃል መድረሻ ላይ ሊመጡ እንደሚችሉ ግንዛቤ ለመፍጠር ድምፆቹ ያሉባቸውን ቃላት በቃል እያቀረቡ እንዲለማመዱ ይሁን፡፡ ለምሳሌ "ደ" በቃል መነሻ "ደመረ" በቃል መሃል "ወደመ" በቃል መጨረሻ "ገመደ" እንደሚገኙ በሁሉም ተተኳሪ ድምጾች በቂ ምሳሌ በመስጠት ያለማምዱ፡፡ በተጨማሪም በየክፍለጊዜው የሚማሩትን ፊደላት ቅርጽ በባለቀለም ወረቀት ግድግዳ ላይ መለጠፍ፣ ፊደላትን ጎላ አድርጎ በሰንጠረዥ ማቅረብ፣ በካርቶን ላይ ፍላሽ ካርዶችን አዘጋጅቶ መጠቀም፣ ፍላሽ ካርዶችን ጠረጴዛ ላይ በታትኖ በማሰቀመጥ እንዲመርጡ ማድረግ፣ በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ከቀረቡት ቃላት በተጨማሪ ተማሪዎች ሌሎችን እንዲያፈልቁ ማበረታታት፣ ተማሪ ከሳጥን ውስጥ እንደ ተራ በተራ ፍላሽ ካርዱን እንደ እጣ በማውጣት፣ ያወጣውን ከፍ አድርጎ በማሳየት ሌሎች ተማሪዎች እንዲጠሩ በማድረግ ትምህርቱን ማቅረብ ይቻላል፡፡

መምህር ከመልመጃ አንድ እስከ አስራ አራት ያሉት መልመጃዎች በቃል ውስጥ ያሉ ድምጾች(ፊደሎች) እየነጣጠሉን እያጣመሩ ያለማምዷቸው፡፡ ይህን ሲተገብሩ አስቀድመው እርሶ በሞዴልነት ነጥለውና አጣምረው ያመልክቷቸው፡፡ በመቀጠልም ይህንኑ ተግባር ከተማሪዎችዎ ጋር በህብረት ይስሩ፡፡በመጨረሻም ተማሪዎች በተናጠል እራሳቸውን ችለው እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡ በምሳሌው መሰረትም ተማሪዎች ድምጾችን

እየነጣጠሉና እያጣመሩ ቃሉን በትክክልና በፍጥነት እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡በቃል ውስጥ ያሉትን ድምጾች(ፊደሎች) ሲነጥሉ እንዲያጨበጭቡ ያድርጓቸው፡፡ ተማሪዎቹም በመማሪያ መጽሀፉ ላይ ያሉትን ተግባራት እየሰሩ እንዲለማመዱ ይርዷቸው፡፡ እያንዳንዱን ድምጽ በፍጥነት እየጠሩ የንባብ ፍጥነታቸው እንዲጨምር ያድርጓቸው፡፡ ይህንንም ተግባር በመደጋገም ያሰሯቸው፡፡ እገዛ ለሚፈልጉ ተማሪዎች እገዛ በማድረግ በትክክልና በተገቢው ፍጥነት እንዲያነቡ ይርዷቸው፡፡ መልመጃዎችንም በደብተራቸው ላይ ጽፈው እንዲለማመዱ ይዘዟቸው፡፡ የተማሪዎችን ተሰትፎ ለማሳደግ ያበረታቷቸው፡፡

መምህር ትምህርቱን ተጨባጭ ለማድረግ ፊደላቱን ለየብቻ በፍላሽ ካርድ አዘጋጅተው በቀኝና በግራ እጅ ወደ ላይ ከፍ አድርገው በመያዝ እየነጠሉና እያገጣጠሙ ያመልክቷቸው፡፡ ተማሪዎችም ይህንኑ ተግባር ተራ በተራ እየገጠሙና እየነጠሉ እንዲያመለክቱ ይርዷቸው፡፡ ፊደላቱን በአካባቢ በሚገኙ ቁሳቁሶች ሰርተው እንዲመጡ የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

# ትምህርት አራት፡ ቃላት

መምህር በቃላት ትምህርት ስር ተማሪዎችዎ የቃላትን ቀጥተኛ ፍቺ የሚለማመዱበት ነው፡፡ ቃላቱ በአረፍተ ነገር ውስጥ ሳይገቡ የተለያዩ ፍቺ ሊይዙ እንደሚችሉ የተለያዩ ምሳሌዎችን በመስጠት ያስረዷቸው፡፡ ለምሳሌ "ወረደ" የሚለው ቃል ተሻረ፣ ሂደ፣ ቀነሰ የሚሉትን ፍቺ ሊይዝ እንደሚችል ያመልክቷቸው፡፡ አንድ ቃል ለምሳሌ "አረፈ" የሚለውን ቃል እንዴት ልዩ ልዩ ፍቺ እንደሚሰጥ ይጠይቋቸው፤ በተጨማሪም መፅሐፉ ላይ በተሰጠው ምሳሌ መሰረት ለቃላት ፍቺ እየሰጡ ያለማምዷቸው፤ የተማሪዎችንም መልስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይፃፉላቸው፡፡ በመቀጠል በመማሪያ መጽሀፋቸው ውስጥ በመልመጃ አስራ አምስት የተሰጡተን ቃላት በደብተራቸው ጽፈው ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡ መልሳቸውንም ጎን ካለው ጓደኛቸው ጋር በማስተያየት ለእርሶ ያሳዩ ፡፡ እርሶም ከተማሪዎችዎ ሙከራ በኋላ መልሱን በሰሌዳ ላይ ይጻፉላቸው፡፡ የተማሪዎችዎን ሙከራም ያድንቁላቸው፡፡

**መልመጃ፡ አስራ አምስት**

አጠና - አነበበ / ተመራመረ / አወቀ ...

ቀበረ- ደበቀ / ሰውረ/ ሸፈነ ...

ገመሰ - ከፈለ / ቆረሰ / ሰበረ...

ደመረ- ጨመረ / ከመረ / አበዛ...

ዘመረ- ዘፈነ/ አዜመ / ...

ጎበዘ - በረታ / ጀገነ/ ደፈረ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

## ትምህርት አምስት፡ መጻፍ

መምህር በዚህ ክፍል ትምህርት ስር ተማሪዎች ቀላል አረፍተነገሮችን የሚያዋቅሩበት ነው፡፡ ተማሪዎች ተራ ወይም ቀላል አረፍተነገሮችን ከመተግበራቸው በፊት በሶስቱ ሳጥን ውስጥ ካሉት ቃላት የተወሰኑ አረፍተነገሮችን እየሰሩ ያሳይዋቸው፡፡ አረፍተ ነገር ሲመሰርቱም አረፍተ ነገሩ ሙሉ መልክት መያዝ እንዳለበት ያስገንዝቧቸው፡፡ በመቀጠል የተወሰኑ ጥያቄዎችን ከተማሪዎችዎ ጋር ሆነው ይስሩ፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎች እራሳቸውን ችለው አረፍተነገር እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡ ተማሪዎች መልመጃዎችን ሲሰሩ የሚያጋጥማቸውን ችግር በቅርብ በመከታተል እገዛ ያድርጉላቸው:: ሁሉም ተማሪዎች ከሞከሩ በኋላ ተገቢውን መልስ ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ተማሪዎች በደብተራቸው ላይ እርማት እንዲወስዱ ያድርጓቸው፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

# የመንገድ ደህንነት

(18ክፍለ ጊዜ)

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ምንባብን በማዳመጥ መልእክትን ይጨብጣሉ፡፡
- በአዳዲስ ፊደላት ቃላትን(ጠ፣ ጨ፣ ጸ፣ ፀ) ይጽፋሉ፡፡
- ቀላል አ/ነገሮችን ይጽፋሉ፡፡
- ቅጥያዎችን ከቃላት ይለያሉ፡፡

## 2. ዝርዝር ይዘቶች

- ድምጻዊ ግንዛቤን አዳምጦ ማዳመጥና መናገር፤
- የተመረጡ አምስት ድምጾች (ጠ፣ ጨ፣ ጸ፣ ፀ)
- የትምዕርተ ድምጽ ግንዛቤ፡ ፊደል ድምጽ ግንኙነት
- ተዘውታሪ /የትምህርት ቃላት
- የቃላት እድገት
- ቃላትን መተርጎም
- ድምጾችን ማንበብና መጻፍ
- የፊደል (ድምጽ) ግንኙነትን በትክክለኛነት፣ በጥሩ አገላለጽ፣ በተገቢ ፍጥነትና በመረዳት ማንበብ
- ፊደላትን በትክክል መጻፍ
- ድምጸታዊ ግንዛቤ፡ የሚታወቁ ቃላትና አ/ነገሮችን ከታወቀ የድምጸት ደረጃ ጋር

## 3. የማስተማሪያ ብልሀቶችና መሳሪያዎች

መምህር ቃላትን ያነባል/ይዘምራል (ለምሳል ቀኝ ፣ ግራ፣ መንገድ፣ ወዘተ)፡፡

ተማሪዎች ከላይ የቀረቡትን ቃላት በማዳመጥ ለብቻቸው ማንበብ፡፡

**መለየት፡** መምህርአስር በተመሳሳይ ድምጾች የሚጀምሩ/የሚጨርሱ ቃላትን አቅርቦ ተማሪዎች ደግሞ ስድስት በትክክል የሚመሳሰሉ ቃላትን ይለያሉ፡፡

ተማሪዎች በተመሳሳይ ድምጾች የሚጀምሩ/የሚጨርሱ አዳዲስ ቃላትን ይለያሉ፡፡ (/የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣ የባለቀለም ወረቀት ፣ የካርቱን ስዕሎች ፣ የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ መጠቀም)

**ቃላትን መመስረት**፡ ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን የቃል ክፍሎችን በመጠቀም መጻፍ፡፡

**ተዘውታሪ ቃላት**፡ በከፍተኛ ደረጃ ድግግሞሽ ያላቸውን ቃላት በፍጥነት የመገንዘብ ችሎታን ማጎልበት፡፡

**መቁጠር**፡ በቃላት ውስጥ ተመሳሳይ ድምጾች ሲያጋጥሙ ማጨብጨብ /የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣ የባለቀለም ወረቀት ፣ የካርቱን ስዕሎች ፣ የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ መጠቀም)

**ድምጸት**፡ ተማሪዎች ተመሳሳይ ቀለም ያላቸውን ቃላት ሲጠሩ መምህር በሰሌዳ ላይ ምልክት ማድረግ

ቀስ በቀስ ራስን ማስቻል፡ ሀ. መምህር ፊደላትን እያሳየ ይጠራል ለ. መምህር ፊደላትን እያመለከተ ተማሪዎች እንዲናገሩ ይጠይቃል ሐ.ተማሪዎች ብቻቸውን ፊደላትን እያሳዩ መጥራት

**እንቅስቃሴ**፡ ድምጾችን ከእንቅስቃሴ ጋር ያገናኛል፡፡ተማሪዎች አፋቸውን ማንቀሳቀሳቸው ድምጾችን መለየት እንዲችሉ ማገዝ፡፡

**የአንደበት እንቅስቃሴ**፡ተማሪዎች ድምጾች አንደበት ውሰጥ እንዴት እንደሚፈጠሩ መማር፡፡

**ማንበብ**፡ሀ. መምህር በቃላት ውስጥ ያሉትን ድምጾች ይጠራል፤ከዚያም ድምጾችን ማጣራት (በታወቁ የፊደል ድምጽ ግንኙነት)

**አርአያነት**፤ መምህር ተማሪዎች ካላቸው የማንበብ ችሎታ በላይ በትክክል ያነባል

ተደጋጋሚ የቃል ንባብ መምህር ተደጋጋሚ ለቃል ንባብ ያጋልጣል፤ ተማሪዎችም በተደጋጋሚ ትክክለኛነትን ለማጎልበት ማንበብ

**ቀስ በቀስ ራስን የማስቻል ሞዴል**፤ ጣትን በመጠቆም በገደል ማሚቶ፣ የጋራ ንባብ፣ ከጓደኛ ጋር ማንበብ ፣ሌላውን ተከትሎ ማንበብ፡፡

ድምጾችን /ፊደላት/ን መቅረጽ

ቀላል አ/ነገሮችን መጻፍ፤ መምህር ሞዴል በመሆን ቀላል አ/ነገሮችን ይጽፋል፤ ተማሪዎችም ቀላል አ/ነገሮችን መጻፍ መጀመር

**በአየር ላይ መጻፍ፡** ተማሪዎች ፊደላትን በአመልካች ጣቶቻቸው በአየር ላይ ወይም በሚጻፍ ነገር ላይ ይቀርጻሉ፤ መምህር የፊደል ድምጾችን ይጠራል፤ ተማሪዎችም በጣቶቻቸው በአየር ላይ ፊደላትን መጻፍ፡፡

## 4. ምዘና

- በቃልና በጽሁፍ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- አካላዊ ምላሽ
- የተማሪዎች በግል ለጥያቄዎች የሚመልሱት አካላዊ ምላሽ
- ኢ-መደበኛ ቁጥጥር
- ምልከታ
- በስዕል መወከል
- ተራ በተራ ማቅረብ
- ስልታዊ ልምምድ
- መውጫ ካርድ

**ክፍለጊዜ፡ አንድ**

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### ቅድመ ማዳመጥ

መምህር ከዚህ ትምህርቱ ርዕስ ጋር የሚገናኝ አጫጭር ቀልዶች ፣መዝሙሮች ፣ እንቆቅልሾች የመሳሰሉትን በማቅረብ የሚደመጠውን ታሪክ በንቃት እንዲከታተሉ ለተማሪዎችዎ ያቅርቡላቸው፡፡ተማሪዎች በመጽሀፉ ላይ ያሉትን ስዕሎች አይተው ስለምን እንደሚያዳምጡ እንዲገምቱ መጠየቅ፣ግምታቸውን ማጠናከር ወይም መለወጥ እንደሚችሉ ይንገሯቸው፡፡ በመቀጠል ከዚህ በታች የቀረቡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ተማሪዎችን በቃል በመጠየቅ የቀደመ እውቀታቸውን ይቀስቅሱ፡፡

1. የመኪና መንገዶችን እንዴት ታቋርጣላችሁ?
2. የትራፊክ መብራት አይነቶችን ዘርዝሩ?

> መምህር የሚደመጠውን ታሪክ በዝግታ ሁለቴ ደጋግመው ያንብቡላቸው፡፡ በጽሁፉ ውስጥ ከቀረቡት ቃላት ውስጥ አዳዲስና ከባድ ቃላትና ሀረጋት ይሆናሉ ብለው ያሰቧቸውን በቅድሚያ ፍቺ ይስጧቸው፡፡ በምንባቡም መሃል ንባቦትን ገታ አድርገው የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎችን ያቅርቡላቸው፡፡

ትምህርት ቤታችን አጠገብ የመኪና መንገድ አለ፡፡ ተማሪዎች ሲወጡና ሲገቡ መንገዱን ያቋርጣሉ፡፡ ሲፈን የመንገድ ደህንነት ክበብ አባል ናት፡፡ የመንገድ ደህንነት ደንብን ተምራለች፡፡በሙያዋም ተማሪዎችን ታገለግላለች፡፡ የትራፊክ ልብሷን ለብሳ መኪናዎችንም ታስተናግዳለች፡፡ ተማሪዎችም ግራቸውን ይዘው እንዲጓዙ ትመክራለች፡፡ የትራፊክ መብራት አይነቶችንና ጥቅማቸውን ለተማሪዎች በማስተማር የዜግንት ግዴታዋን ትወጣለች፡፡

**(የማዳመጥ ጊዜ)** የትራፊክ መብራት ጥቅማቸው ምን ይመስላችዋል?

የትራፊክ መብራት ቀይ ሲበራ መኪና እንደሚቆሙና እግረኛች መተላለፍ እንዳለባቸው ታስረዳለች፡፡ አረንጓዴ ሲበራ ግን መኪናዎች ስለሚንቀሳቀሱ እግረኞች መቆም እንዳለባቸው ታስገነዝባለች፡፡ የትራፊክ መብራት አጠቃቀም በመዝሙር ታሰማቸዋለች::

**ድህረ ማዳመጥ ጥያቄ**

1. ሲፈን የትራፊክ ድንብን በምን ዘዴ ታስተምራለች?
2. የትራፊክ መብራት አረንጓዴ ሲበራ እግረኞች ምን ማድረግ አለባቸው?

እባክዎ መምህር ከዚህ በታች የቀረበውን መዝሙር በቅድሚያ እያዘሙ ያሳይዋቸው፣ በመቀጠል ከተማሪዎችዎ ጋር አብረው ይዘምሩ ፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎች በህብረት እንዲዘምሩ ያድርጓቸው፡፡

**የመንገድ ድህንነትን የተመለከተ መዝሙር፡፡**

ግራ ቀኝ ግራ፤
ግራዬን ይዤ እሄዳለሁ፤
ቀይ ሲበራ ጉዞ እቀጥላለሁ፤
ቢጫ ሲበራ እጠነቀቃለሁ፤
አረንጓዴ ሲሆን ከጉዞዬ እገታለሁ፤
ግራ ቀኝ ግራ፡፡
ቀይ ሲባራ ምን ታደርጋላችሁ?

**ክፍለጊዜ፡ ሁለት**

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

መምህር በዚህ የትምህርት ክፍል ተማሪዎች "የትራፊክ ደህንነትን" በተመለከተ አጭር ንግግር እያደረጉ የንግግር ክሂላቸውን የሚያዳብሩበት ነው፡፡ ስለዚህም በቅድሚ የመንገድ ድህንነትን በተመለከተ ምሳሌ የሚሆን ንግግር በማቅረብ ተማሪዎችዎ በመማሪያ መጽሀፋቸው ውስጥ ያሉትን ምስሎች መሰረት በማድረግ ስዕሎቹን በንግግር እንዲገልጹ ያድርጓቸው፡፡ የመንገድ ግራ ጠርዝ ይዞ መጓዝና የትራፊክ መብራትን አገልግሎት በተመለከተ ንግግር እንዲያደርጉ ለሁሉም ተማሪዎች ተራ እየሰጡ እንዲለማመዱ ያድርጓቸው፡፡ ለተማሪዎችዎም እገዛና አድናቆት ያድርጉላቸው፡፡

**ክፍለጊዜ፡ ሶስት እስከ አስራ ስድስት**

## ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

መምህር ከክፍለጊዜ 3-16 ድረስ የቀረቡ ተተኳሪ ፊደላትን (ጠ፣ ጨ፣ ጰ፣ ፀ እና ዘሮቻቸው) ድምጽና ቅርጽ አዋህዶ ለማስለየት በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡትን የፊደላት ቅርጽና ምስል ድምጽንም በመጨመር እንዲያዛምዱ ይርዷቸው፡፡ ይህንን ሲተገብሩ በቅድሚያ እርሶ ይስሩ፤ በመቀጠልም ከተማሪዎችዎ ጋር አብረው ይስሩ፤ በመጨረሻም ተማሪዎችዎ እራሳቸውን ችለው በተናጠል እንዲሰሩ ያርዷቸው፡፡ ተማሪዎች የሚያውቋቸው በተተኳሪ ድምጾች የተመሰረቱ ቃላት እንዲጠሩልዎት ያድርጉና የተወሰኑትን ይምረጡላቸው፡፡ ከዚያም የተመረጡትን ቃላት በጋራና በተናጠል ያለማምዷቸው፡፡ ተማሪዎች ተተኳሪ ፊደሎች ያሉበትን ቃላት ሲጠሩ በማጨብጨብ ተተካሪ ፊደሉን እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡ እባክዎ መምህር ተማሪዎቹ ይህንኑ ለተወሰነ ጊዜ እየደጋገሙ እንዲለማመዱ ያትጓቸው፡፡ ተተኳሪ ድምፆች በቃል መነሻ፣ በቃል መሀከልና በቃል መድረሻ ላይ ሊመጡ እንደሚችሉ ግንዛቤ ለመፍጠር ድምፆቹ ያሉባቸውን ቃላት በቃል እያቀረቡ እንዲለማመዱ ይሁን፡፡ ለምሳሌ "ጠ" በቃል መነሻ "ጠመደ" በቃል መሃል "ገጠመ" በቃል መጨረሻ "ሰመጠ" እንደሚገኙ በሁሉም ተተኳሪ ድምጾች በቂ ምሳሌ በመስጠት ያለማምዱ፡፡ በተጨማሪም በየክፍለጊዜው የሚማሩትን ፊደላት ቅርጽ በባለቀለም ወረቀት ግድግዳ ላይ መለጠፍ፣ ፊደላትን ጎላ አድርጎ በሰንጠረዥ ማቅረብ፣ በካርቶን ላይ ፍላሽ ካርዶችን አዘጋጅቶ መጠቀም፣ ፍላሽ ካርዶችን ጠረጴዛ ላይ በታትኖ በማሰቀመጥ እንዲመርጡ ማድረግ፣ በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ

ከቀረቡት ቃላት በተጨማሪ ተማሪዎች ሌሎችን እንዲያፈልቁ ማበረታታት፣ ተማሪ ከሳጥን ውስጥ ተራ በተራ ፍላሽ ካርዱን እንደ እጣ በማውጣት፣ ያወጣውን ከፍ አድርጎ በማሳየት ሌሎች ተማሪዎች እንዲጠሩ በማድረግ ትምህርቱን ማቅረብ ይቻላል፡፡

መምህር ከመልመጃ አንድ እስከ አስራ አራት ያሉት በቃል ውስጥ ተለምዷዊ ቅጥያዎች ማስለየት ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ ይህን ሲተገብሩ አስቀድመው እርሶ በሞዴልነት ከቃላት ላይ ያሉትን ቅጥያዎች በመለየት ያመልክቷቸው፡፡ በመቀጠልም ይህንኑ ተግባር ከተማሪዎችዎ ጋር በህብረት ይስሩ፡፡በመጨረሻም ተማሪዎች በተናጥል እራሳቸውን ችለው እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡ በምሳሌው መሰረትም ተማሪዎች ተለምዷዊ ቅጥያዎችን ከለዩ በኋላ ቃሉን በትክክልና በፍጥነት እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡ ፡በቃል ውስጥ ያሉትን ተለምዷዊ ቅጥያዎችን ሲለዩ በቅጥያዎች ብዛትም ተማሪዎችን በማስጨብጨብ በቀላሉ እንዲለዩ ያድርጉ ፡፡ምሳሌ ፡- ፀጋሽ = ፀጋ-ሽ የሚለው ቃል አንድ ቅጥያ ስላለው አንድ ጊዜ በማስጨብጨብ ያሳይዋቸው የቀሩትን መልመጃዎች ተማሪዎቹም በመማሪያ መጽሀፉ ላይ ያሉትን ተግባራት እየሰሩ እንዲለማመዱ ይርዷቸው፡፡ ይህንንም ተግባር በመደጋገም ያሰሯቸው፡፡ እገዛ ለሚፈልጉ ተማሪዎች እገዛ በማድረግ ከቃላት ውስጥ ተለምዷዊ ቃላትን በትክክልና በተገቢው እንዲለዩ ይርዷቸው፡፡ መልመጃዎችንም በደብተራቸው ላይ ጽፈው እንዲለማመዱ ይዘዟቸው፡፡ የተማሪዎችን ተሰትፎ ለማሳደግ ያበረታቷቸው፡፡

መምህር ትምህርቱን ተጨባጭ ለማድረግ ተለምዷዊ ቅጥያዎችን ለየብቻ በፍላሽ ካርድ አዘጋጅተው በቀኝና በግራ እጅ ወደ ላይ ከፍ አድርገው በመያዝ ከቃላት ጋር እየለዩ ያመልክቷቸው፡፡ ተማሪዎችም ይህንኑ ተግባር ተራ በተራ እየለዩ እንዲያመለክቱ ይርዷቸው፡፡ ተለምዷዊ ቅጥያዎችን በአካባቢ በሚገኙ ቁሳቁሶች ሰርተው እንዲመጡ የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

# ትምህርት አራት፡ ቃላት

መምህር በቃላት ትምህርት ስር ተማሪዎችዎ የቃላትን ቀጥተኛ ፍቺ የሚለማመዱበት ነው፡፡ ቃላቱ በአረፍተ ነገርውስጥ ሳይገቡ የተለያዩ ፍቺ ሊይዙ እንደሚችሉ የተለያዩ ምሳሌዎችን በመስጠት ያስረዷቸው፡፡ ለምሳሌ “ወረደ” የሚለው ቃል ተሻረ፣ ሄደ፣ ቀነሰ የሚሉትን ፍቺ ሊይዝ እንደሚችል ያመልክቷቸው፡፡ አንድ ቃል ለምሳሌ “አረፈ”

*የሚለውን ቃል እንዴት ልዩ ልዩ ፍቺ እንደሚሰጥ ይጠይቋቸው በተጨማሪም መፅሐፉ ላይ በተሰጠው ምሳሌ መሰረት ለቃላት ፍቺ እየሰጡ ያለማምዷቸው፤ የተማሪዎችንም መልስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ያለማምዷቸው፡፡ በመቀጠል በመማሪያ መጽሀፋቸው ውስጥ በመልመጃ አስራ አምስት የተሰጡትን ቃላት በደብተራቸው ጽፈው ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡ መልሳቸውንም ጎን ካለው ጓደኛቸው ጋር በማስተያየት ለርሶ ያሳዩ ፡፡ እርሶም ከተማሪዎችዎ ሙከራ በኋላ መልሱን በሰሌዳ ላይ ይጻፉላቸው፡፡*

*መምህር የመልመጃ አስራ አምስት መልመጃ በሚከተለው መንገድ መልስ ይስጧቸው፡፡*

*ገረፈ- መታ /ዠለጠ/ ደበደበ…*

*መረጠ - ለየ/ ፈለገ/ ወደደ…*

*ሠመረ - ተሳካ/ መልክ ያዘ/ ተስማማ…*

*አረመ - አስተካከለ/*

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

# ትምህርት አራት፡ ጽህፈት

*መምህር በዚህ ትምህርት ስር ተማሪዎች ቀላል አረፍተነገሮችን እንዲገነቡ የሚደረግበት ክፍል ነው፡፡ ተማሪዎች ተራ ወይም ቀላል አረፍተነገሮችም ከመተግበራቸው በፊት በሶስቱ ሳጥን ውስጥ ከተዘረዘሩት ቃላት የተወሰኑ አረፍተነገሮችን እየሰሩ ያሳይዋቸው፡ አረፍተ ነገር ሲመሰርቱም አረፍተ ነገሩ ሙሉ ሀሳብ መያዝ እንዳለበት ያስገንዝቧቸው፡ በመቀጠል የተወሰኑ ጥያቄዎችን ከተማሪዎችዎ ጋር ሆነው ይስሩ፡፡ ልምምዱ በቂ ነው ሲሉ ተማሪዎች እራሳቸውን ችለው አረፍተነገር እንዲጽፉ ያድርጓቻው፤ ተማሪዎች መልመጃዎችን ሲሰሩ የሚያጋጥማቸውን ችግር በቅርብ በመከታተል እገዛ ያድርጉላቸው፡ ሁሉም ተማሪዎች ከሞከሩ በኋላ ተገቢውን መልስ ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ተማሪዎች በደብተራቸው ላይ እርማት እንዲወስዱ ያድርጓቸው፡፡ ተማሪዎች የሚሰጡትን መልስ ያድንቁላቸው፤ ስህተታቸውንም በብልህት እርማት ይስጧቸው፡፡ መምህር እያንዳንዱ ተማሪ አራት አራት አረፍተነገር መስራት እንዳለባቸው ይንገሯቸው፡፡*

# ምዕራፍ ሰባት

# ተረቶች

(18ክፍለጊዜ)

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምእራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ምንባቦችን በማዳመጥ ታሪኮችን ይተርካሉ፡፡
- በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ አዳዲስ ቃላትን ያነባሉ፡፡
- በቃላት ውስጥ ያሉ ድምጾችን በመነጠልና በማጣመር ያነባሉ(ተለይተው የተዘረዘሩ ድምጾች/ፊደላት)፡፡

## 2. ዝርዝር ይዘቶች

**ድምጻዊ ግንዛቤ**

- ከምዕራፍ ስድስት ቀጥሎ የሚመጡ ሶስትድምጾች/ፊደላት(ፊ፣ፐ፣ቨ)
- የተመረጡ ድምጾች/ፊደላት ማዛመድ
- ተዘውታሪ/የትምህርት ቃላት
- የቃላት እድገት
- የጽንሰ ሀሳብ ስያሜ
- ቃላትን መነጠልና ማጣመር

## 3. የመማር ማስተማር ብልሀቶችና መሳሪያዎች

መምህር ተማሪዎች በቡድን ተቀምጠው የሚያውቁትን ታሪክ እንዲለዋወጡ ይጠይቃል፡፡ ተማሪዎች እርስ በእርሳቸው የሚያውቁትን ታሪክ ይተርካሉ፡፡ መምህር የተመረጡ ታሪኮችን አቅርቦ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን መጠየቅ፡፡

**መለየት፡** መምህር ቃላትን በቃል ይጠራል፣ በቃሉ ውስጥ ያሉትን ድምጾች ይነጥላል፣ ያጣምራል፡፡ ተማሪዎችም መምህር የሚያሳየውን ድርጊት በመከተል በቃላቱ ውስጥ የሚገኙትን ድምጾች መጥራትእና ማጣመር፡፡ /የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣ የባለቀለም ወረቀት ፣ የካርቱን ስዕሎች ፣ የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ ወዘተ ተጠቀም)

መምህር በአንድ ጎን ቃላትን በቃላት ካርድ ላይ፣ በሌላ ጎን የታወቁ ቅጥያዎችን መጻፍ:: ከዚያም የሚገናኙትን ያዛምዳል፡፡

**መቁጠር፡** ተማሪዎች አዳዲስ ቃላት ከሚታወቁ ቅጥያዎች ጋር በምንባቡ ውስጥ ሲያገኙ ያጨበጭባል፡፡ (የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣ የባለቀለም ወረቀት፣ የካርቱን ስዕሎች፣ የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ ወዘተ መጠቀም)

**ተመሳሳይ ዜማ፡** ተማሪዎች በመድረሻ ላይ ተመሳሳይ ቀለሞች ያሏቸውን ቤተሰባዊ ቃላት መጥራት፡፡ ከዚያም መምህርምላሹን በ ሰሌዳ ላይ ይጽፋል፡፡

**መነጠልና ማጣመር፡** መምህር የታወቁ ቅጥያዎችን በቃላት ላይ ማጣመርና መነጠልን ያሳያል፡፡ ተማሪዎች የታወቁ ቅጥያዎችን ከቃላት ላይ መነጠልና ማጣመርን መለማመድ፡፡

**ቃላትን መመስረት ፡** ተማሪዎች የቃላት ክፍሎችን በመጻፍ አዳዲስ ቃላትን መመስረት መለማመድ፡፡

**ተዘውታሪ ቃላት፡** መምህር የግድግዳ ላይ ቃላትን ከፍቺዎቻቸው ጋር ማዘጋጀት፡፡ ከዚያም ለቃላቱ ትርጉማቸውን መስጠት፡፡

**ቀስበቀስ ማብቃት ፡** ሀ.መምህር ፊደላትን በማሳየት መጥራት፡፡

ለ.መምህር ፊደላትን እያሳየ ተማሪዎችን ፊደላቱን እንዲጠሩ መጠየቅ፡፡

ሐ.ተማሪዎች ፊደላትን ድምጾችን ማዛመድን መልመድ፡፡

**እንቅስቃሴ፡** ድምጾችን ከእንቅስቃሴ ጋር ያገናኛል፡፡ ይህ ተማሪዎች አካላቸውን በማንቀሳቀስ ድምጾችንና ፊደላትን እንዲያስታውሱ ማገዝ፡፡

**አፋዊ እንቅስቃሴዎች፡** ተማሪዎች በአንደበት አካላት ውስጥ ድምጾች እንዴት እንደሚፈጠሩ መማር፡፡

**መጻፍ፡** ሀ. መምህር በቃላት ውስጥ ያሉትን ድምጾች በመነጠል ይጠራል፡፡ (የታወቁ የፊደል ድምጾችን መጠቀም)

**አርአያ፡** መምህር ተማሪዎች ከኋቸው የማንበብ ችሎታ በላይ የሚነበቡ ምንባቦችን በከፍተኛ ድምጽ ማንበብ፡፡

**ተደጋጋሚ የቃል ንባብ፡** ይህ ተማሪዎች ትክክለኛነትን እንዲያዳብሩ እድል መስጠት፡፡

**ቀስበቀስ ማብቃት፡** ጣትን በመጠቆም በገደል ማሚቶ፣ የጋራ ንባብ፣ ከጓደኛ ጋር ማንበብ ፣ ሌላውን ተከትሎ ማንበብ፡፡

ድምጾችን /ፊደላትን መቅረጽ

በተደጋጋሚ የሚከሰቱ ፊደላትን መጻፍ

**መጻፍ፡** መምህር ቀላል አረፍተ ነገሮችን ይጽፋል፡፡ በመቀጠል መምህሩን በመከተል በትክክል ቀላል አረፍተ ነገሮችን ይጽፋሉ፡፡

## 4. ምዘና

- በተደጋጋሚ የሚከሰቱ ፊደላትን መጻፍ
- በቃልና በጽሁፍ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- አካላዊ ምላሽ
- የተማሪዎች በግል ለጥያቄዎች የሚመልሱት አካላዊ ምላሽ
- ኢመደበኛ ቁጥጥር
- ምልከታ
- በስዕል መወከል
- ተራ በተራ ማቅረብ
- ስልታዊ ልምምድ
- መውጫ ካርድ

**ክፍለጊዜ፡ አንድ**

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### ቅድመ ማዳመጥ

መምህር በዚህ ትምህርት ርዕስ "ተረቶች"ን ተማሪዎች እያዳመጡ የተረቱን መልዕክት፣ የአተራራክ ስልትን እየተማሩ የማዳመጥ ክሂላቸውን የሚያበለጽጉበት ክፍል ነው፡፡ የሚደመጠውን ታሪክ በንቃት እንዲከታተሉና ለማዳመጥ እንዲዘጋጁ ያድርጓቸው፡፡ ተማሪዎች በመጽሀፉ ላይ ያሉትን ስዕሎች አይተው ስለምን እንደሚያዳምጡ እንዲገምቱ መጠየቅ፣ ግምታቸውን ማጠናከር ወይም መለወጥ እንደሚችሉ ይንገሯቸው፡፡ የተረቱንም ርዕስ ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ተማሪዎችዎ እንዲገምቱ ያድርጓቸው፡፡ በመቀጠል ወደ ንባብ ተግባር ከመግባቶ በፊት የተማሪዎቹን የቀደመ እውቀት መቀስቀስ እንደሚያስፈልግ

አይዘንጉ፡፡ ለዚህም የሚከተሉትንና የመሳሰሉትን ቅድመ ማዳመጥ ቀስቃሽ ጥያቄዎች ይጠይቁ፡፡

1. ተረት አዳምጣችሁ ተቃላችሁ?
2. ታሪኩ ስለምን ነበር?
3. የአዳመጣችሁትን ተረት ርዕስ ተናገሩ፡፡

> *መምህር የሚደመጠውን ታሪክ በዝግታ ሁለቴ ደጋግመው ያንብቡላቸው፡፡ በጽሁፉ ውስጥ ከቀረቡት ቃላት ውስጥ አዳዲስና ከባድ ቃላትና ሀረጋት ይሆናሉ ብለው ያሰቧቸውን በቅድሚያ ፍቺ ይስጧቸው፡፡ በምንባቡም መሃል ንባቦትን ገታ አድርገው የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎችን ያቅርቡላቸው፡፡*

ዛሬ የምታዳምጡት ተረት ስለ "ገበሬና ነብር" ይሆናል፡፡

## "ገበሬና ነብር"

በአንድ መንደር ውስጥ የሚኖር አንድ ገበሬ ነበር፡፡ አንድ ቀን ሲያርስ ነብር መጣበት:: ነብሩንም አዳኞች ያባርሩት ነበር፡፡ ነብሩም "እባክህን አንተ ገበሬ ደብቀህ አድነኝ" አለው፡፡ገበሬውም "እሺ" ብሎ ዘር ያመጣበት ስልቻ ውስጥ ደበቀው፡፡ አዳኞቹም ገበሬ አጠገብ ደረሱና "አንድ ነብር በዚህ ሲያልፍ አይተሃል? "ብለው ጠየቁት፡፡ ገበሬውም "እኔ አላያሁም" ብሎ መለሰላቸውና አዳኞቹ ነብሩን ፍለጋ ወደ ጫካ ሄዱ፡፡

**(የማዳመጥ ጊዜ)** ገበሬው ነብሩን ምን ያደርገው ይሆን?

ገበሬውም ሰዎቹ ርቀው ስለሄዱ ነብሩን "ከስልቻ ውጣና ሂድ" አለው፡፡ ነብሩ ግን "በጣም ርቦኛል የሚበላ ካላገኘው አልሄድም" አለው፡፡ ገበሬውም "ምግብ አላያዝኩም ምን ትበላ? "አለው፡፡ ነብሩም "አንተን እበላለሁ" አለው፡፡ ገበሬውም "ይህንን ካልክ ጓደኞችህ ይፍረዱ" አለው፡፡ በዚህም ተስማምተው ፍርድ ጥየቃ ሄዱ፡፡ ዝንጀሮ፣ ፍየል፣ ውሻን ጅብ በገበሬው ፍረዱበት፡፡ ጦጣ ግን "እንዴት እንዳዳንከው አሳየኝ" ብላ ጠየቀችው፡፡ ገበሬውም ነብሩን ስልቻ ውስጥ አስግብቶ አሰረውና አሳያት፡፡ ጦጣም ደብድቦ እንዲገድለው ለገበሬው በምልክት ነገረችው፡፡

### ድህረ ማዳመጥ

ማዳመጣቸውን የሚፈትሹ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡ (ጥያቄዎችን በተናጠልና በተራ በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ)

1. ዝንጀሮ፣ ፍየል፣ ውሻና ጅብ ምን ብለው ፈረዱ?
2. ጦጣስ ለማን ፈረደች?
3. ከዚህ ትረካ ምን ተረዳችሁ?
4. እናንተ ብትሆኑ ምን ትፈርዳላችሁ?

## ክፍለጊዜ፡ ሁለት

### ቅድመ ማዳመጥ

መምህር ዛሬ ተማሪዎች የሚያዳምጡት ተረት ርዕስ “የራበው ውሻ” የሚል ነው፡፡ ተማሪዎች በክፍለጊዜ አንድ ላይ ተረትን እንዴት ማዳመጥ እንዳለባቸው የነገሯቸውን ተግባራት እንዳይዘነጉ መልሰው አስታውሷቸው፡፡ የሚደመጠውን ታሪክ በንቃት እንዲከታተሉና ለማዳመጥ እንዲዘጋጁ ያድርጓቸው፡፡ ተማሪዎች በመጽሀፉ ላይ ያሉትን ስዕሎች አይተው ስለምን እንደሚያዳምጡ እንዲገምቱ መጠየቅ፣ ግምታቸውን ማጠናከር ወይም መለወጥ እንደሚችሉ ይንገሯቸው፡፡ የተረቱንም ርዕስ ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ተማሪዎቹ እንዲገምቱ ያድርጓቸው፡፡ በመቀጠል ወደ ንባብ ተግባር ከመግባቶ በፊት የተማሪዎቹን የቀደመ እውቀት መቀስቀስ እንደሚያስፈልግ አይዘንጉ፡፡ ለዚህም የሚከተሉትንና የመሳሰሉትን ቅድመ ማዳመጥ ቀስቃሽ ጥያቄዎች ይጠይቁ፡፡

1. ውሻን የተመለከተ ተረት አዳምጣችሁ ታቃላችሁ?
2. የራበው ውሻ ምን ይመስላል?

| |
|---|
| መምህር የሚደመጠውን ታሪክ በዝግታ ሁለቴ ደጋግመው ያንብቡላቸው፡፡ በጽሁፉ ውስጥ ከቀረቡት ቃላት ውስጥ አዳዲስና ከባድ ቃላትና ሀረጋት ይሆናሉ ብለው ያሰቧቸውን በቅድሚያ ፍቺ ይስጧቸው፡፡ በምንባቡም መሃል ንባቦትን ገታ አድርገው የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎችን ያቅርቡላቸው፡፡ |

### “የራበው ውሻ”

ከለታት አንድ ቀን አንድ በጣም የራበው ውሻ ነበር፡፡ የሚበላ ነገር ለመፈለግ ወደ አንድ መንገድ ሄደ፡፡ እዚያ ሰዎች በሬ አርደው ስጋ ሲከፋፈሉ አየና አጠገባቸው ቆመ፡፡ ከሰዎቹ መካከል አንዱ ለውሻው አዝኖለት የበሬውን ሳንባ ወረወረለት፡፡ ውሻው ሳንባውን ባፉ ይዞ ወደ ጫካ ሮጠ፡፡

**(የማዳመጥ ጊዜ)** ውሻው ሳንባውን ይዞ ወደ ጫካ ሲገባ ምን ያጋጥመው ይሆን?

ውሻው ጫካ ውስጥ ሲገባ ኩሬ አይቶ ቆመ፡፡ ወደ ውሃው ሲመለከትየራሱን መልክ ከውሃው ውስጥ አየ፡፡ከዚህ በኋላ ውሻው ሌላ ውሻ ስጋ ይዞ የቀመ መሰለው፡፡ ስለዚህ ስጋውን ለመቀማት ፈለገና ለመጮህ አፉን ሲከፍት ያዘው ሳንባ አምልጦት ከውሃ ውስጥ ወደቀበት፡፡በዚህ ምክንያት ምንም ሳይበላ ወደ ቤቱ ተመለሰ፡፡

### (ድህረ ማዳመጥ)

**መምህር**

ማዳመጣቸውን የሚፈትሹ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡ ጥያቄዎችን በተናጥልና በተራ በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡

1. ውሻው ምንም ሳይበላ ለምን ተመለሰ?
2. ውሻው ሌላ ውሻ ስጋ ይዞ እንዴት የቆመ መሰለው?
3. ውሻው የያዘው ሳንባ እንዴት አምልጦት ውሃ ውስጥ ገባ?

### ክፍለጊዜ፡ ሶስት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

መምህር በዚህ ክፍል ውስጥ ተማሪዎች ካዳመጧቸው ሁለት ተረቶች ውስጥ እንደየ ፍላጎታቸው ለክፍል ጓደኞቻቸው በየተራ መልሰው ተረቱን እንዲተርቱ የሚያደርጉበት የትምህርት ክፍል ነው፡፡ ተማሪዎችም በየተራ እጃቸውን በማውጣት እርሶ በሚሰጧቸው ቅደም ተከተል መሰረት ለሴት ተማሪዎች የተለየ ትኩረት በመስጠት ተረቱን እንዲተርኩ ያድርጓቸው፡፡ ተማሪዎችዎ ተረቱን ደግመው ሲተርኩ የተረቱን ቅደም ተከተልና ዋና ሀሳብ በትረካቸው ውስጥ በትክክል እንደተጠቀሙ ኢመደበኛ በሆነ መንገድ እየገመገሙ በብልሀት ምጋቤ ምላሽ ይስጧቸው፡፡ እያንዳንዱ ተማሪ ተናግሮ ከጨረሰ በኋላ የክፍል ተማሪዎችዎ እንዲያጨበጭቡ በማድረግ ማበረታታቶትን አይዘንጉ፡፡ በክፍለጊዜ አራት እያንዳንዱ ተማሪ ከቤተሰቡ፣ ከጓደኞቻቸው ወይም ከመጽሀፍ ያገኙትን ተረት ይዘው እንዲመጡ ያሳስቧቸው፡፡

### ክፍለጊዜ፡ አራት

መምህር በክፍለጊዜ ሶስት ተማሪዎች ባደረጉት ተግባር መሰረት ያዳመጡትን ተረት መልሰው በመተረክ ልምምድ አግኝተዋል፡፡ በክፍለጊዜ አራት ትምህርታቸው ደግሞ ከቤተሰቦቻቸው፣ ከጓደኞቻችው፣ ወይም ከመጽሀፍ ያገኙትን ተረት ለክፍል ተማሪዎች

በማቅረብ የንግግር ክሂላቸውን የሚያዳብሩበት ነው፡፡ ስለዚህም ተማሪዎች በየተራ እጅ በማውጣት ለክፍል ተማሪዎች እንዲተርቱ ያድርጉ፡፡ ተማሪዎችም ተረቱን ተርከው ሲያበቁ ተማሪዎች እንዲያጨበጭቡላቸው ያድርጉ፡፡ እርሶም ያበረታቷቸው፡፡

## ክፍለጊዜ፡ አምስት እስከ አስራ አንድ

# ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

መምህር ከክፍለጊዜ 5-11 ድረስ የቀረቡ ተተኳሪ ፊደላትን (ፈ፣ ፐ፣ ቨ እና ዘሮቻቸው) ድምጽና ቅርጽ አዋህዶ ለማስለየት በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡትን የፊደላት ቅርጽና ምስል ድምጽንም በመጨመር እንዲያዛምዱ ይርዷቸው፡፡ ይህንን ሲተገብሩ በቅድሚያ እርሶ ይስሩ፤ በመቀጠልም ከተማሪዎችዎ ጋር አብረው ይስሩ፤ በመጨረሻም ተማሪዎችዎ እራሳቸውን ችለው በተናጠል እንዲሰሩ ይርዷቸው፡፡ ተማሪዎች የሚያውቋቸው በተተኳሪ ድምጾች የተመሰረቱ ቃላት እንዲጠሩልዎት ያድርጉና የተወሰኑትን ይምረጡላቸው፡፡ ከዚያም የተመረጡትን ቃላት በጋራና በተናጠል ያለማምዷቸው፡፡ ተማሪዎች ተተኳሪ ፊደሎች ያሉበትን ቃላት ሲጠሩ በማጨብጨብ ተተኳሪ ፊደሉን እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡ እባክዎ መምህር ተማሪዎቹ ይህንኑ ለተወሰነ ጊዜ እየደጋገሙ እንዲለማመዱ ያትጓቸው፡፡ ተተኳሪ ድምፆች በቃል መነሻ፣ በቃል መሀከልና በቃል መድረሻ ላይ ሊመጡ እንደሚችሉ ግንዛቤ ለመፍጠር ድምፆቹ ያሉባቸውን ቃላት በቃል እያቀረቡ እንዲለማመዱ ይሁን፡፡ ለምሳሌ “ፈ” በቃል መነሻ “ፈረስ” በቃል መሃል “ሰፈረ” በቃል መጨረሻ “ሰነፈ” እንደሚገኙ በሁለም ተተኳሪ ድምጾች በቂ ምሳሌ በመስጠት ያለማምዱ፡፡ለ”ፐ” እና “ቨ” ልዩ ትኩረት በማድረግ ተማሪዎችዎ በትክክል ድምጹን እንዲጠሩ ፣ ምልክቶቹን እንዲለዩ ለማድረግ ደጋግመው ልምምድ ይስጧቸው፡፡ በተጨማሪም በየክፍለጊዜው የሚማሩትን ፊደላት ቅርጽ በባለቀለም ወረቀት ግድግዳ ላይ መለጠፍ ፣ ፊደላትን ጎላ አድርጎ በሰንጠረዥ ማቅረብ፣ በካርቶን ላይ ፍላሽ ካርዶችን አዘጋጅቶ መጠቀም ፣ፍላሽ ካርዶችን ጠረጴዛ ላይ በታትኖ በማሰቀመጥ እንዲመርጡ ማድረግ፣ በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ከቀረቡት ቃላት በተጨማሪ ተማሪዎች ሌሎችን እንዲያፈልቁ ማበረታታት፣ ተማሪ ከሳጥን ውስጥ ተራ በተራ ፍላሽ ካርዱን እንደ እጣ በማውጣት፣ ያወጣውን ከፍ አድርጎ በማሳየት ሌሎች ተማሪዎች እንዲጠሩ በማድረግ ትምህርቱን ማቅረብ ይቻላል፡፡

መምህር ከመልመጃ አንድ እስከ አራት ያሉት በቃል ውስጥ ያሉትን ድምጾች ወይም ፊደሎች በመነጠልና በማጣመር የተተኳሪ ድምጾች ድምጻቸውን፣ ምልክታቸውን የሚለዩበት ነው፡፤ በዚህ መሰረት በቅድሚያ በቃል ውስጥ ያሉትን ድምጾች እየለዩ በሞዴልነት ያሳይዋቸው፡፡ በመቀጠል ከተማሪዎችዎ ጋር በመሆን በቃላት ውስጥ ያሉትን ድምጾች እየነጠሉና እያጣመሩ በመደጋገም በህብረት ይስሩ፡፡ በቃላት ውስጥ ያሉትን ድምጾች ሲነጥሉ በፊደሎቹ መጠን ተማሪዎች እንዲያጨበጭቡ ያድርጓቸው፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪዎች በቃል ውስጥ ስንት ፊደሎች እንዳሉ በቀላሉ በዜማ መልክ እንዲማሩ ይረዳቸዋል፡፡ ለምሳሌ "ፈረስ" በሚለው ቃል ውስጥ ሶስት ፊደሎች ስላሉ ተማሪዎች ሶስቴ እንዲያጨበጭቡ ያድርጓቸው፡፡ ከዚህ ልምምድ በኋላ ተማሪዎችዎ እራሳቸውን ችለው በግል እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡ የቀሩትን መልመጃዎች ተማሪዎቹም በመማሪያ መጽሀፉ ላይ ያሉትን ተግባራት እየሰሩ እንዲለማመዱ ይርዷቸው፡፡ የእርሶም እገዛና ክትትል እንዳይለያቸው፡፡

መምህር ከመልመጃ አምስት እስከ ሰባት ያሉት በቃል ውስጥ ተለምዷዊ ቅጥያዎች ማስለየት ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ ይህን ሲተገብሩ አስቀድመው እርሶ በሞዴልነት ከቃላት ላይ ያሉትን ቅጥያዎች በመለየት ያመልክቷቸው፡፡ በመቀጠልም ይህንኑ ተግባር ከተማሪዎችዎ ጋር በህብረት ይስሩ፡፡በመጨረሻም ተማሪዎች በተናጥል እራሳቸውን ችለው እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡ በምሳሌው መሰረትም ተማሪዎች ተለምዷዊ ቅጥያዎችን ከለዩ በኋላ ቃሉን በትክክልና በፍጥነት እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡በቃል ውስጥ ያሉትን ተለምዷዊ ቅጥያዎችን ሲለዩ በቅጥያዎች ብዛትም ተማሪዎችን በማስጨብጨብ በቀላሉ እንዲለዩ ያድርጉ ፡፡ምሳሌ ፡- ፀጋሽ = ፀጋ-ሽ የሚለው ቃል አንድ ቅጥያ ስላለው አንድ ጊዜ በማስጨብጨብ ያሳይዋቸው የቀሩትን መልመጃዎች ተማሪዎቹም በመማሪያ መጽሀፉ ላይ ያሉትን ተግባራት እየሰሩ እንዲለማመዱ ይርዷቸው፡፡ ይህንንም ተግባር በመደጋገም ያሰሯቸው፡፡እገዛ ለሚፈልጉ ተማሪዎች እገዛ በማድረግ ከቃላት ስውጥ ተለምዷዊ ቃላትን በትክክልና በተገቢው እንዲለዩ ይርዷቸው፡፡ መልመጃዎችንም በደብተራቸው ላይ ጽፈው እንዲለማመዱ ይዟቸው፡፡ የተማሪዎችን ተሰትፎ ለማሳደግ ያበረታቷቸው፡፡

መምህር ትምህርቱን ተጨባጭ ለማድረግ ተለምዷዊ ቅጥያዎችን ለየብቻ በፍላሽ ካርድ አዘጋጅተው በቀኝና በግራ እጆ ወደ ላይ ከፍ አድርገው በመያዝ ከቃላት ጋር እየለዩ ያመልክቷቸው፡፡ ተማሪዎችም ይህንኑ ተግባር ተራ በተራ እየለዩ እንዲያመለክቱ

ይርዷቸው፡፡ ተለምዷዊ ቅጥያዎችን በአካባቢ በሚገኙ ቁሳቁሶች ሰርተው እንዲመጡ የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

# ትምህርት አራት፡ ቃላት

መምህር በዚህ ክፍል ውስጥ ተማሪዎች የትምህርት እና የተዘውታሪ ቃላት ችሎታቸውን የሚዳብሩበት ነው፡፡ የቃላት ችሎታቸውን ለማደበር በመልመጃ ስምንት የተሰጡትን ቃላት ከፍቻቸው እያዛመዱ የቃላት ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ያለማምዷቸው፡፡ ስለዚህም በምሳሌው መሰረት መምህሩ ለቃላት ፍቺ እየሰጡ ያሳይዋቸው፡፡ በመቀጠልም ከተማሪዎችዎ ጋር በህብረት በመስራት በቂ ልምምድ ከሰጧቸው በኋላ እራሳቸውን ችለው በመማሪ መጽሀፋቸው ውስጥ በመልመጃ ስምንት ያሉትን ጥያቄዎች በተናጥል ያሰሯቸው፡፡ በመጨረሻም የመልመጃውን መልስ በሰሌዳ ላይ በመጻፍ ተማሪዎችዎ እርማት እንዲውስዱ ያድርጓቸው፡፡

**መልመጃ ፡ስምንት**

**ቃላትን ከፍቻው ጋር አዛምዱ፡፡**

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| አየ | አዳመጠ |
| ሰማ | ተመለከተ |
| ረዳ | መኖሪያ |
| ቤት | አገዘ |

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሶስት**

መምህር በክፍለጊዜ አስራ ሶስት በቃላት ትምህርት ስር ተማሪዎች ቃላትን ከፍቺያቸው ጋር እያዛመዱ የቃላት ችሎታቸውን እንዳዳበሩ ይታመናል፡፡ ይህንኑ የቃላት ትምህርት ለማጠንከር በመልመጃ ዘጠኝ ስር ለተዘረዘሩት ቃላት ተማሪዎች ፍቺ እየሰጡ እንዲለማመዱና የቃላት እውቀታቸው እንዲዳብር ያትጓቸው፡፡ ይህንን ለመተግበር በቅድሚያ በሞዴልነት በምሳሌው መሰረት ለቃላት ፍቺ እየሰጡ ያለማምዷቸው፡፡ በመቀጠልም ከተማሪዎች ጋር በህብረት ለተለያዩ ቃላት ፍቺ በመስጠት ያለማምዷቸው በመጨረሻም ተማሪዎች እራሳቸውን ችለው ለቃላቱ ፍቺ እንዲሰጡ መማሪያ መጽሀፍ

ውስጥ በመልመጃ ዘጠኝ ላይ የቀረቡትን ቃላት ያሰሯቸው፡፡ የተማሪዎችዎንም ጥረት እያደነቁ እገዛ ለሚፈልጉ ተማሪዎች እገዛ ያድርጉላቸው፡፡ ቃላቱም የተለያዩ ፍቺ ሊይዙ እንደሚችሉ በምሳሌ ያመልክቷቸው፡፡ ለቃላቱ ፍቺ ናቸው የሚሏቸውን የቃላት ፍቺ ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ተማሪዎች እርማት እንዲወስዱ ድርጓቸው፡፡

**መልመጃ፡ ዘጠኝ**

**ለሚከተሉት ቃላት ፍቺ ስጡ፡፡**

ምሳሌ፡ ተረከ   አወራ/ተናገረ/ዘረዘረ

መራ = ቀደመ፣ አመለከተ፣ አሳየ…

በለጠ = ተሸለ፣ ቀደመ፣ አሸነፈ

ተማረ = አወቀ፣ ሰለጠነ፣ ተለማመደ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት**

መምህር በዚህ ክፍለጊዜ ውስጥ ተማሪዎች ከቃሉ ላይ የተጎረዱትን ፊደላት እያሟሉ ቃሉ ፍቺ እንዲሰጥ የሚያደርጉበት ነው፡፡ ይህ ልምምድ ተማሪዎች ቃላት ፍቺ እንዲሰጡ በስርዓተ ፊደላት ተሟልተው መቅረብ እንዳለባቸው የሚማሩበት ነው፡፡ ስለዚህ መልመጃውን በምሳሌ መሰረት በሞዴልነት እየሰሩ ያሳይዋቸው፡፡ በመቀጠል ከተማሪዎችዎ ጋር በህብረት እየሰሩ ያለማምዷቸው፡፡ ልምምዱ በቂ ነው ሲሉ እያንዳንዱ ተማሪ በግል ፊደላትን እያሞሉ ቃላት ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡ በልምምድ ወቅትም እገዛ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች እገዛ ይስጧቸው፡፡ ተማሪዎችም በመማሪያ መጽሀፋቸው ውስጥ ያለውን መልመጃ አስርን እንዲሰሩ ይዘዟቸው፡፡ ትክክለኛውን መልስ በሰሌዳ ላይ በማድረግ ተማሪዎች እርማት እንዲወስዱ ያድርጓቸው::

**መልመጃ አስር፡ የጎደሉትን ፊደሎች አሟሉ**

ፍ__ር = ፍቅር /ፍርድ /

ፓፓ__ =ፓፓያ

ቬ__= ቬሎ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት**

# ትምህርት አምስት፡ ጽሕፈት

መምህር ይህ የትምህርት ክፍል ጽህፈት ላይ ተተኳሪ ያደረገ ነው፡፡ ተማሪዎች የተለያዩ ፊደላት ቅርጽን እንዲለዩና በትክክል እንዲጽፉ የሚለማመዱበት ነው፡፡ ስለዚህ

በቅድሚያ በሞዴልነት እርሶ በቃል ውስጥ ያሉትን ፊደሎች እየነጣጠሉ ፊደሎችን በትክክል እየቀረጹ ያሳይዋቸው፡፡ በመቀጠል ከክፍሉ ተማሪዎች ጋር በመሆን በህብረት በቃል ውስጥ ያሉትን ፊደላት እየነጣጠሉ በትክክል እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡ በድግግም ከተለማመዱ በኋላ ተማሪዎችዎ በየግላቸው እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡ በተማሪ መጽሀፍ በመልመጃ አስራ አንድ ላይ ያለውን መልመጃ ተማሪዎች በደብተራቸው ጽፈው እንዲለማመዱ ይዘዟቸው፡፡ በክፍል ውስጥ ዞር ዞር በማለት እገዛ ለሚሹ ተማሪዎች እገዛ ያድርጉላቸው፡፡ ትክክለኛውንም መልስ ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ተማሪዎች እርማት እንዲወስዱ ያድርጓቸው፡፡

## መልመጃ፡ አስራ አንድ

**በቃላት ውስጥ ያሉትን ፊደሎች ነጥላችሁ ጻፉ፡፡**

ምሰሌ፡ ፍየል= ፍ የ ል

ፓፓያ= ፓ ፓ ያ

ፖስታ= ፓ ስ ታ

ፍራፍሬ= ፍ ራ ፍ ሬ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት**

መምህር ይህ የትምህርት ክፍል ጽህፈት ላይ ተተኳሪ ያደረገ ነው፡፡ ተማሪዎች የተለያዩ ፊደላት ቅርጽን እንዲለዩና በትክክል እንዲጽፉ የሚለማመዱበት ነው፡፡ ስለዚህ በቅድሚያ በሞዴልነት መምህር በቃል ውስጥ ተነጣጥለው ያሉትን ፊደሎች እያጣመሩ ፊደሎችን በትክክል እየቀረጹ ያሳይዋቸው፡፡ በመቀጠል ከክፍሉ ተማሪዎች ጋር በመሆን በህብረት በቃል ውስጥ ተነጣጥለው ያሉትን ፊደላት እያጣመሩ በትክክል እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡ በድግግም ከተለማመዱ በኋላ ተማሪዎችዎ በየግላቸው እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡ በተማሪ መጽሀፍ በመልመጃ አስራ ሁለት ላይ ያለውን መልመጃ ተማሪዎች በደብተራቸው ጽፈው እንዲለማመዱ ይዘዟቸው፡፡ በክፍል ውስጥ ዞር ዞር በማለት እገዛ ለሚሹ ተማሪዎች እገዛ ያድርጉላቸው፡፡ ትክክለኛውንም መልስ ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ተማሪዎች እርማት እንዲወስዱ ያድርጓቸው፡፡

**መልመጃ ፡ አስራ ሁለት**

**በቃላት ውስጥ ያሉትን ፊደሎች አጣምራችሁ ጻፉ፡፡**

ቬ ሎ= ቬሎ

ፈ ለ ቀ= ፈለቀ

ፖ ሊ ስ=ፖሊስ

ፌ ን ጣ=ፌንጣ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

መምህር በዚህ ክፍለጊዜ ውስጥ ተማሪዎች የቃላት እውቀታቸውን ለማሳደግ እንዲረዳቸው ተለማዷዊ ቅጥያዎችን ከቃላት ላይ እየለዩ የሚለማመዱበት ነው፡፡ ስለዚህ ተለምዷዊ ቅጥዎችን ከቃል እየለዩ እንዲለማመዱ በቅድሚያ በምሳሌው መሰረት በሞዴልነት ያሳይዋቸው፡፡ በመቀጠልም ከተማሪዎችዎ ጋር በህብረት በመሆን ያለማምዷቸው፡፡ በመጨረሻም በተማሪ መጽሀፍ ላይ በመልመጃ አስራ አንድ ላይ ያሉትን ጥያቄች ተማሪዎች ደብተራቸው ላይ እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡ የተማሪዎችዎን ሙከራ እያደነቁላቸው እገዛ ለሚፈልጉ ተማሪዎች እገዛ በማድረግ ያለማምዷቸው፡፡ ትክክለኛውንም መልስ ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ተማሪዎች እርማት እንዲወስዱ ያድርጓቸው፡፡

1. ገባች = ገባ-ች
2. ቤትህ= ቤት-ህ
3. ቦርሳሽ = ቦርሳ-ሽ
4. መጽሀፍዋ = መጽሀፍ-ዋ
5. መኪናዎች = መኪና-ዎች

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

መምህር በክፍለጊዜ አስራ ሰባት ላይ ተማሪዎች ከቃላት ላይ ቅጥያዎችን እየነጠሉ ተለማምደዋል፡፡ በዚህ ክፍለጊዜ (በክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት) ደግሞ በቃላት ላይ ተማሪዎች የተለያዩ ፍቺ የሚሰጡ ቅጥያዎችን የሚቀጥሉበት መልመጃ ነው፡፡ ይህንን መልመጃ ለመስራት በቅድሚያ በሞዴልነት እርሶ ሰርተው ያሳዩአቸው፡፡ በመቀጠልም መምህር ከተማሪዎች ጋር በህብረት በመሆን በቃላት ላይ የተለያዩ ተለማዷዊ ቅጥያዎችን አየሰሩ ያለማምዷቸው፡፡ ከበቂ ልምምድ በኋላ ተማሪዎችዎ በየግላቸው በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ በመልመጃ አስራ  አራት ላይ ላሉት ቃላት ቅጥያ እንዲያደርጉ እና በደብተራቸው ላይ እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡ በክፍል ውስጥ እየተዘዋወሩ

የተማሪዎችን ሙከራ ያድንቁላቸው፡፡ በመጨረሻም ትክክለኛውን መልስ በሰሌዳ ላይ በመጻፍ ተማሪዎችዎ እርማት እንዲወስዱ ያድርጓቸው፡፡

**መልመጃ፡ አስራ አራት**

1. ሰው= ሰውዬ/ሰዎች/ሰውን …
2. እርሳስ = እርሳሶች/እርሳስህ/እርሳስሽ/…
3. ተረት= ተረቶች/ተረትክ/ተረትዋ…
4. ብዕር= ብዕሮች/ብዕርክ/ብዕርሽ…
5. ተማሪ =ተማሪዎች/ተማሪክ/ተማሪዋ…

# ምዕራፍ ስምንት

# ምግብ

(18ክፍለ ጊዜ)

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ምንባቡን በማዳመጥ የምግብ አይነቶችን ይዘረዝራሉ፡፡
- አዳዲስ ፊደላትን/ድምጾችን ያነባሉ፡፡
- ድምጾችን ከቃላት ውስጥ በመነጠልና በማጣመር ያነባሉ፡፡
- ተዘውታሪ ቃላትን ያነባሉ፡፡

## 2. ዝርዝር ይዘቶች

- ምንባብን አዳምጦ ዝርዝር ሀሳቦችን መናገር
- ከምዕራፍ ሰባት በኋላ የሚመጡ የተመረጡ ሞክሼ ድምጾች/ፊደሎች(ሀ፣ ሐ፣ ኀ፣ ኸ) መለየት
- ተዘውታሪ ቃላት(የትምህርት)
- በትክክል፣ በፍጥነት፣ በጥሩ አገላለጽና በመረዳት ማንበብ
- **በትክክል የፊደላትን ድምጸት መጻፍ**

## 3.የመማር ማስተማር ብልሀቶችና መሳሪያዎች

መምህር በቤታቸው ውስጥ ስለሚገኙ ምግቦች ቃላዊ ጥያቄዎችን ማቅረብ፡፡ ከዚያም መምህር ምባቡን በቃል ያነባል፡፡ መምህር ቢጋር ሰንጠረዥን በአዕምሮ ይስላል፡፡

ተማሪዎች የምንባቡን ዋና መልእክትና ተዘውታሪ ቃላትን የተዘጋጀውን ቢጋር ሰንጠረዥ በመመልከት ይገልጻሉ፡፡ (ለምሳሌ ስም፣ አይነት፣ ጥቅም፣ አዘገጃጀት)

መለየት መምህር በተለዩ ድምጾች የሚጀምሩ/የሚጨርሱ ቃላትን መጻፍ፡፡ ተማሪዎች በቃላት ውስጥ ያሉትን ድምጾች ለመለየት በመነጠልና በማጣመር መጥራት፡፡ (የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣ የባለቀለም ወረቀት፣ የካርቱን ስዕሎች ፣ የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ ወዘተ ተጠቀም)

**መቁጠር፡** ተማሪዎች በቃላት ውስጥ ባሉ ቅጥያዎች ብዛት መጠን በመለየት ማጨብጨብ፡፡

**ተመሳሳይ ድምጽ፡** ተማሪዎች ተመሳሳይ ቀለም ያላቸውን ቃላት ይፈጥራሉ፤ መምህሩም በሰሌዳ ላይ ምላሽ ይሰጣል፡፡ (የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣ የባለቀለም ወረቀት፣ የካርቱን ስዕሎች ፣ የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ ወዘተ መጠቀም)

**መነጠልና ማጣመር፡** ተማሪዎች በቃል ውስጥ የተለዩ ድምጾችን ለይተው በፍጥነት ይጠሯቸዋል፡፡ (መምህር ደግሞ ማጣመርን ለማሳየት ፊደላትን ያቀናጃል)ተማሪዎች በቃላት ውስጥ ያሉትን ቀለማት ወይም ድምጾች መጥራት፡፡

**ቀስበቀስ ማብቃት፡** ሀ. መምህር ፊደላትን በማሳየት መጥራት፡፡

ለ. መምህር ፊደላትን እያሳየ ተማሪዎችን ፊደላቱን እንዲጠሩ መጠየቅ፡፡

ሐ. ተማሪዎች ፊደላትን ድምጾችን ማዛመድን መለማመድ፡፡

**እንቅስቃሴ፡** ድምጾችን ከእንቅስቃሴ ጋር ያገናኛል፡፡ ይህ ተማሪዎች አካላቸውን በማንቀሳቀስ ድምጾችንና ፊደላትን እንዲያስታውሱ ማገዝ፡፡

**ቃላትን መመስረት፡** ተማሪዎች የቃላት ክፍሎችን በመጻፍ አዳዲስ ቃላትን መመስረት ማለማመድ፡፡

**ተዘውታሪ ቃላት**፡ በከፍተኛ ደረጃ ተደጋግመው የሚነገሩ ቃላትን ለማወቅ ልምድ ማዳበር

**አፋዊ እንቅስቃሴ፡** ተማሪዎች ድምጾች በአንደበታቸው ውስጥ እንዴት እንደሚፈጠሩ መማር፡፡

**በአየር ላይ መጻፍ፡** ተማሪዎች የተለዩ ፊደላትን በአየር ላይ ወይም በሚጻፍ ነገር ላይ በአመልካች ጣቶቻቸው መጻፍ፡፡ መምህር የፊደሉን ድምጽ ይጠራል፡፡ ተማሪዎች በአየር ላይ ወይም በመጻፊያ ነገር ላይ በጣቶቻቸው መጻፍ፡፡

**ማንበብ፡** መምህር በቃላት ውስጥ ያሉ ድምጾችን እያሳየ መጥራት፡፡ ከዚያም ድምጾቹን ያጣምራል፡፡ (የታወቁ የፊደል ድምጽ ግንኙነቶችን ተጠቀም)

**አርአያ፡** መምህር ተማሪዎች ካሏቸው የማንበብ ችሎታ በላይ የሚነበቡ ምንባቦችን በከፍተኛ ድምጽ ማንበብ፡፡

**ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ፡** ተማሪዎች በትክክል ማንበብን እንዲያዳብሩ ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብን ማቅረብ፡፡

**ቀስበቀስ ማብቃት፡** በአመልካች ጣትና መርህን ተከትለው በገደል ማሚቶ ንባብ፣ በጋራ ንባብ፣ ከሌሎች ጋር አብሮ ማንበብ፡፡

በተደጋጋሚ የሚከሰቱ ፊደላትን መቅረጽ

አረፍተ ነገሮችን መጻፍ

አጭር ምንባብ መጻፍ

## 4. ምዘና


- በቃልና በጽሁፍ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- አካላዊ ምላሽ
- የተማሪዎች በግል ለጥያቄዎች የሚመልሱት አካላዊ ምላሽ
- ኢ-መደበኛ ቁጥጥር
- ምልከታ
- በስዕል መወከል
- ተራ በተራ ማቅረብ
- ስልታዊ ልምምድ
- መውጫ ካርድ

**ክፍለጊዜ፡ አንድ**

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

መምህር ዛሬ ተማሪዎች የሚያዳምጡት ትምህርት ርዕስ ምግብ በሚለው ምዕራፍ ውስጥ " የምግብ አይነቶች " የሚል ነው፡፡ በቅድሚያ የሚደመጠውን ታሪክ በንቃት እንዲከታተሉና ለማዳመጥ እንዲዘጋጁ ያድርጓቸው፡፡ ተማሪዎች በመጽሀፉ ላይ ያሉትን ስዕሎች አይተው ስለምን እንደሚያዳምጡ እንዲገምቱ መጠየቅ፣ ግምታቸውን ማጠናከር ወይም መለወጥ እንደሚችሉ ይንገሯቸው፡፡ የጽሀፉንም ርዕስ ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ተማሪዎቹ እንዲገምቱ ያድርጓቸው ፡፡ በመቀጠል የቢጋር ሰንጠረዥ ሰሌዳው ላይ በመጻፍ ተማሪዎች የምግብ አይነቶች የሚሏቸውን በቢጋር ሰንጠረዥ ላይ ይጻፉ::

**ተማሪዎቹ የሚሰጡትን የምግብ አይነቶች ዝርዝር በቢጋር ሰንጠረዥ ላይ ይጻፉ፡፡**




**የተማሪዎቹን የቀደመ እውቀት ለመቀስቀስ የሚከተሉትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡**

1. **ምግብ ለምን ይጠቅማል?**
2. **የምግብ አይነቶችን ዘርዝሩ፡፡**

> *መምህር የሚደመጠውን ታሪክ በዝግታ ሁለቴ ደጋግመው ያንብቡላቸው፡፡ በጽሁፉ ውስጥ ከቀረቡት ቃላት ውስጥ አዳዲስና ከባድ ቃላትና ሀረጋት ይሆናሉ ብለው ያሰቧቸውን በቅድሚያ ፍቺ ይስጧቸው፡፡ በምንባቡም መሃል ንባቦትን ገታ አድርገው የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎችን ያቅርቡላቸው፡፡*

## የምግብ አይነቶች

**ምግብ ለሰውነታችን እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ የተመጣጠነ ምግብ ከተመገብን ጤንነታችን ይጠበቃል፡፡ ምግብ በውስጡ ጠቃሚ የሆኑ ንጥረ ነገሮችን ይዟል፡፡ በአካባቢያችን የተለያዩ የምግብ አይነቶች አሉ፡፡ የምግብ አይነቶችን ባህላዊና ዘመናዊ ብለን ልንከፍላቸው እንችላለን፡፡ ምግቦች በአይነታቸው የተለያዩ ከመሆናቸውም በተጨማሪ የሚገኙባቸው ምንጮችም የተለያዩ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ከአዝዕርት፣ ከጥራጥሬ፣ ከአትክልት፣ ከፍራፍሬ፤ ከእንሰሳና ከእንጓሳት ውጤቶች ሊገኙ ይችላሉ፡፡**

**(የማዳመጥ ጊዜ)** ባህላዊና ዘመናዊ ምግቦች ምን ምን ናቸው?

ባህላዊ ምግቦች የአንድ ማህበረሰብ መለያ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ገንፎ፣ አንጮቴ፣ ክትፎ በባህላዊ ምግብነት የሚመደቡ ሲሆኑ፣ ከዘመናዊ ምግቦች ደግሞ ፓስታ፣ ፒዛ፣ ኬክ ወዘተ ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ ባህላዊም ሆኑ ዘመናዊ ምግቦች የየራሳቸው የሆነ የአሰራር መንገድ አላቸው፡፡

## የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች

**መምህር/ት**

ማዳመጣቸውን የሚፈትሹ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡ ጥያቄዎችን በተናጥልና በተራ በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡

1. ባህላዊ ምግቦችን ዘርዝሩ፡፡
2. ዘመናዊ ምግቦችን ዘርዝሩ፡፡

**ክፍለጊዜ፡ ሁለት**

መምህር በክፍለጊዜ አንድ የማዳመጥ ትምህርታቸው ስለ ምግብ አይነቶችና ምግብ ከየት እንደሚገኙ አዳምጠዋል፡፡ በዚህ ክፍልጊዜ ደግሞ ምግብ እንዴት ሊዘጋጅ እንደሚችል አንድ የባህላዊ ምግብ በመውሰድ እናያለን፡፡ ወደ የማዳመጥ ትምህርቱ ተማሪዎች ከመግባታቸው በፊት በመማሪያ መጽሀፋቸው ውስጥ ያሉትን ምስሎች አይተው የሚደመጠውን የማዳመጥ ርዕስ እንዲገምቱ ያድርጓቸው፡፡ በመቀጠልም ከዚህ በታች ያሉትን የቅድመ የማዳመጥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

## የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. በአካባቢያችሁ ከሚገኙ ምግቦች ውስጥ የአንድ የምግብ አዘገጃጀትን ግለጹ፡፡
2. ምግብ ለማዘጋጀት ቅድመ ተከተል ያስፈልጋል?ለምን?

| |
|---|
| መምህር የሚደመጠውን ታሪክ በዝግታ ሁለቴ ደጋግመው ያንብቡላቸው፡፡ በጽሁፉ ውስጥ ከቀረቡት ቃላት ውስጥ አዳዲስና ከባድ ቃላትና ሀረጋት ይሆናሉ ብለው ያሰቧቸውን በቅድሚያ ፍቺ ይስጧቸው፡፡ በምንባቡም መሃል ንባቦትን ገታ አድርገው የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎችን ያቅርቡላቸው፡፡ |

ጫልቱ ተወልዳ ያደገችው አዳማ ነው፡፡ ከባህላዊ ምግብ ውስጥ በጣም የምትወደው ገንፎን ነው፡፡ እናቷም ለቁርስ አዘወትረው የሚያዘጋጁት ገንፎ ነው፡፡ ገንፎ ከተለያዩ እህሎች ሊዘጋጅ ይችላል፡፡

(**የማዳመጥ ጊዜ** ) ተማሪዎች ገንፎ እንዴት እንደሚዘጋጅ ታውቃላችሁ?

ገንፎ በብዛት ከገብስ ዱቄት ይሰራል፡፡ የአዘገጃጀት ሂደቱም፡- በቅድሚያ ዱቄቱ ይቀርባል፡፡ እንደየአካባቢው የሸክላ ወይም የብረት ድስት ውሃ ተጨምሮበት ይጣዳል፡፡ ውሃው ሲፈላ ዱቄቱ ተመጥኖ ይጨመርበታል፡፡ ዱቄቱን ከውሃው አዋህዶ ለማብሰልም ማማሳያ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ በደንብ እስኪበስልና ውሃው ከውስጡ እስኪያልቅ እሳቱ ላይ እየተላገ ይቆያል፡፡ ከበሰለም በኋላ ከምድጃ ይወርዳል፡፡ ወደ ጎድጓዳ ሰሃን ወይም ቆሪ ይገለበጥና የተዘጋጀው ቅቤና ሚጥሚጣ ተደርጎበት ለመመገብ ዝግጁ ይሆናል፡፡

## ድህረ ማዳመጥ

**መምህር/ት**

ማዳመጣቸውን የሚፈትሹ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡( ጥያቄዎችን በተናጥልና በተራ በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ)

1. የገንፎ አዘጋጃጀት ቅደም ተከተልን ግለጹ?
2. እስቲ በአካባቢያችሁ የሚዘወተር ምግብ እንዴት እንደሚሰራ ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ?

**ክፍለጊዜ ሶስት**

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

መምህር በክፍለጊዜ ሁለት ስር "የገንፎ አዘገጃጀት" በሚለው ርዕስ ተማሪዎች በአዳመጡት ምንባብ መሰረት የገንፎ አዘገጃጀትን ቅደም ተከተል ጠብቀው ንግግር እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው፡፡ ለዚህም ተግባር በቅድሚያ በሞዴልነት እርሶ አጭር ንግግር በማድረግ ያሳያቸዋል፡፡ ተማሪዎችም ተራ በተራ እጅ እያወጡ ንግግር እንዲያደርጉ በመጠየቅ ተማሪዎች ንግግር እንዲያደርጉ እድል ይስጧቸው፡፡ በንግግር ወቅትም ተማሪዎች በስህተታቸው እንዳይሸማቀቁ እያደነቋቸው ስህተታቸውን በብልሀት ያርሟቸው፡፡

**ክፍለጊዜ፡ አራት**

መምህር በዚህ ክፍለ ጊዜ ውስጥ ተማሪዎችዎ በራሳቸው ምርጫ በአካባቢያቸው ከሚዘወተር የባህል ምግቦች ውስጥ አንዱን በመምረጥ አዘገጃጀቱን ቅድም ተከተል ጠብቀው በንግግር እያቀረቡ የንግግር ክሂላቸውን የሚያዳብሩበት ነው፡፡ ስለዚህም ተማሪዎች በምግብ አዘገጃጀት ላይ ንግግር ከማድረጋቸው በፊት ምግብ ሲዘጋጅ ቅደም ተከተልን አስፈላጊ መሳሪያዎች መጥቀስ እንዳለባቸው በቅድሚያ በሞዴልነት እርሶ

ንግግር በማድረግ ያሳዩአቸው፡፡ በአሳዩአቸው መሰረት እንዲያደርጉ ለሁሉም ተማሪዎች እድል ተራ በተራ በመስጠት ንግግር እንዲያድርጉ ያድርጓቸው፡፡ የእርሶም እገዛ አይለያቸው፡፡

**ክፍለጊዜ አምስት እስከ አስራ አምስት**

## ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

መምህር ከክፍለጊዜ 5-11 ድረስ የቀረቡ ሞክሼ ፊደላትን (ሀ፤ ሐ፤ ኀ እና ዘሮቻቸው) ድምጽና ቅርጽ አዋህዶ ለማስለየት በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡትን የፊደላት ቅርጽና ምስል ድምጽንም በመጨመር እንዲያዛምዱ ይርዷቸው፡፡ ይህንን ሲተገብሩ በቅድሚያ እርሶ ይስሩ፤ በመቀጠልም ከተማሪዎችዎ ጋር አብረው ይስሩ፤ በመጨረሻም ተማሪዎችዎ እራሳቸውን ችለው በተናጠል እንዲሰሩ ይርዷቸው፡፡ ተማሪዎች የሚያውቋቸው በተተኳሪ ሞክሼ ድምጾች የተመሰረቱ ቃላት እንዲጠሩልዎት ያድርጉና የተወሰኑትን ይምረጡላቸው፡፡ ከዚያም የተመረጡትን ቃላት በጋራና በተናጠል ያለማምዷቸው፡፡ ተማሪዎች ተተኳሪ ሞክሼ ፊደሎች ያሉበትን ቃላት ሲጠሩ በማጨብጨብ ተተኳሪ ፊደሉን እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡ እባክዎ መምህር ተማሪዎቹ ይህንኑ ለተወሰነ ጊዜ እየደጋገሙ እንዲለማመዱ ያትጓቸው፡፡ ተተኳሪ ድምፆች በቃል መነሻ፣ በቃል መሀከልና በቃል መድረሻ ላይ ሊመጡ እንደሚችሉ ግንዛቤ ለመፍጠር ድምፆቹ ያሉባቸውን ቃላት በቃል እያቀረቡ እንዲለማመዱ ይሁን፡፡ ለምሳሌ "ፈ" በቃል መነሻ "ፈረስ" በቃል መሃል "ሰፈረ" በቃል መጨረሻ "ሰነፈ" እንደሚገኙ በሁለም ተተኳሪ ድምጾች በቂ ምሳሌ በመስጠት ያለማምዱ፡፡ በተጨማሪም በየክፍለጊዜው የሚማሩትን ፊደላት ቅርጽ በባለቀለም ወረቀት ግድግዳ ላይ መለጠፍ ፣ ፊደላትን ጎላ አድርጎ በሰንጠረዥ ማቅረብ፣ በካርቶን ላይ ፍላሽ ካርዶችን አዘጋጅቶ መጠቀም ፣ ፍላሽ ካርዶችን ጠረጴዛ ላይ በታትኖ በማሰቀመጥ እንዲመርጡ ማድረግ፣ በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ከቀረቡት ቃላት በተጨማሪ ተማሪዎች ሌሎችን እንዲያፈልቁ ማበረታታት፣ ተማሪ ከሳጥን ውስጥ እንድ ተራ በተራ ፍላሽ ካርዱን እንደ እጣ በማውጣት፣ ያወጣውን ከፍ አድርጎ በማሳየት ሌሎች ተማሪዎች እንዲጠሩ በማድረግ ትምህርቱን ማቅረብ ይቻላል፡፡

መምህር ከመልመጃ አንድ እስከ አስራ ሶስት ያሉት በቃል ውስጥ ያሉትን ድምጾች ወይም ፊደሎች በመነጠልና በማጣመር የተተኳሪ ሞክሼ ድምጾች ድምጻቸውን፣

ምልክታቸውን የሚለዩበት ነው፡፡ በዚህ መሰረት በቅድሚያ በቃል ውስጥ ያሉትን ድምጾች እየለዩ በሞዴልነት ያሳይዋቸው፡፡ በመቀጠል ከተማሪዎችዎ ጋር በመሆን በቃላት ውስጥ ያሉትን ድምጾች እየነጠሉና እያጣመሩ በመደጋገም በህብረት ይስሩ፡፡ በቃላት ውስጥ ያሉትን ድምጾች ሲነጥሉ በፊደሎቹ መጠን ተማሪዎች እንዲያጨበጭቡ ያድርጓቸው፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪዎች በቃል ውስጥ ስንት ፊደሎች እንዳሉ በቀላሉ በዜማ መልክ እንዲማሩ ይረዳቸዋል፡፡ ለምሳሌ "ፈረስ" በሚለው ቃል ውስጥ ሶስት ፊደሎች ስላሉ ተማሪዎች ሶስቴ እንዲያጨበጭቡ ያድርጓቸው፡፡ ከዚህ ልምምድ በኋላ ተማሪዎችዎ እራሳቸውን ችለው በግል እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡ የቀሩትን መልመጃዎች ተማሪዎቹም በመማሪያ መጽሀፉ ላይ ያሉትን ተግባራት እየሰሩ እንዲለማመዱ ይርዷቸው፡፡ የእርሶም እገዛና ክትትል እንዳይለያቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ፡ አስራ ሁለት**

መምህር ከክፍለጊዜ አስራ ሁለት የቀረቡ ፊደል (ኸ እና ዘሮቹ) ፡፡ ይህ ድምጽ በተለየ በመደጋገም ተማሪዎችዎን መለማመድና ድምጹንና ምልክቱን ማስለየት ይጠይቃል፡፡ ድምጽና ቅርጽ አዋህዶ ለማስለየት በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡትን የፊደላት ቅርጽና ምስል ድምጽንም በመጨመር እንዲያዛምዱ ይርዷቸው፡፡ ይህንን ሲተገብሩ በቅድሚያ እርሶ ይስሩ፤ በመቀጠልም ከተማሪዎችዎ ጋር አብረው ይስሩ፤ በመጨረሻም ተማሪዎችዎ እራሳቸውን ችለው በተናጥል እንዲሰሩ ያርዷቸው፡፡ ተማሪዎች የሚያውቋቸው በተተኳሪ ድምጽ የተመሰረቱ ቃላት እንዲጠሩልዎት ያድርጉና የተወሰኑትን ይምረጡላቸው፡፡ ከዚያም የተመረጡትን ቃላት በጋራና በተናጠል ያለማምዷቸው፡፡ ተማሪዎች ተተኳሪ ሞክሼ ፊደሎች ያሉበትን ቃላት ሲጠሩ በማጨብጨብ ተተኳሪ ፊደሉን እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡ እባክዎ መምህር ተማሪዎቹ ይህንኑ ለተወሰነ ጊዜ እየደጋገሙ እንዲለማመዱ ያትጓቸው፡፡ በተተኳሪ ድምጹ በቂ ምሳሌ በመስጠት ያለማምዱ፡፡ በተጨማሪም በየክፍለ ጊዜው የሚማሩትን ፊደላት ቅርጽ በባለቀለም ወረቀት ግድግዳ ላይ መለጠፍ ፣ ፊደላትን ጎላ አድርጎ በሰንጠረዥ ማቅረብ፣ በካርቶን ላይ ፍላሽ ካርዶችን አዘጋጅቶ መጠቀም፣ ፍላሽ ካርዶችን ጠረጴዛ ላይ በታትኖ በማሰቀመጥ እንዲመርጡ ማድረግ፣ በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ከቀረቡት ቃላት በተጨማሪ ተማሪዎች ሌሎችን እንዲያፈልቁ ማበረታታት፣ አንድ ተማሪ ከሳጥን ውስጥ ተራ በተራ ፍላሽ ካርድን እንደ እጣ በማውጣት፣ ያወጣውን ከፍ አድርጎ በማሳየት ሌሎች ተማሪዎች እንዲጠሩ በማድረግ ትምህርቱን ማቅረብ ይቻላል፡፡


**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሶስት**

# ትምህርት አራት ፡ ቃላት

መምህር በዚህ ክፍል ውስጥ ተማሪዎች የትምህርት እና የተዘውታሪ ቃላት ችሎታቸውን የሚዳብሩበት ነው፡፡ የቃላት ችሎታቸውን ለማደበር በመልመጃ አስራ አምስት የተሰጡትን ቃላት ከፍቻቸው እያዛመዱ የቃላት ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ያለማምዷቸው፡፡ ስለዚህም በምሳሌው መሰረት እርሶ ለቃላት ፍቺ እየሰጡ ያሳይዋቸው። በመቀጠልም ከተማሪዎችዎ ጋር በህብረት በመስራት በቂ ልምምድ ከሰጧቸው በኋላ እራሳቸውን ችለው በመማሪያ መጽሀፋቸው ውስጥ በመልመጃ አሥራ አምስት ያሉትን ጥያቄዎች በተናጠል ያሰሯቸው፡፡ በመጨረሻም የመልመጃውን መልስ በሰሌዳ ላይ በመጻፍ ተማሪዎችዎ እርማት እንዲውስዱ ያድርጓቸው፡፡

**መልመጃ አስራ አምስት፡**

**የሚከተሉትን ቃላት ከፍቻቸው ጋር አዛምዱ**




**ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት**

መምህር በክፍለጊዜ አስራ ሶስት በቃላት ትምህርት ስር ተማሪዎች ቃላትን ከፍቺያቸው ጋር እያዛመዱ የቃላት ችሎታቸውን እንዳዳበሩ ይታመናል፡፡ ይህንኑ የቃላት ትምህርት ለማጠንከር በመልመጃ አስራ ስድስት ስር ለተዘረዘሩት ቃላት ተማሪዎች ፍቺ እየሰጡ እንዲለማመዱና የቃላት እውቀታቸው እንዲዳብር ያትጓቸው፡፡ ይህንን ለመተግበር በቅድሚያ በሞዴልነት በምሳሌው መሰረት ለቃላት ፍቺ እየሰጡ ያለማምዷቸው፡፡ በመቀጠልም ከተማሪዎች ጋር በህብረት ለተለያዩ ቃላት ፍቺ

በመስጠት ያለማምዷቸው፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎች እራሳቸውን ችለው ለቃላቱ ፍቺ እንዲሰጡ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ በመልመጃ አሥራ ስድስት ላይ የቀረቡትን ቃላት ያሰሯቸው፡፡ የተማሪዎችዎንም ጥረት እያደነቁ እገዛ ለሚፈልጉ ተማሪዎች እገዛ ያድርጉላቸው፡፡ ቃላቱም የተለያዩ ፍቺ ሊይዙ እንደሚችሉ በምሳሌ ያመልክቷቸው፡፡ ለቃላቱ ፍቺ ናቸው የሚሏቸውን የቃላት ፍቺ ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ተማሪዎች እርማት እንዲወስዱ ድርጓቸው፡፡

**መልመጃ አስራ ስድስት**

1. ተሰራ= ተዘጋጀ/ተከናወነ/ተቀነባበረ...
2. አጸዳ= አነጻ/ጠረገ/ አስተካከለ....
3. በሰለ= ደረሰ/ተዘጋጀ/ ....
4. መገበ= አበላ/ሰጠ...
5. እሳት= የሚያቃጥል/ሀይለኛ...

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት**

# ትምህርት አምስት፡ ጽህፈት

መምህር በዚህ ክፍለጊዜ ውስጥ የተመረጡ የሞክሼ ድምጾች ቅርጻቸውን በደንብ ለይተው እንዲጽፉ ተማሪዎችን ለማለማመድ የተዘጋጀ መልመጃ የሚቀርብበት ነው፡፡ ስለዚህ መምህር ተማሪዎች በትክክል የ"ሐ" እና "ኀ" ድምጾችን ከነዘራቸው ደጋግመው እንዲጽፉ በማድረግ ተማሪዎችዎን ይርዷቸው፡፡ ይህም ሲሆን በቅድሚያ እርሶ ቀስ በማለት ፊደሎችን በየተራ እየቀረጹ የሳይዋቸው፡፡ በመማሪያ መጽሀፉ በመልመጃ አስራ ሰባት ያለውን ተማሪዎች ደብተራቸው ላይ ጽፈው እንዲለማመዱ ያድርጓቸው፡፡ የተለመደውም እገዛዎት ከተማሪዎችዎ አይለይ፡፡

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት**

መምህር በዚህ ክፍለጊዜ ውስጥ የተመረጠ ድምጽ ቅርጽ በደንብ ለይተው እንዲጽፉ ተማሪዎችን ለማለማመድ የተዘጋጀ መልመጃ የሚቀርብበት ነው፡፡ ስለዚህ መምህር ተማሪዎች በትክክል የ"ኸ" ን ድምጽ ከነዘራቸው ደጋግመው እንዲጽፉ በማድረግ ተማሪዎችዎን ይርዷቸው፡፡ ይህም ሲሆን በቅድሚያ እርሶ ቀስ በማለት ፊደሎችን በየተራ እየቀረጹ የሳይዋቸው፡፡ በመማሪያ መጽሀፉ በመልመጃ አስራ ስምንት ያለውን

ተማሪዎች ደብተራቸው ላይ ጽፈው እንዲለማመዱ ያድርጓቸው፡፡ የተለመደውም እገዛዎት ከተማሪዎችዎ አይለይ፡፡

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

መምህር በክፍለጊዜ አሰራ ስድስት የተማሩትን የሞክሼ ፊደላትን ቅርጽ የሚቀጥል ተግባር ነው፡፡ ስለዚህም በክፍለ ጊዜ አስራስድስት በተናጠል ሲጽፉቸው የነበርውን የሞክሼ ዶምጾች ምልክት በቃላት ደረጃ እንዲጽፉ የተዘጋጀ መልመጃ ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎችው በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ በመልመጃ አስራ ዘጠኝ የተዘረዘሩት ቃላት ደጋግመው በደብተራቸው ላይ እየጻፉ እንዲለማመዱ ያድርጓቸው፡፡ በዚህም ልምምድ ተማሪዎችዎን እያደነቁ እገዛ ለሚፈልጉ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

መምህር በዚህ ክፍል ውስጥ በክፍለጊዜ አስራ ሰባት ሞክሼ ድምጾች በቃል ደረጃ ሲጸፏቸው የነበሩትን ቃላት በአረፍተ ነገር ደረጃ እየጻፋቸው የሚለማመዱበት ክፍል ነው፡፡ ይህም ሲሆን ተማሪዎችዎ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ በመልመጃ ሃያ ያሉትን ቃላት በደብተራቸው እየጻፉ የሚለማመዱበት ነው፡፡ በዚህም ልምምድ ተማሪዎችዎን እያደነቁ እገዛ ለሚፈልጉ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡

# ምዕራፍ ዘጠኝ

# የግል ንጽህና

(18 ክፍለ ጊዜ)

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

**ከዚህ ምእራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ምንባብን አዳምጠ መልዕክቱን በቃል ይገልጻሉ፡፡
- አዳዲስ ፊደላትን/ድምጾችን ያነባሉ(የተመረጡ ድምጾች(ሠ፣ ሰ) /ፊደላት) ይዘረዝራሉ፡፡
- ድምጾችን በመነጠልና በማጣመር (የተመረጡ ድምጾች /ፊደላት (ሠ፣ ሰ)) ያነባሉ::
- ከግል ንጽህና ጋር የተያያዙ ቃላትን ያነባሉ፡፡
- ባለሁለት ቀለም ቃላትን ነጥለው ያጣምራሉ፡፡

## 2. ዝርዝር ይዘቶች

- ትዕምርተ ድምጻዊ ግንዛቤ
- ድምጾች/ፊደላት(ሠ፣ ሰ) መለየት
- ድምጾችን መነጠልና ማጣመር
- ቅጥያዎችን መለየት

## 3. የመማር ማስተማር ብልሀቶችና መሳሪያዎች

መምህር በከፊል የተዘጋጀ የቢ.ጋር ሰንጠረዥ አዘጋጅቶ ቀሪውን ተማሪዎች ከሚያዳምጡት ምንባብ እንዲያሟሉ መጠየቅ፡፡ ከግል ንጽህና ጋር የተያያዙ ቃላትን (ለምሳሌ፡- ጽዱ፣ ንጹህ፣ ማጠብ፣ ቆሻሻ፣ ዘዴ፣ ጥቅምና አደገኛ)

**መለየት፡** መምህር በቃላት ውስጥ የተመረጡ ድምጾችን/ፊደላትን መጥራት፡፡ መጀመሪያ መምህር በቃላት ውስጥ ያሉትን ድምጾች በመነጠልና በማጣመር ሞዴል መሆን፡፡ ከዚያም ተማሪዎች አምስት ድምጾችን በቃላት ውስጥ ለይተው በመነጠልና በማጣመር (የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣ የባለቀለም ወረቀት፣ የካርቱን ስዕሎች፣ የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ ወዘተ) መጠቀም፡፡

**መቁጠር፡** ተማሪዎች በአረፍተነገር ውስጥ ባሉ ቃላት፣ በቃል ውስጥ ባሉ ተመሳሳይ ቀለሞች፣ በቃላት ውስጥ ባሉ ድምጾች መጠን ማጨብጨብ (የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣ የባለቀለም ወረቀት፣ የካርቱን ስዕሎች፣ የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ ወዘተ ተጠቀም)

**ተመሳሳይ ድምጽ** ተማሪዎች ተመሳሳይ ቀለም ያላቸውን ቃላት መፍጠር፤ መምህሩም በሰሌዳ ላይ ምላሽ መጻፍ፡፡

**ማጣመርና መነጠል፡** ተማሪዎች በቃሉ ውስጥ ያሉትን ድምጾች በመነጠል መናገር፡፡ (በፍጥነት ማስባል) በመቀጠል (መምህር መነጠልን ለማሳየት ፊደላትን ማጣመር)፡፡ ተማሪዎች ቃሉን ጠርተው በቃሉ ውስጥ ያሉትን ቀለሞችና ድምጾች መጥራት፡፡

**ቀስበቀስ ማብቃት፡** ሀ. መምህር ፊደላትን በማሳየት መጥራት፡፡

ለ. መምህር ፊደላትን እያሳየ ተማሪዎችን ፊደላቱን እንዲጠሩ መጠየቅ፡፡

ሐ. ተማሪዎች ፊደላትንና ድምጾችን ማዛመድን መለማመድ፡፡

**እንቅስቃሴ፡** ድምጾችን ከእንቅስቃሴ ጋር ማገናኘት፡፡ ይህ ተማሪዎች አካላቸውን በማንቀሳቀስ ድምጾችንና ፊደላትን እንዲያስታውሱ ማገዝ፡፡

**ቃላትን መመስረት፡** ተማሪዎች የቃላት ክፍሎችን በመጻፍ አዳዲስ ቃላትን በመመስረት መለማመድ፡፡

**ተዘውታሪ ቃላት፡** በከፍተኛ ደረጃ ተደጋግመው የሚነገሩ ቃላትን ለማወቅ ልምድ ማዳበር

**መናገር፡** ሀ.መምህር ቃላትን በማሳየት፣ እያንዳንዱን ድምጽ በመጥራት፣ ድምጾችን በመነጠል (የታወቁ የድምጾችን ምልክቶች በመጠቀም) ማስተባበር፡፡ መምህር መር በሆነ ዘዴ ተማሪዎች ድምጾችን መነጣጠል፡፡

**አርአያ፡** መምህር ተማሪዎች ካሏቸው የማንበብ ችሎታ በላይ የሚነበቡ ምንባቦችን በከፍተኛ ድምጽ ማንበብ፡፡

**ድምጾችን መቅረጽ**

**ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ፡** ተማሪዎች ለተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ እንዲጋለጡ እድል መስጠት፡፡

**ቀስበቀስ ማብቃት፡** በአመልካች ጣትና መርህን ተከትለው በገደልማሚቶ ንባብ፣ በጋራ ንባብእና ከሌሎች ጋር አብሮ ማንበብ፡፡

**በተደጋጋሚ የሚከሰቱ ፊደላትን መቅረጽ፡**

ተማሪዎች የተለዩ ፊደላትን በአየር ላይ ወይም በሚጻፍ ነገር ላይ በአመልካች ጣቶቻቸው መጻፍ፡፡ መምህር የፊደሉን ድምጽ መጥራት፡፡ ተማሪዎች በአየር ላይ ወይም በመጻፊያ ነገር ላይ በጣቶቻቸው መጻፍ፡፡

## 4.ምዘና

- ተማሪዎች በግል ለጥያቄዎች የሚመልሱት አካላዊ ምላሽ
- ኢመደበኛ ቁጥጥር፣ምልከታ ፣በስዕል መወከል ተራ በተራ ማቅረብ
- ስልታዊ ልምምድ፣
- መውጫ ካርድና ጽብረቃ ይጠቀሙ፡፡

**ክፍለጊዜ፡ አንድ**

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### ቅድመ ማዳመጥ፡

መምህር ዛሬ ተማሪዎች የሚያዳምጡት ትምህርት ርዕስ የግል ንጽህና" በሚለው ምዕራፍ ውስጥ "አቶ ጉርሜሳ" የሚል ነው፡፡ በቅድሚያ የሚደመጠውን ታሪክ በንቃት እንዲከታተሉና ለማዳመጥ እንዲዘጋጁ ያድርጓቸው፡፡ ተማሪዎች በመጽሀፉ ላይ ያሉትን ስዕሎች አይተው ስለምን እንደሚያዳምጡ እንዲገምቱ መጠየቅ፣ ግምታቸውን ማጠናከር ወይም መለወጥ እንደሚችሉ ይንገሯቸው፡፡ የጽሁፉንም ርዕስ ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ተማሪዎቹ እንዲገምቱ ያድርጓቸው፡፡ ወደ ሚደመጠው ምንባብ ከመግባቱ በፊት የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ለመቀስቀስ ከዚህ በታች ያለውን የቢጋር ሰንጠረዥ ሰሌዳው ላይ በመጻፍ ተማሪዎች የግል ንጽህና የሚያሟላቸውን በቢጋር ሰንጠረዥ ላይ እንዲሞሉ ያድርጓቸው ፡፡

የግል ንጽህና በቢጋር ሰንጠረዥ ላይ ይጻፉ፡፡

**ይህን የቢጋር ሰንጠረዥ በቅድመ ማዳመጥ ያሰሯቸው፡፡**

| የግል ንጽህና | | | | |
|---|---|---|---|---|
| • ገላን መታጠብ | • ጸጉርን መከርከም | • ጥፍርን መቁረጥ | • ልብስን ማጠብ | • እጅን መታጠብ |
| • ንጹህ ውሃ መጠጣት | • ቆሻሻን መቅበር | • ጥርስን በውሃና ሳሙና መቦረሽ | • እግርን መታጠብ | • ጆሮን ማጽዳት |

*መምህር የሚደመጠውን ታሪክ በዝግታ ሁለቴ ደጋግመው ያንብቡላቸው፡፡ በጽሁፉ ውስጥ ከቀረቡት ቃላት ውስጥ አዳዲስና ከባድ ቃላትና ሀረጋት ይሆናሉ ብለው ያሰቧቸውን በቅድሚያ ፍቺ ይስጧቸው፡፡ በምንባቡም መሃል ንባቦትን ገታ አድርገው የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎችን ያቅርቡላቸው፡፡*

## "አቶ ጉርሜሳ"

የኔ ስም ጉርሜሳ ነው፡፡ የኔንና የቤተሰቦቼን የግል ንጽህና እጠብቃለሁ፡፡ የልጆቼን ልብስ ወንዝ አጥባለሁ፡፡ ገላቸውን እንዲታጠቡ ልጆቼን እመክራለሁ፡፡ ከምግብ በፊትና በኋላ እጃቸውን በውሃና ሳሙና እንዲታጠቡ አደርጋለሁ፡፡ ጥፍራቸው እና ጸጉራቸው ሲያድግ እቆርጣለሁ፡፡

**(የማዳመጥ ጊዜ)** የግል ንጽህናችን ለምን እጠብቃለን?

የግል ንጽህና መጠበቅ ጤናማ እንድንሆን ይረዳል፡፡ ጥርሳችንን መፋቅ ከመጥፎ ጠረን ይከላከልልናል፡፡ ከመጸዳጃ ቤት ተጸዳድተን ስንወጣ እጃችንን በውሃና ሳሙና መታጠብ ያስፈልጋል፡፡ የግል ንጽህናን መጠበቅ ከበሽታ እንድንጠበቅ ይረዳናል፡፡

## የድህረ ማዳመጥ ጥያቄ

*መምህር ማዳመጣቸውን የሚፈትሹ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡ ጥያቄዎችን በተናጠልና በተራ በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡*

1. የግል ንጽህና ባንጠብቅ ምን እንሆናለን?
2. የግል ንጽህናችንን እንዴት እንጠብቃለን?

**ክፍለጊዜ፡ ሁለት**

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

መምህር በዚህ ክፍል ተማሪዎች ካዳመጡት የግል ንጽህና ታሪክ ተነስተው የግል ንጽህናቸውን እንዴት እንደሚጠብቁ፣ የግል ንጽናቸውን ለመጠቀም የሚያስፈልጉ ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ እየዘረዘሩ የንግግር ክሂላቸው እንዲዳብር ልምምድ የሚያደርጉበት ነው፡፡ ይህም ተግባር የተሳካ እንዲሆን በቅድሚያ እርሶ በሞዴልነት በርዕሱ ላይ በአጭሩ ንግግር በማቅረብ ለተማሪዎች ያሳዩ፡፡ በመቀጠል ተማሪዎች ተራ በተራ እጃቸውን እያወጡ ንግግር እንዲያደርጉ እድል ይሰጣሉ፡፡ ተማሪዎችም የፍርሃት ስሜት እንዳይኖርባቸው ያበረታቷቸው፡፡ በንግግር ወቅትም ለሚፈጽሙት ስህተት በብልሀት ማስተካከያ ይስጧቸው፡፡ ተማሪዎች ንግግራቸውን ከጨረሱ በኋላ የክፍሉ ተማሪን በማስጨብጨብ ያበረቷቷቸው፡፡ ፈጣን ተማሪዎችን ማበልጸግና እገዛ ለሚሹ ተማሪዎች የቅርብ ክትትልና እርዳታዎት አይለያቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ሶስት እስከ ዘጠኝ**

# ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

መምህር ከክፍለጊዜ 3-9 ድረስ የቀረቡ ሞክሼ ፊደላትን (ሠ፣ ሰ እና ዘሮቻቸው) ድምጽና ቅርጽ አዋህዶ ለማስለየት በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡትን የፊደላት ቅርጽና ምስል ድምጽንም በመጨመር እንዲያዛምዱ ይርዷቸው፡፡ ይህንን ሲተገብሩ በቅድሚያ እርሶ ይስሩ፤ በመቀጠልም ከተማሪዎችዎ ጋር አብረው ይስሩ፤ በመጨረሻም ተማሪዎችዎ እራሳቸውን ችለው በተናጠል እንዲሰሩ ያርዷጓቸው፡፡ ተማሪዎች የሚያውቋቸው በተተኳሪ ሞክሼ ድምጾች የተመሰረቱ ቃላት እንዲጠሩልዎት ያድርጉና የተወሰኑትን ይምረጡላቸው፡፡ ከዚያም የተመረጡትን ቃላት በጋራና በተናጠል ያለማምዷቸው፡፡ ተማሪዎች ተተኳሪ ሞክሼ ፊደሎች ያሉበትን ቃላት ሲጠሩ በማጨብጨብ ተተኳሪ ፊደሉን እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡ እባክዎ መምህር ተማሪዎቹ ይህንኑ ለተወሰነ ጊዜ እየደጋገሙ እንዲለማመዱ ያትጓቸው፡፡ በሁለም ተተኳሪ ድምጾች በቂ ምሳሌ በመስጠት ያለማምዱ፡፡ በተጨማሪም በየክፍለ ጊዜው የሚማሩትን ፊደላት ቅርጽ በባለቀለም ወረቀት ግድግዳ ላይ መለጠፍ፣ ፊደላትን ጎላ አድርጎ በሰንጠረዥ ማቅረብ፣ በካርቶን ላይ ፍላሽ ካርዶችን አዘጋጅቶ መጠቀም፣ ፍላሽ ካርዶችን ጠረጴዛ ላይ በታትኖ በማሰቀመጥ እንዲመርጡ ማድረግ፣ በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ከቀረቡት ቃላት በተጨማሪ ተማሪዎች

ሌሎችን እንዲያፈልቁ ማበረታታት፣ አንድ ተማሪ ከሳጥን ውስጥ ተራ በተራ ፍላሽ ካርድን እንደ እጣ በማውጣት፣ ያወጣውን ከፍ አድርጎ በማሳየት ሌሎች ተማሪዎች እንዲጠሩ በማድረግ ትምህርቱን ማቅረብ ይቻላል፡፡

መምህር ከመልመጃ አንድ እስከ አምስት ያሉት በቃል ውስጥ ያሉትን ድምጾች ወይም ፊደሎች በመነጠልና በማጣመር የተተኳሪ ሞክሼ ድምጾች ድምጻቸውን፣ ምልከታቸውን የሚለዩበት ነው፡፡ በዚህ መሰርት በቅድሚያ በቃል ውስጥ ያሉትን ድምጾች እየለዩ በሞዴልነት ያሳይዋቸው፡፡ በመቀጠል ከተማሪዎችዎ ጋር በመሆን በቃላት ውስጥ ያሉትን ድምጾች እየነጠሉና እያጣመሩ በመደጋግም በህብረት ይስሩ፡፡ በቃላት ውስጥ ያሉትን ድምጾች ሲነጥሉ በፊደሎቹ መጠን ተማሪዎች እንዲያጨበጭቡ ያድርጓቸው፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪዎች በቃል ውስጥ ስንት ፊደሎች እንዳሉ በቀላሉ በዜማ መልክ እንዲማሩ ይረዳቸዋል፡፡ ለምሳሌ "ሠበረ" በሚለው ቃል ውስጥ ሶስት ፊደሎች ስላሉ ተማሪዎች ሶስቴ እንዲያጨበጭቡ ያድርጓቸው፡፡ ከዚህ ልምምድ በኋላ ተማሪዎችዎ እራሳቸውን ችለው በግል እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡ የቀሩትን መልመጃዎች ተማሪዎቹም በመማሪያ መጽሀፉ ላይ ያሉትን ተግባራት እየሰሩ እንዲለማመዱ ይርዷቸው፡፡ የእርሶም እገዛና ክትትል እንዳይለያቸው፡፡

መምህር ከመልመጃ አምስት እስከ ሰባት ያሉት በቃል ውስጥ ተለምዷዊ ቅጥያዎች ማስለየት ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ ይህን ሲተገብሩ አስቀድመው እርሶ በሞዴልነት ከቃላት ላይ ያሉትን ቅጥያዎች በመለየት ያመልክቷቸው፡፡ በመቀጠልም ይህንኑ ተግባር ከተማሪዎችዎ ጋር በህብረት ይስሩ፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎች በተናጠል እራሳቸውን ችለው እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡ በምሳሌው መሰረትም ተማሪዎች ተለምዷዊ ቅጥያዎችን ከለዩ በኋላ ቃሉን በትክክልና በፍጥነት እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡ በቃል ውስጥ ያሉትን ተለምዷዊ ቅጥያዎችን ሲለዩ በቅጥያዎች ብዛትም ተማሪዎችን በማስጨብጨብ በቀላሉ እንዲለዩ ያድርጉ፡፡ ምሳሌ፡- ስጋሽ = ስጋ-ሽ የሚለው ቃል አንድ ቅጥያ ስላለው አንድ ጊዜ በማስጨብጨብ ያሳይዋቸው የቀሩትን መልመጃዎች ተማሪዎቹም በመማሪያ መጽሀፉ ላይ ያሉትን ተግባራት እየሰሩ እንዲለማመዱ ይርዷቸው፡፡ ይህንንም ተግባር በመደጋገም ያሰሯቸው፡፡ እገዛ ለሚፈልጉ ተማሪዎች እገዛ በማድረግ ከቃላት ውስጥ ተለምዷዊ ቃላትን በትክክልና በተገቢው እንዲለዩ ይርዷቸው፡፡ መልመጃዎችንም በደብተራቸው ላይ ጽፈው እንዲለማመዱ ይዘዟቸው፡፡ የተማሪዎችን ተሰትፎ ለማሳደግ ያበረታቷቸው፡፡

መምህር ትምህርቱን ተጨባጭ ለማድረግ ተለምዷዊ ቅጥያዎችን ለየብቻ በፍላሽ ካርድ አዘጋጅተው በቀኝና በግራ እጅ ወደ ላይ ከፍ አድርገው በመያዝ ከቃላት ጋር እየለዩ ያመልክቷቸው፡፡ ተማሪዎችም ይህንኑ ተግባር ተራ በተራ እየለዩ እንዲያመለክቱ ይርዷቸው፡፡ ተለምዷዊ ቅጥያዎችን በአካባቢ በሚገኙ ቁሳቁሶች ሰርተው እንዲመጡ የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡

## ክፍለጊዜ አስር እስከአስራ አምስት፡

መምህር ከክፍለጊዜ 10-15 ድረስ የቀረቡ ውህድ ድምጾች (ኗ፣ ሟ፣ ሏ፣ ሯ፣ ቋ፣ ቧ፣ ቷ፣ ቿ፣ ጇ፣ ዷ፣ ጓ፣ ጧ፣ ጯ ዟ፣ ኟ፣) ድምጽና ቅርጽ አዋህዶ ለማስለየት በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡትን የፊደላት ቅርጽና ምስል ድምጽንም በመጨመር እንዲያዛምዱ ይርዷቸው፡፡ ይህንን ሲተገብሩ በቅድሚያ እርሶ ይስሩ፤ በመቀጠልም ከተማሪዎችዎ ጋር አብረው ይስሩ፤ በመጨረሻም ተማሪዎችዎ እራሳቸውን ችለው በተናጠል እንዲሰሩ ይርዷቸው፡፡ ተማሪዎች የሚያውቋቸው በተተኳሪ ዲቃላ ድምጾች የተመሰረቱ ቃላት እንዲጠሩልዎት ያድርጉና የተወሰኑትን ይምረጡላቸው፡፡ ከዚያም የተመረጡትን ቃላት በጋራና በተናጠል ያለማምዷቸው፡፡ ተማሪዎች ዲቃላ ፊደሎች ያሉበትን ቃላት ሲጠሩ በማጨብጨብ ተተኳሪ ፊደሉን እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡እባክዎ መምህር ተማሪዎቹ ይህንኑ ለተወሰነ ጊዜ እየደጋገሙ እንዲለማመዱ ያትጓቸው፡፡ በሁሉም ተተኳሪ ድምጾች በቂ ምሳሌ በመስጠት ያለማምዱ፡፡ በተጨማሪም በየክፍለጊዜው የሚማሩትን ፊደላት ቅርጽ በባለቀለም ወረቀት ግድግዳ ላይ መለጠፍ፣ ፊደላትን ጎላ አድርጎ በሰንጠረዥ ማቅረብ፣ በካርቶን ላይ ፍላሽ ካርዶችን አዘጋጅቶ መጠቀም፣ ፍላሽ ካርዶችን ጠረጴዛ ላይ በታትኖ በማስቀመጥ እንዲመርጡ ማድረግ፣ በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ከቀረቡት ቃላት በተጨማሪ ተማሪዎች ሌሎችን እንዲያፈልቁ ማበረታታት፣ አንድ ተማሪ ከሳጥን ውስጥ ተራ በተራ ፍላሽ ካርድን እንደ እጣ በማውጣት፣ ያወጣውን ከፍ አድርጎ በማሳየት ሌሎች ተማሪዎች እንዲጠሩ በማድረግ ትምህርቱን ማቅረብ ይቻላል፡፡

መምህር ከመልመጃ ስምንት እስከ አስራ ሁለት ያሉት በቃል ውስጥ ተለምዷዊ ቅጥያዎች ማስለየት ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ ይህን ሲተገብሩ አስቀድመው እርሶ በሞዴልነት ከቃላት ላይ ያሉትን ቅጥያዎች በመለየት ያመልክቷቸው፡፡ በመቀጠልም ይህንኑ ተግባር ከተማሪዎችዎ ጋር በህብረት ይስሩ፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎች በተናጠል

እራሳቸውን ችለው እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡ በምሳሌው መሰረትም ተማሪዎች ተለምዷዊ ቅጥያዎችን ከለዩ በኋላ ቃሉን በትክክልና በፍጥነት እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡ በቃል ውስጥ ያሉትን ተለምዷዊ ቅጥያዎችን ሲለዩ በቅጥያዎች ብዛትም ተማሪዎችን በማስጨብጨብ በቀላሉ እንዲለዩ ያድርጉ ፡፡ምሳሌ :- ስጋሽ = ስጋ-ሽ የሚለው ቃል አንድ ቅጥያ ስላለው አንድ ጊዜ በማስጨብጨብ ያሳይዋቸው የቀሩትን መልመጃዎች ተማሪዎቹም በመማሪያ መጽሀፉ ላይ ያሉትን ተግባራት እየሰሩ እንዲለማመዱ ይርዷቸው፡፡ ይህንንም ተግባር በመደጋገም ያሰሯቸው፡፡ እገዛ ለሚፈልጉ ተማሪዎች እገዛ በማድረግ ከቃላት ውስጥ ተለምዷዊ ቃላትን በትክክልና በተገቢው እንዲለዩ ይርዷቸው፡፡ መልመጃዎችንም በደብተራቸው ላይ ጽፈው እንዲለማመዱ ይዘዟቸው፡፡ የተማሪዎችን ተሰትፎ ለማሳደግ ያበረታቷቸው፡፡

መምህር ትምህርቱን ተጨባጭ ለማድረግ ተለምዷዊ ቅጥያዎችን ለየብቻ በፍላሽ ካርድ አዘጋጅተው በቀኝና በግራ እጅ ወደ ላይ ከፍ አድርገው በመያዝ ከቃላት ጋር እየለዩ ያመልክቷቸው፡፡ ተማሪዎችም ይህንኑ ተግባር ተራ በተራ እየለዩ እንዲያመለክቱ ይርዷቸው፡፡ ተለምዷዊ ቅጥያዎችን በአካባቢ በሚገኙ ቁሳቁሶች ሰርተው እንዲመጡ የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት**

# ትምህርት አራት፡ ቃላት

መምህር በዚህ ትምህርት ክፍል ውስጥ የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ደረጃ ለማደርጅት የተለያዩ መልመጃዎች የሚሰጡበት ነው፡፡ ስለዚህም ተማሪዎች በሞክሼ ድምጽ የተማሯቸውን ቃላት እያዛመዱ የቃሉንም የሞክሼ ፊደላት በትክክል እንዲይዙ የሚረዳቸው መልመጃ ቀርቦላቸዋል፡፡ ይህንን የቃላት ጥያቄ ከመስራታቸው በፊት ጥያቄ እንዴት መሰራት እንዳለበት በቂ ምሳሌ እየሰጡ ያሳይዋቸው፡፡ በመቀጠል የተውሰኑ ልምምዶችን ከተማሪዎችዎ ጋር በህብረት ይተግብሩ፡፡ ተማሪዎችዎ በቂ ልምምድ ካገኙ በኋላ በመማሪያ መጽሀፉ በመልመጃ አስራ ሶስት የቀረበውን ጥያቄ ደብተራቸው ላይ በመጻፍ በየግል እንዲሰሩ ይዘዟቸው፡፡ ፈጣን ተማሪዎችን እያበለጸጉ የርሶን እገዛ ለሚሹ ተማሪዎች እገዛ ያድርጉላቸው፡፡ የተማሪዎችዎን ሙከራ ያድንቁላቸው‹‹በመጨረሻም ትክክለኛውን መልስ ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ተማሪዎችዎ እርማት እንዲወስዱ ያድርጓቸው፡፡

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

# ትምህርት አምስት፡ ጽሕፈት

መምህር በዚህ ክፍል ውስጥ  በዲቃላ ድምጾች የተመሰረቱ ቃላትን ደጋግመው እየጻፉ ልምምድ የሚያረጉበት ክፍል ነው፡፡ የዲቃላ ድምጾች ቅርጻቸው በዚህ ደረጃ ለሚማሩ ተማሪዎች ፊደላትን ለመቅረጽ ስለሚያስቸግራቸው የመምህሩ ያልሰላቸ እገዛ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ተማሪዎችዎም የሚያደርጉትን ሙከራ ያድንቁላቸው፣ ያበረታቷቸው፡፡ ይህንንም በቅድሚያ ቀስ ብለው ፊደላቱን እየቀረጹ ያሳይዋቸው፡፡ በመቀጠልም ከተማሪዎችዎ ጋር በህብረት በመሆን ልምምዱን ይቀጥሉ፡፡ በመቀጠልም ተማሪዎች እራሳቸውን ችለው በየግል እንዲሰሩ በመማሪያ መጽሀፍ  መልመጃ አስራ አራት ላይ ያለውን ጥያቄ በደብተራቸው እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡ የፊደላቱንም ቅርፅ በሰንጠረዥ ወይም በባለ ቀለም ወረቀት ላይ ወይም በአካባቢ ከሚገኙ ነገሮች ቀርጸ በማሳየት ትምህርቱ ተጨባጭ እንዲሆን ያድርጉ፡፡

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

መምህር በክፍለጊዜ አስራ ስምንት ውስጥ ተማሪዎች  ከሁለት ፊደል የሚመሰረቱ ፍቺ የሚሰጡ ቃላት እየጻፉ የጽህፈት ልምምዳቸውን የሚቀጥሉበት  ክፍል ነው፡፡ ስለዚህም መምህሩ በሞዴልነት ቢቻል ከተማሩት ሞክሼ ድምጽ ወይም ከዲቃላ ድምጽ የተወሰዱ ቢሆኑ ይመረጣል አለበለዚያም ትምህርታዊ ቃላት ወይም ሌላ ሊሆን ይችላል ቃላት እየጻፉ የሚለማመዱበት ነው፡፡ ተማሪዎች ቃላቱን ሲመሰርቱ  ቃሉ ባለ ሁለት ፊደል ያለውና ፍቺ የሚሰጥ መሆን እንዳለበት በሞዴልት በቅድሚ እየሰሩ ያሳይዋቸው፡፡ በመቀጠል ከተማሪዎችዎ ጋር በመሆን አብረው ይስሩ፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎችዎ በየግል እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡ ለተማሪዎችዎ እገዛና ማበረታታት አይለይዎት፡፡

# ምዕራፍ አስር

# የቤት እንሰሳት

(18 ክፍለ ጊዜ)

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምእራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ምንባብን አዳምጠው ከነባራዊው ሁኔታ ጋር ያዛምዳሉ፡፡ የፊደላትን ድምጾች ይጠራሉ፡፡
- ባለሶስት ቀለም ቃላትን ወደ ድምጾች በመነጠል መልሰው ያጣምራሉ፡፡
- ቃላትን በአዳዲስ ፊደላት ይጽፋሉ፡፡
- ቅጥያዎችን ይለያሉ፡፡

## 2. ዝርዝር ይዘቶች

- ትዕምርተ ድምጻዊ ግንዛቤ፡ ሞክሼ ፊደላት ( አ፣ ዐ ጸ፣ ፀ)
- ተዘውታሪ ቃላት (ትምህርታዊ)
- የቃላት እድገት
- ጽንሰ ሀሳባዊ ስያሜ
- አጫጭር ምንባቦችን ማንበብ፡ በትክክል፣ በፍጥነት፣ በጥሩ አገላለጽና በመረዳት፡፡

## 3. የመማር ማስተማር ብልሀቶችና መሳሪያዎች

*መምህር የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት መቀስቀስ፡፡ መምህር የተወሰኑ ሀሳቦችን ከሚደመጠው ምንባብ የሚያመለክቱ የቢጋር ሰንጠረዦችን ሞልቶ የተቀሩትን ክፍት መተው፡፡ ተማሪዎችም ክፍት ቦታ በመተው ምንባቡን በማዳመጥ የቢጋር ሰንጠረዡን ማሟላት፡፡*

***መለየት፡*** *መምህር በተመሳሳይ ድምጾች/ፊደላት የሚጀምሩ ወይም የሚጨርሱ ቃላትን እንዲጽፉ መጠየቅ፡፡ ከዚያም መምህር ሞዴል የሚሆኑ ቃላትን መጥራት፡፡ ተማሪዎች አምስት ድምጾችን በመነጠልና በማጣመር ለይቶ ማንበብ፡፡ (የድምጾችን/የፊደላትን (ቅርጽ፣ የባለቀለም ወረቀት፣ የካርቱን ስዕሎች፣ የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ ወዘተ መጠቀም)*

**መቁጠር፡** ተማሪዎች በአረፍተነገር ውስጥ ባሉ ቃላት፣ በቃል ውስጥ ባሉ ተመሳሳይ ቀለሞች፣ በቃላት ውስጥ ባሉ ድምጾች መጠን ማጨብጨብ፡፡

**ተመሳሳይ ድምጽ፡-** ተማሪዎች ተመሳሳይ ቀለም ያላቸውን ቃላት መጥራት፤መምህርም በሰሌዳ ላይ ምላሽ መስጠት፡፡

**ማጣመርና መነጠል፡** ተማሪዎች በቃሉ ውስጥ ያሉትን ድምጾች በመነጠል መናገር፡፡ (በፍጥነት ማስባል) በመቀጠል (መምህር መነጠልን ለማሳየት ፊደላትን ማጣመር)፡፡ ተማሪዎች ቃሉን ጠርተው በቃሉ ውስጥ ያሉትን ቀለሞችና ድምጾች መጥራት፡፡ (የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣ የባለቀለም ወረቀት፣ የካርቱን ስዕሎች፣ የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ ወዘተ መጠቀም)

**ቃላትን መመስረት፡** ተማሪዎች የቃላት ክፍሎችን በመጻፍ አዳዲስ ቃላትን መመስረት መለማመድ፡፡

**ተዘውታሪ ቃላት፡** በከፍተኛ ደረጃ ተደጋግመው የሚነገሩ ቃላትን ለማወቅ ልምድ ማዳበር

**ቀስበቀስ ማብቃት፡** ሀ. መምህር ፊደላትን በማሳየት መጥራት፡፡

ለ. መምህር ፊደላትን እያሳየ ተማሪዎችን ፊደላቱን እንዲጠሩ መጠየቅ፡፡

ሐ. ተማሪዎች ፊደላትንና ድምጾችን ማዛመድን መለማመድ፡፡

**እንቅስቃሴ፡** ድምጾችን ከእንቅስቃሴ ጋር ማገናኘት፡፡ ይህ ተማሪዎች አካላቸውን በማንቀሳቀስ ድምጾችንና ፊደላትን እንዲያስታውሱ ያግዛቸዋል፡፡

**አፋዊ እንቅስቃሴ፡** ተማሪዎች ድምጾች በአንደበታቸው ውስጥ እንዴት እንደሚፈጠሩ መማር፡፡

**መናገር፡** መምህር በቃላት ውስጥ ያሉ ድምጾችን እያሳዩ መጥራት፡፡ ከዚያም ድምጾቹን ማጣመር፡፡ (የታወቁ የፊደል ድምጽ ግንኙነቶችን መጠቀም)

**አርአያ፡** መምህር ተማሪዎች ካሏቸው የማንበብ ችሎታ በላይ የሚነበቡ ምንባቦችን በከፍተኛ ድምጽ ማንበብ፡፡

**ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ፡** ተማሪዎች ለተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ እንዲጋለጡ እድል መስጠት፡፡

**ቀስበቀስ ማብቃት ሞዴል፡** በአመልካች ጣትና መርህን ተከትለው በገደልማሚቶ ንባብ፣ በጋራ ንባብ፣ ከሌሎች ጋር አብሮ ማንበብ፡፡

## 4. ምዘና

- በተደጋጋሚ የሚከሰቱ ፊደላትን መቅረጽ
- ቃላዊና ጽሁፋዊ ጥያቄዎችን መጠየቅ፣
- አካላዊ ምላሽ፡፡
- ተማሪዎች አካላዊ ምላሽ በመጠቀም በግል የሚመልሷቸው ጥያቄዎች፣
- ኢመደበኛ ቁጥጥር፣
- ምልከታ፣
- በስዕል መወከል፣
- ተራ በተራ ማቅረብ፣
- ስልታዊ ልምምድ፣
- መውጫ ካርድ

**ክፍለጊዜ፡ አንድ**

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### ቅድመ ማዳመጥ

መምህር ዛሬ ተማሪዎች የሚያዳምጡት ትምህርት ርዕስ "የቤት አንሰሳት" በሚለው ምዕራፍ ውስጥ " የቤት እንሰሳ አይነቶች " የሚል ነው፡፡ በቅድሚያ የሚደመጠውን ታሪክ በንቃት እንዲከታተሉና ለማዳመጥ እንዲዘጋጁ ያድርጓቸው፡፡ ተማሪዎች በመጽሀፉ ላይ ያሉትን ስዕሎች አይተው ስለምን እንደሚያዳምጡ እንዲገምቱ መጠየቅ፣ ግምታቸውን ማጠናከር ወይም መለወጥ እንደሚችሉ ይንገሯቸው፡፡ የጽሀፉንም ርዕስ ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ተማሪዎቹ እንዲገምቱ ያድርጓቸው ፡፡ ወደ የሚደመጠው ምንባብ ከመግባቱ በፊት የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ለመቀስቀስ ከዚህ በታች ያለውን የቢጋር ሰንጠረዥ ሰሌዳው ላይ በመጻፍ ተማሪዎች የቤት እንሰሳት አይነቶችን የሚያሚላቸውን በቢጋር ሰንጠረዥ ላይ እንዲሞሉ ያድርጓቸው ፡፡

**የቢጋር ሰንጠረዥ**

| የቤት እንስሳት አይነቶችን ዘርዝሩ | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ድመት | ውሻ | በግ | ፍየል | በሬ |
| ላም | ፈረስ | በቅሎ | አህያ | ግመል |

የቀሩትን የቤት እንሰሳት አይነቶች ቢጋሩ ላይ ተማሪዎቹ እንዲሞሉ ያድርጓቸው፡፡

3. የመማሪያ ክፍላችሁ ምን ምን ይዟል?

> መምህር የሚደመጠውን ታሪክ በዝግታ ሁለቴ ደጋግመው ያንብቡላቸው፡፡ በጽሁፉ ውስጥ ከቀረቡት ቃላት ውስጥ አዳዲስና ከባድ ቃላትና ሀረጋት ይሆናሉ ብለው ያሰቧቸውን በቅድሚያ ፍቺ ይስጧቸው፡፡ በምንባቡም መሃል ንባቦትን ገታ አድርገው የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎችን ያቅርቡላቸው፡፡

**የቤት እንስሳት አይነቶች**

የቤት እንስሳት ከሰው ጋር አብረው የሚኖሩ ናቸው፡፡ በርካታ የቤት እንስሳት አይነቶች አሉ፡፡ የቤት እንሰሳትን በአይነት በአይነት ከፋፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ አንዳንዶቹ የቀንድ ከብቶች ናቸው፡፡ ለምሳሌ በሬና ላም፡፡ ሌሎቹ ደግሞ የጋማ ከብቶች ናቸው፡፡ እነሱም አህያ፣ ፈረስና በቅሎ ናቸው፡፡ ውሻና ድመትም በቤት እንስሳት ውስጥ ይመደባሉ፡፡

**(የማዳመጥ ጊዜ)** የቤት እንስሳት አኗኗራቸውን ግለጹ፡፡

የቤት እንስሳት አኗኗራቸው የተለያየ ነው፡፡ በሬና ላም በበረት ውስጥ ይኖራሉ፡፡ ፍየልና በግ ደግሞ በጉረኖ ያድራሉ፡፡ የጋማ ከብቶች በጋጣ ውስጥ ይታሰራሉ፡፡ ድመት ግን ከሰው ጋር በአንድ ቤት ውስጥ አብራ ትኖራለች፡፡

### ድህረ ማዳመጥ ጥያቄ

ማዳመጣቸውን የሚፈትሹ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡ ጥያቄዎችን በተናጥልና በተራ በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡

1. በሬና ላም የት ያድራሉ?
2. የበግና ፍየል ማደሪያ ምን ይባላል?

**ክፍለጊዜ፡ ሁለት**

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

መምህር በዚህ ክፍለ ትምህርት ተማሪዎች የቤት እንስሳት ለሰው ልጅ የሚሰጡትን አገልግሎት በመማሪያ መጽሀፉ ላይ ያሉትን ምስሎች በማየት የሚገልጹና የንግግር ክሂላቸውን የሚያዳብሩበት ነው፡፡ ስለዚህም በመማሪያ መጽሀፉ ላይ ያሉትን ምስል መሰረት በማድረግ በቅድሚያ እርሶ አጭር ንግግር በማድረግ በሞዴልነት ያስያዋቸው፡፡ ተማሪዎችዎም ያዩትን የንግግር አቀራረብ መሰረት አድርገው ተራ በተራ እጅ በማውጣት እንዲለማመዱ ያድርጓቸው፡፡ በንግግር ላይ ተማሪዎች የሚፈጽሙትን ስህተት በብልሀት ያርሟቸው፤፤ ጥረታቸውንም ያድንቁላቸው፡፡ተማሪዎች ንግግር አድርገው ሲጨርሱ ተማሪዎች በጭብጨባ እንዲያበረቷቷቸው ይዘዟቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ሶስት እስከ አስራስድስት**

# ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

መምህር ከክፍለጊዜ 3-16 ድረስ የቀረቡ ሞክሼ ፊደላትን (አ፣ ዐ፣ ፀ፣ ጸ እና ዘሮቻቸው) ድምጽና ቅርጽ አዋህዶ ለማስለየት በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡትን የፊደላት ቅርጽና ምስል ድምጽንም በመጨመር እንዲያዛምዱ ይርዷቸው፡፡ ይህንን ሲተገብሩ በቅድሚያ እርሶ ይስሩ፤ በመቀጠልም ከተማሪዎችዎ ጋር አብረው ይስሩ፤ በመጨረሻም ተማሪዎችዎ እራሳቸውን ችለው በተናጠል እንዲሰሩ ይርዷቸው፡፡ ተማሪዎች የሚያውቋቸው በተተኳሪ ሞክሼ ድምጾች የተመሰረቱ ቃላት እንዲጠሩልዎት ያድርጉና የተወሰኑትን ይምረጡላቸው፡፡ ከዚያም የተመረጡትን ቃላት በጋራና በተናጠል ያለማምዷቸው፡፡ ተማሪዎችዎ ተተኳሪ ሞክሼ ፊደሎች ያሉበትን ቃላት ሲጠሩ በማጨብጨብ ተተኳሪ ፊደሉን እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡ እባክዎ መምህር ተማሪዎቹ ይህንኑ ለተወሰነ ጊዜ እየደጋገሙ እንዲለማመዱ ያትጓቸው፡፡ በሁለም ተተኳሪ ድምጾች በቂ ምሳሌ በመስጠት ያለማምዱ፡፡ በተጨማሪም በየክፍለጊዜው የሚማሩትን ፊደላት ቅርጽ በባለቀለም ወረቀት ግድግዳ ላይ መለጠፍ፣ ፊደላትን ጎላ አድርጎ በሰንጠረዥ ማቅረብ፣ በካርቶን ላይ ፍላሽ ካርዶችን አዘጋጅቶ መጠቀም፡፡ ፍላሽ ካርዶችን ጠረጴዛ ላይ በታትኖ በማሰቀመጥ እንዲመርጡ ማድረግ፣ በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ከቀረቡት ቃላት በተጨማሪ ተማሪዎች ሌሎችን እንዲያፈልቁ ማበረታታት፣ አንድ ተማሪ ከሳጥን

ውስጥ ተራ በተራ ፍላሽ ካርድን እንደ እጣ በማውጣት፣ ያወጣውን ከፍ አድርጎ በማሳየት ሌሎች ተማሪዎች እንዲጠሩ በማድረግ ትምህርቱን ማቅረብ ይቻላል፡፡

መምህር ከመልመጃ አንድ እስከ ዘጠኝ ያሉት በቃል ውስጥ ያሉትን ድምጾች ወይም ፊደሎች በመነጠልና በማጣመር የተተኳሪ ሞክሼ ድምጾች ድምጻቸውንና ምልከታቸውን የሚለዩበት ነው፡፡ በዚህ መሰረት በቅድሚያ በቃል ውስጥ ያሉትን ድምጾች እየለዩ በሞዴልነት ያሳይዋቸው፡፡ በመቀጠል ከተማሪዎችዎ ጋር በመሆን በቃላት ውስጥ ያሉትን ድምጾች እየነጠሉና እያጣመሩ በመደጋገም በህብረት ይስሩ፡፡ በቃላት ውስጥ ያሉትን ድምጾች ሲነጥሉ በፊደሎቹ መጠን ተማሪዎች እንዲያጨበጭቡ ያድርጓቸው፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪዎች በቃል ውስጥ ስንት ፊደሎች እንዳሉ በቀላሉ በዜማ መልክ እንዲማሩ ይረዳቸዋል፡፡ ለምሳሌ "ሠበረ" በሚለው ቃል ውስጥ ሶስት ፊደሎች ስላሉ ተማሪዎች ሶስቴ እንዲያጨበጭቡ ያድርጓቸው፡፡ ከዚህ ልምምድ በኋላ ተማሪዎችዎ እራሳቸውን ችለው በግል እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡ የቀሩትን መልመጃዎች ተማሪዎቹም በመማሪያ መጽሀፉ ላይ ያሉትን ተግባራት እየሰሩ እንዲለማመዱ ይርዷቸው፡፡ የእርሶም እገዛና ክትትል እንዳይለያቸው፡፡

መምህር ከመልመጃ አስር እስከ አስራ ሁለት ያሉት በቃል ውስጥ ተለምዷዊ ቅጥያዎች ማስለየት ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ ይህን ሲተገብሩ አስቀድመው እርሶ በሞዴልነት ከቃላት ላይ ያሉትን ቅጥያዎች በመለየት ያመልክቷቸው፡፡ በመቀጠልም ይህንኑ ተግባር ከተማሪዎችዎ ጋር በህብረት ይስሩ፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎች በተናጥል እራሳቸውን ችለው እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡ በምሳሌው መሰረትም ተማሪዎች ተለምዷዊ ቅጥያዎችን ከለዩ በኋላ ቃሉን በትክክልና በፍጥነት እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡ በቃል ውስጥ ያሉትን ተለምዷዊ ቅጥያዎችን ሲለዩ በቅጥያዎች ብዛትም ተማሪዎችን በማስጨብጨብ በቀላሉ እንዲለዩ ያድርጉ፡፡ ምሳሌ፡ ፀዳች = ፀዳ-ች የሚለው ቃል አንድ ቅጥያ ስላለው አንድ ጊዜ በማስጨብጨብ ያሳይዋቸው፡፡ የቀሩትን መልመጃዎች ተማሪዎቹም በመማሪያ መጽሀፉ ላይ ያሉትን ተግባራት እየሰሩ እንዲለማመዱ ይርዷቸው፡፡ ይህንንም ተግባር በመደጋገም ያሰሯቸው፡፡ እገዛ ለሚፈልጉ ተማሪዎች እገዛ በማድረግ ከቃላት ውስጥ ተለምዷዊ ቃላትን በትክክልና በተገቢው እንዲለዩ ይርዷቸው፡፡ መልመጃዎችንም በደብተራቸው ላይ ጽፈው እንዲለማመዱ ይዘዟቸው፡፡ የተማሪዎችን ተሳትፎ ለማሳደግ ያበረታቷቸው፡፡

መምህር ትምህርቱን ተጨባጭ ለማድረግ ተለምዷዊ ቅጥያዎችን ለየብቻ በፍላሽ ካርድ አዘጋጅተው በቀኝና በግራ እጅ ወደ ላይ ከፍ አድርገው በመያዝ ከቃላት ጋር እየለዩ ያመልክቷቸው፡፡ ተማሪዎችም ይህንኑ ተግባር ተራ በተራ እየለዩ እንዲያመለክቱ ይርዷቸው፡፡ ተለምዷዊ ቅጥያዎችን በአካባቢ በሚገኙ ቁሳቁሶች ሰርተው እንዲመጡ የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡

መምህር በክፍለጊዜ አስራ አራት እስከ አስራ ስድስት የሚገኙት አጫጭር ምንባቦች በስዕል የተደገፉ ናቸው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ስዕሉን እያዩ ምንባቡን እያነበቡ የምንባቡን መልዕክት እንዲረዱ ያግዟቸው፡፡ ይህን ተግባር ለመተግበር በቅድሚያ እርሶ ድምፆን ከፍ በማድረግ እያነበቡ ያሳይዋቸው፡፡ በመቀጠል ተማሪዎች በተገቢው ፍጥነት እንዲያነቡ ይርዷቸው፡፡ ምንባቡን ሲያነቡ ቃላትን በትክክል እንዲጠሩ ይከታተሏቸው፡፡ ይህን ተግባር እያንዳንዱ ተማሪ በግል እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡ ተማሪዎችዎንም ያድንቋቸው፡፡ ስህተታቸውንም በብልሀት ያርሟቸው፡፡

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

# ትምህርት አራት፡ ቃላት

መምህር በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ ተማሪዎች የቋንቋ ክሂላቸውን የሚያዳብሩበት፤ የቃላት እውቀታቸውን የሚያሳድጉበት ክፍል ነው፡፡ የቃላት እውቀት ለማዳመጥ፣ ለመናገር ፣ ለማንበብና ለመጻፍ ክህሎት አስፈላጊ መኑን ለተማሪዎችዎ ያስገንዝቧቸው፡፡ ተማሪዎች የቃላት እውቀታቸውን ለማዳበር ከሚደረጉ መልመጃዎች አንዱ ለቃላት የቁም ፍቺ እንዲሰጡ ማድረግ ነው፡፡ ቃላት ለብቻቸው ከአረፍተነገር ውጭ ሲሆኑ የተለያዩ ፍቺ ሊሰጡ እንደሚችሉ በምሳሌ በማስደገፍ ያስረዷቸው፡፡ በመቀጠል የተወሰነ የቃላትን ፍቺ ከተማሪዎችዎ ጋር በህብረት ይስሩ፡፡ በመጨረሻም እያንዳንዱ ተማሪ በመማሪያ መጽሀፋቸው ላይ በመልመጃ አስራ ሁለት ያለውን ጥያቄ እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡ ለተማሪዎችዎ ቅርብ ክትትል እያደረጉ ጥረታቸውን በማድነቅ እገዛ ለሚፈልጉ ተማሪዎች እገዛ ያድርጉላቸው፡፡ በመጨረሻም ትክክለኛውን መልስ በሰሌዳ ላይ በመጻፍ እርማት እንዲወስዱ ያድርጓቸው፡፡

**መልመጃ፡ አስራ ሁለት**

**ለሚከተሉት ቃላት ፍቺ ስጡ፡፡**

1. ፍቺ= ትርጉም/ ገለጻ/...
2. ቅጥያ= ተጨማሪ/ ተደራቢ/ተቀጽላ...
3. ነጠለ= ለየ/ አወጣ/ ከፋፈለ....
4. አጣመረ= አገናኘ/ አያያዘ/አዋሀድ/ደረበ...
5. መሰረተ= መነሻ/ ወለል/መጀመሪያ...

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

# ትምህርት አምስት፡ ጽሕፈት

መምህር በትምህርት አስራ ስምንት፣ ጽሕፈት ስር ተማሪዎች ከቃላት ውስጥ የሚገቡትን ፊደላት እየነጠሉና እያጣመሩ የድምጾችን ትዕምርት በትክክል የሚጽፉበት መልመጃ የተዘጋጀ ነው፡፡ ስለዚህም በቅድሚያ የተወሰኑ ቃላት ወስደው በሞዴልነት እየነጠሉና እያጣመሩ ያሳይዋቸው፡፡ ይህንንም ልምምድ ይደጋግሙላቸው፡፡ በመቀጠል ከተማሪዎችዎ ጋር በህብረት በተለያዩ ቃላት የመነጠልና የማጣመር ተግባር ያከናውኑ፡ ከበቂ ልምምድ በኋላ በመማሪያ መጽሀፉ ላይ በመልመጃ አስራሶስት በ"ሀ" እና "ለ" የተቀመጡትን ጥያቄዎች ተማሪዎች በደብተራቸው እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡ የተማሪዎችን ትጋት ያድንቁላቸው፡፡ እገዛ ለሚሹ እገዛ በማድረግ የተማሪዎችዎን የቃላት እውቀት ያዳብሩ፡፡ ከተማሪዎችዎ ሙከራ በኋላ ትክክለኛውን መልስ በሰሌዳ ላይ በመጻፍ ተማሪዎችዎ እርማት እንዲወስዱ ይዘዟቸው፡፡

**መልመጃ፡ አስራ ሶስት**

**ሀ.ፊደላትን ነጣጥላችሁ ጻፉ፡፡**

ምሳሌ፡ ድመት= ድ መ ት

1. አበጀ= አ በ ጀ
2. ፈረስ= ፈ ረ ስ
3. ፀደቀ= ፀ ደ ቀ

**ለ.ፊደላትን አጣምራችሁ ጻፉ፡፡**

ምሳሌ፡ በ ረ ት= በረት

1. በ ቅ ሎ= በቅሎ
2. ፅ ዳ ት= ፅዳት
3. ግ መ ል= ግመል

# አማርኛ እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ አንደኛ ክፍል መርሀ ትምህርት

## መግቢያ

በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ በትምህርት አሰጣጥ ፈጣንና መሻሻል በታየበት ሁኔታ እየሰራች ነው፡፡ ልዩ ትኩረት የተሰጠው "ጥራቱ የተጠበቀና እኩል ተደራሽነት ያለውን ትምህርት ለሁሉም ማዳረስ" ላይ ነው፡፡ ይኸውም ለ21ኛው ክፍለ ዘመን እድገት እንደመሳሪያ ሆኖ በብቃት ህብረተሰቡን ወደ ፊት የሚያራምድ ነው፡፡ ይህንን ግብ ለማሳካት ትምህርት ሚንስቴር የነበረውን ክፍተት ለመሙላት ምርምሮችን በማድረግ አዲስ ስርዓተ ትምህርትን ቀርጿል፡፡ በዚህም የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት መሳሪያዎቹ (የይዘት ፍሰት፣ አነስተኛ የመማር ብቃትና መርሀ ትምህርት) በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ስርኣተ ትምህርት ማእቀፍ ውስጥ ተመስርተው እንዲዘጋጁ ተደርገዋል፡፡ እነዚህ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት መሳሪያዎች ዋና መነሻቸው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ልህቀትን ለማሻሻል ሲሆን በአውድ የተደገፈ፣ በህጻናት እድገት ላይ በተደረገው የምርምር ማስረጃና በመማር ላይ የተመሰረተ ትምህርታዊ ስኬታማነትን እንዲያረጋግጡ ተደርገው ተቀርፀዋል፡፡ በአውዱ የተሰጡት መነሻ ልምምዶችም የተማሪውን መማር የመጨረሻ ግብ የሚያሳድጉ ናቸው ተብሎ ይታሰባል፡፡ የስርዓተ ትምህርት መሳሪዎች በዋናነት እንዲቀረፁ የተደረጉት የመማር ውጤት፣ ብቃት፣ ይዘት፣ የመማር ስልቶች፣ ምዘናና ለእያንዳንዱ ይዘት ጊዜ በመስጠት ነው፡፡

መርሃ ትምህርቱ የተለያዩ አገር በቀል እውቀቶችን፣ ዋና ዋና ክሂሎችን፣ ለህይወት አስፈላጊ የሆኑትንና ብርቱ ብሄራዊ ጉዳዮችንና ብቃቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት ተዘጋጅቷል፡፡

ይህም በብሄራዊና በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ ብቁ ዜጋ ለማፍራት ታስቦ የተሰናዳ ነው፡፡ የይዘቱ ፍሰትም ከቀላል ወደ ውስብስብ፣ ከሚታወቅ ወደ ማይታወቅ፣ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሚሄድ ሆኖ ተማሪዎቹ አውዳዊ ይዘቱን እንዲረዱ የሚያስችል ነው፡፡ መልመጃዎቹ ተማሪ ተኮር የሆኑ፣ አብዛኛውን እድል ለተማሪዎች የሚሰጡ፣ የታሰበውን የቋንቋ ክሂል ተለማምደው እንዲያሳድጉ የሚያስችሉ ሆነው በደረጃቸው የቀረቡ ናቸው፡፡

በዚሁ መሰረት የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ በክልሉ ለሚገኙ አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ ለፈቱ ተማሪዎች ይህን በትምህርት ሚኒስቴር የቀረበ ስርዓተ ትምህርት ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ አስማምቶ አቅርቦታል፡፡

## የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት ግቦችና አላማዎች

## የአፍ መፍቻ ቋንቋ የማስተማር ግቦች ፡-

- ከቅድመ አንደኛ ደረጃ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ያለውን የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት በስኬታማነት ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎቹ ቀጥለው ያሉትን ግቦችና አላማዎች እንዲያሳኩ ይጠበቃል፡፡

## ግቦች

- የመሰረታዊ ፊደላትን ክሂል ማበልጸግ የተማሪውን አእምሮታዊ፣ ስሜታዊና ማህበራዊ ክሂሎችን ለማሳደግ አስተዋጽኦ ያደርጋል፤
- ተማሪዎችን የቋንቋ ክህሎትና ስነልሳናዊ እውቀት ማስተዋወቅ ለተግባቦት ብቃት ማዳበር ስለሚያግዛቸው ሀሳባቸውንና ስሜታችውን በተለያዩ አውዶች ውስጥ ለመግለጽ ይረዳቸዋል፤
- ተማሪዎቹን አገር በቀል እውቀትና እሴቶችን እንዲያውቁ ስለሚያደርጋቸው በተለያዩ ማህበራዊ አውዶች ውስጥ እንዲጠቀሙባቸው ያስችላቸዋል፡፡

## <u>አላማዎች</u>

## የአፍ መፍቻ ቋንቋ ማስተማርና የመማር አበይት አላማዎች፡-

- መሰረታዊ ትምህርትን በማዳበር ተማሪዎች ለወደፊት የትምህርት ግባቸው ዝግጁ እንዲሆኑ ጽናት ይሰጣቸዋል፤
- የቋንቋውን ዋና ዋና ክሂሎች መረዳት የተግባቦት ችሎታቸውን ለማሳደግ እና ሀሳባችውንና ስሜታቸውን ውጤት ባለው መንገድ ለመግለጽ ይረዳቸዋል፤
- የቋንቋውን ንዑሳን ክሂሎች ማወቅ የተግባቦት ችሎታቸውን ለማዳበር እንደሚረዳቸው እንዲገነዘቡ ያደርጋቸዋል፤
- ከሳይንሳዊ ምርምር የተገኙትን የቋንቋና የስነልሳን ባህሪያት እንዲረዱ ያደርጋቸዋል፤
- የቋንቋ አጠቃቀምን በትምህርት፣ በማህበራዊ ኑሮና በምጣኔ ሀብት ሁነቶች ውስጥ እንዲያዳብሩ ያስችላቸዋል፤

- የአገር በቀል ቋንቋ ስልቶችን በተለያዩ የቋንቋ ይዘቶች በማቅረብ እንዲያሳድጉ ይረዳቸዋል፡፡

## ራዕይና እሴቶች

### ራዕይ

የአፍ መፍቻ ቋንቋ መማርና ማስተማር ለአለም ቋንቋዎች ሁሉ ዋጋ ይሰጣል ተብሎ ስለሚጠበቅ እያንዳንዱ ሰው በተለይም ህጻናት ቋንቋውን መናገር ብቻ ሳይሆን መማር በመቻል ያንን ቋንቋ በቀላሉ ይረዳሉ፡፡ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በአፍ መፍቻ ቋንቋ ጠንካራ መሰረቶች የሚኖሩ ከሆነ ተማሪዎች በተሻለ መንገድ ስርዓተ ትምህርቱን እየተረዱ እንደዚሁም አዎንታዊ አመለካከት ኖሯቸው ወደ ትምህርት ቤት ይሄዳሉ፡፡ ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ከህጻንነታቸው ጀምሮ ጠበቅ አድርገው ማወቃቸው አስፈላጊ በመሆኑ በየክፍል ደረጃው የተሻለ ጥረት በማድረግ ለውጥ ማምጣት ይችላሉ፡፡

የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት የህጻናት አእምሮ ብስለትን በማሳደግ የቋንቋ ክሂሎችን፣ ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶችንና ሌሎች ትምህርቶችን ለመማር ይረዳቸዋል፡፡ ይህን እሳቤ ውስጥ በማስገባት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ተምረው ያለፉ ኢትዮጵያዊ ተማሪዎች በሰላምና በመተሳሰብ አብሮ በመኖር ፡-

- ብቃት ያለው የቋንቋ ክሂል ባለቤት፣ ባህልንና ማንነትን አክባሪ፣ የማሰብና የመፍጠር ባለቤት፣ በራስ የሚተማመኑ፣ ችግር ፈቺዎች፣ ትጉኃን፣ ትኩረት ሰጪዎች፣ ምክንያታዊያን ተባባሪና ራስን በመስጠት የሚሰሩ ይሆናሉ፤

### እሴቶች

እሴቶች አስፈላጊና ፍትሃዊ ስለሆኑ ነገሮች ያሉን እምነቶች ናቸው፡፡ እሴቶች ድርጊታችንንና ውሳኔያችንን ይመራሉ፤ ስለዚህ ይህ ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት የተዘጋጀው ጽሁፍ ተማሪዎቹ፡-

አገር በቀል እወቀቶችን አክባሪና ተጠቃሚ፣ የህብረተሰቡን የግጭት አፈታት ባህሎችን የሚተገብሩ፣ የስርዓተ ጾታ እኩልነትን ተግባራዊ የሚያደርጉ፣ የመረዳዳት መንፈስ ያላቸው፣ የመቻቻል ባህል የተላበሱ፣ ብሄራዊና አለማቀፋዊ ቅርስ የሚንከባከቡ፣ በልዩነት ውስጥ አንድነት የሚቀበሉ፣ እርስ በእርስ የሚከባበሩ፣ ጠንክሮ የመስራት ባህል ያላቸው፣ በላቀ ሁኔታ የሚያስቡ፣ የፈጠራ ችሎታን የተላበሱ፣ ችግር ፈቺዎች፣ ስለአካባቢ ጥበቃ የሚያስቡ እንዲሆኑ የሚያበረታታ መሆን አለበት፡፡

# የአንደኛ ክፍል የአንደኛ ወሰነ ትምህርት መርሃ ትምህርት

**ምዕራፍ አንድ፡ ቤተሰብ (18 ክፍለ ጊዜ)**

**የሚጠበቁ ውጤቶች**

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- መምህር ስለ ሀትመት ግንዛቤ የሚያደርገውን ገለጻ ካዳመጡ በኋላ ለጓደኞቻቸው ሀሳቦችን ያጋራሉ፡፡
- ተዘውታሪ ቃላትን ይጠቅሳሉ፡፡
- አዳዲስ ድምጾችን/ፊደላትን ይለያሉ፡፡
- ሁሉንም ፊደላት በቅደም ተከተላቸው አስተካክለው ያስቀምጣሉ፡፡
- የእርሳስና የብዕር አያያዝን ይማራሉ፡፡

| ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| የህትመት ግንዛቤን መግለጽ<br><br>መጽሀፍ፣ ብዕርና እርሳስ በአግባቡ መያዝ፤<br><br>በቋንቋ ውስጥ ሶስት ተዘውታሪ ድምጾችን/ፊደላትን መለየት(ሀ፣ ለ፣ መ)፤<br>ተዘውታሪ ቃላትን መጥቀስ | **የህትመት ግንዛቤን ማዳመጥና መናገር፡-**<br><br>**የንግግር ድምጾች ግንዛቤ፡-**<br>የተመረጡ ሦስት ድምጾች/ፊደላት<br><br>**የትምዕርተ ድምጽ ግንዛቤ፡**<br>የተመረጠ ድምጽና የፊደሉ ግንኙነት<br><br>**የቃላት ጥናት፡** | **መምህር** የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ይፈትሻል (ከማዳመጣቸው በፊት መምህር የህትመት ግንዛቤ ጥያቄዎችን ማቅረብ)፡፡<br>**ተማሪዎች፡-**የቀደመ ዕውቀታቸውን ያንጸባርቃሉ፡፡<br>**መምህር፡** ተማሪዎች የተመለከቱትን ርዕስ፣ ስዕሎችና ቁልፍ ቃላትን መሰረት አድርገው ስለምን እንደሚያዳምጡ እንዲገምቱ መጠየቅ እና የተማሪዎችን የመማሪያ መጽሀፍ በመያዝ ስለመጽሃፉ ክፍሎች የሚያስረዱ ቃላት (ርዕስ፣ ሽፋን) መናገር፡፡<br>**ተማሪዎች፡** የጽህፈትን አቅጣጫ ይከተላሉ (ከግራ ወደ ቀኝ፣ ከላይ ወደታች፣ ስለመጽሀፍ ፣ ስለ ብእርና እርሳስ አያያዝ ይጠነቀቃሉ)፡፡ ስለህትመት ግንዛቤ ለመጨበጥ ከጓደኞቻቸው ጋር ይሰራሉ፤ ስለቤተሰቦቻቸው የሚያስረዱ ጥያቄዎችን መመለስ፡፡ የቤተሰብ አባላትን በዛፍ ስዕል መልክ ስለው ማስቀመጥ (የተማሪዎችን የመማሪያ መጽሃፍ ተጠቀም)፡፡<br>**መምህር፡** በተመሳሳይ ድምጾች የሚጀምሩ ቃላትን እንዲናገሩ መጠየቅ ፡፡ (ድምጾችን/ ፊደላትን፣ የቃላት ካርዶችን፣ ባለቀለም ወረቀቶችን፣ ካርቱን ምስሎችን እና ወዘተ ምስሎችን መጠቀም፡፡<br>**ተማሪዎች፡** ሁለት ቃላት በተመሳሳይ ድምጽ በመነሻ ወይም በመድረሻ የሚጀምሩ ወይም የሚጨርሱ መሆናቸውን መለየት፡፡<br>**መቁጠር፡** ተማሪዎች በቃላት ውስጥ ባሉት ድምጾች ብዛት መጠን ማጨብጨብ፡፡ (የቃላት ካርድና ጥቁር ሰሌዳን መጠቀም)<br>**ተመሳሳይ የድምጽ ቃና፡** ተማሪዎች ተመሳሳይ የድምጽ ቃና ያላቸውን ቃላት መፍጥር፤ መምህር | የቃል ጥያቄዎችን መጠየቅና ምላሽ መስጠት (በህትመት ግንዛቤ ላይ)<br>አካላዊ ምላሽ፣<br>ተማሪዎች በግል የሚሰጡት አካላዊ ምላሽ፣<br>ኢ-መደበኛ ቁጥጥር፣<br>ምልከታ፣<br><br>በሚታይ ነገር መወከል፣<br>ሚና መለዋወጥ፣<br>የመውጫ ካርዶች፣<br>ጽብረቃ፣<br>ስልታዊ ልምምድ፣<br>ድምጽን/ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ተዘውታሪ ቃላት(የትምህርት ቃላት) የቃላት እድገት<br><br>**ማንበብና መጻፍ:**<br>ድምጾችን ማንበብና መጻፍ<br><br>**ማንበብ:**<br>በተገቢ አገላለጽ፣ በፍጥነት፣ በትክክለኛነትና በመረዳት<br>**መጻፍ:**<br>በትክክል መጻፍ<br>**ድምጸታዊ ግንዛቤ:**<br>ዘወትር የሚታወቅ ድምጽ | የተማሪዎችን ምላሽ በሰሌዳ ላይ መጻፍ (የቃላት ካርድና ሰሌዳ ተጠቀም)<br>ተዘውታሪ ቃላት፡ መምህር ተዘውታሪ ቃላትን ትርጉም በቡድን በመወያየት መስጠት፡፡<br>ተማሪዎች ከሚደመጡ ጽሁፎች ጋር ለማዛመድ መሞከር ይፈልጋሉ፡፡<br>**ቀስ በቀስ ማብቃት፡**<br>ሀ.መምህር ፊደላትን ይጠራል<br>ለ.መምህር ተማሪዎችን ፊደላቱን እንዲጠሩ ይጠይቃል<br>ሐ.ተማሪዎች ድምጾችንና ፊደላትን ማገናኘት ይለማመዳሉ፡፡<br>**እንቅስቃሴ፡** በእንቅስቃሴ ድምጾችን ያገናኛሉ፡፡ ይህ ተማሪዎች አካላቸውን እንዲያንቀሳቅሱ ይጠይቃል፡፡<br>**የአፍ እንቅስቃሴ፡** ይሄ ተማሪዎች ድምጾች እንዴት እንደሚፈጠሩ ያስተምራቸዋል፡፡<br>**መጻፍ፡**<br>ሀ.መምህር ድምጾችን መጥራት ከዚያም ማጣመር ፡፡ (የታወቁ የፊደላት ድምጾችን)<br>ለ. ተማሪዎች፡ ፊደላትን ከድምጾቻቸው ጋር (በ ሰሌዳ፣ በቃላት ካርድ ላይ) ማገናኘት፡፡<br>**አርአያ መሆን፡**<br>መምህር ከተማሪዎች በተሸለ ሁኔታ ድምጹን ከፍ በማድረግ በትክክል ለተማሪዎች ማንበብ፡፡<br>**ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ፡** ተማሪዎች ቃላዊ ንባብን እንዲከውኑ እድል መስጠት ፡<br>**አርአያ በመሆን ማንበብን ለተማሪዎች ቀስበቀስ መተው፡** ጣትን በመጠቆም በገደል ማሚቶ፣ በጋራ ማንበብ፣ በጥንድ ድምጽን ከፍ አድርጎ ማንበብ፣ ድምጾችንና ፊደላትን በመንካት ማገናኘት፡፡<br>**የተመረጡ ፊደላትን ማሳየት**<br>**በአየር ላይ መጻፍ፡**<br>**ተማሪዎች** ፊደላትን በአየር ላይ ወይም በወረቀት ላይ በአመልካች ጣታቸው መፃፍ፡፡<br>**መምህር፡** የፊደላትን ወይም የድምጾችን ስም መናገር ፡፡<br>**ተማሪዎች፡** ደግሞ በአየር ላይ ወይም በወረቀት ላይ በጣታቸው መጻፍ፡፡<br>**ተማሪዎች፡** ቤተሰባዊ ዝምድና ያላቸውን ቃላት መጥራት ቃላትን ቤተሰብ በዛፍ ስዕል መልክ | ፍደላትን የመለየት ጥያቄ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ጽፈው ማሳየት፡፡<br>**ቅድመ መጻፍ ተግባራት፡** ከመጻፍ በፊት የሚከሰቱ ተግባራትን ማስቀመጥ<br>**መምህር፡** ድምጸችን ወይም ፊደላትን ለልምምድ በርካታ ቃላትን ቃላዊ በሆነ መንገድ ማቅረብ ፡፡<br>**ተማሪዎች፡** መምህር ያቀረበውን በርካታ መንገድ ተጠቅመው ፊደላትን ወይም ድምጸችን ይለያሉ፡፡ | |

**ምዕራፍ ሁለት፡ ቤት (18 ክፍለ ጊዜ)**

**ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ምንባቡን አዳምጠው መልዕክቱን ይረዳሉ፡፡
- በቤታቸው ያሉ የተለያዩ ቁሳቁሶችን ጠርተው ቅርጻቸውን ያሳያሉ(ይረስሳሉ)፡፡
- መሰረታዊ ቅርጾችን ይረስሳሉ፡፡
- አዳዲስ ድምጾችን/ፊደላትን ያነባሉ፡፡
- ድምጾችን ከምልክቶቻቸው ጋር ያዛምዳሉ፡፡
- ባለሁለት ቀለም ቃላትን ይጽፋሉ፡፡

| ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • ምንባቡን ማድመጥና የተረዱትን መልክት መግለጽ<br>• በቤታቸው የሚገኙትን የተለያዩ መሳሪያዎች ስም መጥቀስ<br>• መሰረታዊ ቅርጻቸውን ማመልከት<br>• አዳዲስ ድምጾችን/ምልክተቶችን (አምስት የተመረጡ ፊደላትን/ድምጾችን) ማንበብ (ሠ፣ ረ፣ ሸ፣ ቀ፣ በ)<br>• የፊደላትን ድምጸት | **ማነቃቃት፡** ለምዕራፍ ሁለት አምስት ድምጾችን መምረጥ<br>**የትዕምርተ ድምጻዊ ግንዛቤ፡**<br>የተመረጡ የፊደል ድምጾች ግንኙነት፡ ተመሳሳይ ቀለሞች ያሏቸውን ቃላት ሲጠሩ ያጨበጭባሉ፡፡<br>**የቃላት ጥናት፡** ተዘውታሪ ቃላት(የትምህርት ቃላት) የቃላት | መምህር ስለ መሰረታዊ ቅርጾች ምልክት ጥያቄ መጠየቅ<br>**መገመት፡** ተማሪዎችን ርዕሱን፣ ስዕሎችን፣ ቁልፍ ቃላትን ተመልክተው ስለ ምን እንደሚያዳምጡ መጠየቅ፣ መምህር መሰረታዊ ቅርጾችን በሰሌዳ ላይ መጻፍ፡፡ ከዚያም በአየር ላይ ቅርጾችን በመጻፍ ማሳየት፡፡ (ስዕሎችን የድምጾችን /ፊደላትን ቅርጽ፣ የቃላት ካርድ፣ ባለቀለም ወረቀት፣ ካርቱን ምስሎች፣ ሰሌዳ ወዘተ መጠቀም)<br>ከዚያም ቅርጾችን በአየር ላይ ጣቶቹን በአየር ላይ ማመልከት፡፡ (እራስን የማስቻል ሞዴል መከተል)<br>**መምህር፡** ተማሪዎች ሶስት በተመሳሳይ ድምጽ የሚጀምሩ ወይም የሚጨርሱ ቃላትን እንዲያቀርቡ መጠየቅ፡፡ (የድምጾችን ወይም ፊደላትን ቅርጾች ወይም የቃላት ካርድ፣ ባለቀለም ወረቀት፣ ካርቱን ስዕሎች፣ ሰሌዳ ወዘተ)<br>ተማሪዎች በተመሳሳይ ድምጽ የሚጀምሩ ወይም የሚጨርሱ ሶስት ቃላትን መለየት፡፡ | የምንባቡን ዋና ይዘት በቃል/ በጽሁፍ ጥያቄዎችን በመጠየቅ፣ ግብረ መልስ መስጠት፤ መሰረታዊ ቅርጾችን እንዲጽፉ መጠየቅ፤<br>ለጥያቄዎች የሚሰጡት ምላሽ፤ መሰረታዊ ቅርጾችን ሲጽፉ ኢ-መደበኛ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ማዛመድ<br><br><br>• ተዘውታሪ ባለሁለት ቀለም ቃላትን መጻፍ | እድገት<br><br>**ማንበብና መጻፍ:** ድምጾችን ማንበብና መጻፍ<br><br>**ማንበብ:** ድምጾችን ከሚወክሏቸው ፊደላት ጋር በማገናኘት በትክክል ማንበብ<br><br>**በትክክል መጻፍ:** መሰረታዊ ምልክቶችና ቅርጾች<br><br>**ድምጸታዊ ግንዛቤ:** የታወቁ የድምጸት ደረጃዎች | **መቁጠር:** ተማሪዎች በቃላት ውስጥ ባሉ የድምጾች መጠን ያህል ያጨበጭባሉ፡፡<br>**መምህር:** ተማሪዎች በተመሳሳይ ድምጽ የሚጨርሱትን ቃላት እንዲናገሩና ዜማ እንዲኖረው ማድረግ፤<br>**ተማሪዎች:** በተመሳሳይ ድምጽ የሚጨርሱትን ቃላት ቤተሰብ ማመንጨትና መምህር ደግሞ የተማሪዎችን ምላሽ በሰሌዳ ላይ መጻፍ፡፡ (በግድግዳ ላይ የተጻፉ ቃላት)<br>**ቀስበቀስ ማብቃት:**<br>ሀ. መምህር ፊደላትን አድምቆ በማሳየት ድምጸታቸውን መጥራት ፡፡<br>ለ.መምህር ተማሪዎቹ ያደመቁትን ፊደላት በማሳየት የፊደላቱን ድምጸት እንዲሉ መጠየቅ ፡፡<br>ሐ.ተማሪዎች የደመቁትን ፊደላትና የሚወክሏቸውን ድምጾች ማዛመድ መለማመድ፡፡<br>**የመምህር አርአያነት:** ድምጾችን ከእንቅስቃሴዎች ጋር ማዋሀድ፡፡ ይህ ተማሪዎች አካላዊ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ድምጾችንና ፊደላትን እንዲያስታውሱ ይረዳል፡፡<br>**የአፍ እንቅስቃሴ:** ተማሪዎች በአንደበት አካላቸው ውስጥ ድምጾች እንዴት እንደሚፈጠሩ መማር፡፡<br>**ቃላትን መመስረት:** ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን ከአዳዲስ የቃል ክፍሎች ጋር ማንበብ ይለማመዳሉ፡፡<br>**ተዘውታሪ ቃላት:** መምህር በምንባቡ ውስጥ ተዘውታሪ ቃላትን በማሳየት ተማሪዎቹ የቃላቱን ትርጉም በቡድን ሆነው መስጠት<br>**ማንበብ:**<br>ሀ.መምህር ቃላትን በማሳየት፣ በቃላት ውስጥ ያሉትን ድምጾች መጥራት፡፡ ከዚያም ድምጾችን መነጠል፡፡ (በጉልህ የታወቁ ድምጾችን መጠቀም)<br>ተማሪዎች ሁሉንም ድምጾች በመነጠልና በማጣመር ይለያሉ፡፡<br>**አርአያ:** መምህር ከተማሪዎች በተሻለ ደረጃ ምንባብን ጮክ ብሎ ማንበብ፡፡ | ቁጥጥር ማድረግ፡፡<br><br>ምልከታ፣<br><br>በሚታይ ነገር መወከል፣<br><br>ተራ በተራ ማቅረብ፤ ስልታዊ ልምምድ፤ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | **ተደጋጋሚ የቃል ንባብ፡**<br>ተማሪዎች ለተደጋጋሚ የቃል ንባብ በመጋለጥ በትክክል የማንበብ ችሎታቸውን ያሳድጋሉ፡፡<br>**ቀስበቀስ ማብቃት፡**<br>በጣታቸው በማመልከት የገደል ማሚቶ የጋራ ንባብ፣ ግላዊ ንባብ በመጋራት ማንበብ፡፡<br>**መምህር፡** ቃላትን በመጠቀም ድምጾችን /ፊደላትን ለመለማመድ በርካታ እድሎችን መፍጠር፤<br>**ተማሪዎች፡** በርካታ ድምጾችን ፊደሎችን ለመለየት በርካታ ዕድሎችን መጠቀም፤ የተመረጡ ፊደላትን/ድምጾችን መቅረጽ፤<br>**በአየር ላይ መጻፍ ፡**<br>**መምህር፡** የፊደላቱን ስም መጥራት፡፡<br>**ተማሪዎች፡** በጣታቸው በአየር ላይ ወይም በመጻፊያ ነገር ላይ ፊደላትን መቅረጽ፡፡ ከዚያም ተማሪዎች በአመልካች ጣታቸው በአየር ላይ ወይም በመጻፊያ ነገር ላይ ፊደላቱን መጻፍ፡፡ | |

**ምዕራፍ ሶስት፡ ትምህርት ቤት** (18 **ክፍለ ጊዜ**)

**ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ምንባብን በማዳመጥ ተዘውታሪ ቃላትን ይጠራሉ፡፡
- አዳዲስ ድምጾችን/ፊደላትን ያነባሉ፡፡
- አዲስ የድምጽ- ፊደል ተዛምዶን ይፈጥራሉ፡፡
- ተዘውታሪ ባለሶስት ቀለም ቃላትን ይጽፋሉ፡፡

| **ብቃቶች** | **ይዘቶች** | **የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች** | **ምዘና** |
|---|---|---|---|
| ምንባብን አዳምጦ መልእክቱን መረዳት<br><br>አዳዲስ አምስት ፊደላትን/ድምጾችን ማንበብ (ተ፣ ቸ፣ ነ፣ ኘ፣ አ) ድምጾችን መነጠልና ማጣመር፤ ለተለመዱ ቃላት ፍቺ መስጠት፤ አዲስ የፊደል- ድምጽ ተዛምዶን መፍጠር፤<br>• ድምጾችን መነጠልና ማጣመር<br>• ተዘውታሪ ቃላትን ፍች መስጠት<br>• አዲስ የፊደል- ድምጽ ተዛምዶን መፍጠር | ማዳመጥና መናገር<br><br>ስነድምጻዊ ግንዛቤ የተመረጡ አምስት ድምጾች/ከምዕራፍ ሁለት በኋላ ተከትለው የሚመጡ ፊደላት ትዕምርተ ድምጻዊ ግንዛቤ የተመረጡ የፊደል ድምጽ ግኑኙነት የቃላት ጥናት ተዘውታሪ (የትምህርት) ቃላት -የቃላት እድገት የጽንሰ ሀሳብ ስያሜ ማንበብና መጻፍ፡ ድምጾችን ማንበብና መጻፍ ማንበብ፡ ድምጾችን ከፊደላት ጋር አዛምዶ ፣ በፍጥነትና በጥሩ አገላለጽ ማንበብ | **መምህር**፡ ርዕሶችን፣ ስዕሎችንና ቁልፍ ቃላትን በመጠቀም ምንባቡ ስለ ምን እንደሚያወሳ እንዲገምቱ የተማሪዎችን የቀደመ ዕውቀት ለመቀስቀስ መጠየቅ፡፡ እንዲሁም ከትምህርት ቤት ቁሳቁሶች ጋር የተገናኙ ቃላትን ትርጉም መለየት፡፡<br>መምህር ተማሪዎች በተመሳሳይ ድምጽ የሚጀምሩና የሚጨርሱ ቃላትን እንዲዘረዝሩ ማድረግ፡፡ ተማሪው ቃላቱ በተመሳሳይ ድምጽ የሚጀምሩና የሚጨርሱ መሆናቸውን በማረጋገጥ የድምጾቹን አጠራር መለየት፡፡<br>**መቁጠር፡**<br>ተማሪዎች በቃላት ውስጥ ባሉ ድምጾችና ቀለማት ልክ ያጨበጭባሉ (ስዕሎችን፣ የፊደል ካርዶችን፣ ቀለማዊ ወረቀቶችን፣ የካርቱን ምስሎችንና ሰሌዳን ወዘተ መጠቀም፡፡<br>**ተመሳሳይ ዜማ፡** መምህር ለተማሪዎች በተመሳሳይ ቀለም የሚጨርሱ ቃላትን ማቅረብ፡፡ ከዚያም መዝሙሮችን በቃላት መፍጠር፡፡ ተማሪዎች ተመሳሳይ የመጨረሻ ቀለሞች ያሏቸውን ቃላት ቤተሰብ መፍጠር፡፡ ከዚያም መምህር ሰሌዳው ላይ ግብረመልስ መስጠት፡፡<br>**መነጠልና ማጣመር፡** መምህር በቃላት ውስጥ ያሉትን ድምጾች ምሳሌ በመሆን መነጠል፡፡ መምህር በቃላት ውስጥ ያሉትን ድምፆች በነጠለው መንገድ ተማሪዎችም በቃላት መካከል ያሉትን ድምጾች በፍጥነት መነልጠ ተማሪዎች ቃሉን መጥራት፡፡ እንዲሁም እያንዳንዱን ድምጽ መጥራት፡፡<br>**ቀስበቀስ ማብቃት፡**<br>ሀ.መምህር ፊደላትን አድምቆ በማሳየት ድምጾታቸውን መጥራት፡፡<br>ለ. መምህር ምልክቱን ለተማሪዎች ሲያሳይ | ቃላዊ ጥያቄዎችን መጠየቅና ግብረመልስ መስጠት፤ አካላዊ ምላሽ ፤<br><br>ተማሪዎች በግላቸው ለጥያቄዎች የሚሰጡት ምላሽ<br><br>ኢ-መደበኛ ቁጥጥር<br><br>ምልከታ በምስል መወከል በሚታይ መወከል: ተራ በተራ ማቅረብ፤ ስልታዊ ልምምድ፤ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | መጻፍ ፡ በትክክለኛነት በተደጋጋሚ የሚመጡ ፊደላትን መቅረጽ የድምጸት ግንዛቤ፡ተዘውታሪ የድምጸት ደረጃዎች | ተማሪዎች ድምጸቱንና ስሙን መናገር፡፡<br>ሐ.ተማሪዎች ድምጸቱንና ምልክቱን የማዛመድ ተግባር መለማመድ፡፡<br>**እንቅስቃሴ፡** ድምጽን ከእንቅስቃሴ ጋር ማገናኘት፡፡ ይህም ተማሪዎች አካላቸውን እንዲያንቀሳቅሱ ይረዳቸዋል፡፡ ይህ ደግሞ ፊደሉንና ድምፁን እንዲያስታውሱ ይረዳቸዋል፡፡<br>**የድምጾች/የፊደላት ምልክት**<br>**የአፍ እንቅስቃሴዎች፡** ተማሪዎች እንዴት ድምጽ በአፍ ውስጥ እንደሚፈጠር መማር፡፡<br>**የድምጾች/ፊደላት ምልክት**<br>**በአየር ላይ መጻፍ** መምህር የፊደላትን ድምጽ በሚጠራበት ወቅት ተማሪዎች ፊደላቱን በጣታቸው በአየር ላይ ወይም በመጻፊያ ላይ መጻፍ፡፡<br>**ምልክቶችን መተርጎም፡** መምህር ቃላትን በማሳየት፣ እያንዳንዱን ድምጽ በማለትና በመነጠል መርዳት፡፡ (በሚታወቁ ስዕላዊ ድምጾችን በመጠቀም)<br>ተማሪዎች የመምህሩን ገለጻ በመከተል እያንዳንዱን ድምጽ ማለትና መነጠል፡፡<br>**ቃልን መገንባት፡** ተማሪዎች የቃል ክፍሎችን በመጠቀም ለአዳዲስ ቃላት ትርጉም መስጠት ይለማመዳሉ፡፡ ወይም የቃል ክፍሎችን በመጠቀም አዳዲስ ቃላትን መመስረት፡፡<br>**ማንበብ ፡** መምህር የሚነበቡ ቃላትን በ ሰሌዳ ላይ በመጻፍና ተማሪዎች በቡድን ሆነው በመመካከር ለቃላት ትርጉም እንዲሰጡ ስራ መስጠት፡፡<br>**አርአያ፤** መምህር ከማስተማሪያ መጽሀፉ ላይ ደምጽን ከፍ በማድረግ ምሳሌ በመሆን ማንበብ፤ ይህ ደግሞ ተማሪዎች የማንበብ ችሎታቸው ከፍ እንዲል ያግዛል፡፡<br>**ተደጋጋሚ የቃል ንባብ፡** መምህር ተማሪዎች በተደጋጋሚ የቃል ንባብ እንዲያደርጉ መወሰን፡፡<br>**ቀስበቀስ ማብቃት፡** በጣታቸው እያመለከቱ ማንበብና በገደል ማሚቶ ምንባብ መማር፣ በህብረት ማንበብ፣ ከጓደኞቻቸው ጋር ተባብረው ማንበብ<br>በማንሾካሾክ ከሌላ አንባቢ ጋር ማንበብ፣ | |

**ምዕራፍ አራት፡ ጓደኛማቾች (18 ክፍለ ጊዜ)**

**የሚጠበቁ ውጤቶች**

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ምንባቡን ካዳመጡ በኋላ መልእክቱን ይገነዘባሉ፡፡
- የሚታወቁ ቃላትን ይለያሉ፡፡
- አዳዲስ ፊደላትን/ድምጾችን ያነባሉ፡፡
- ደምጽንና ፊደላትን ያዛምዳሉ፡፡

| ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • ምንባቡን አንብቦየምንባቡን መልእክት መረዳት፤<br>• አዳዲስ ፊደሎችን/ድምጾችን ማንበብ፤ (ቀጥለው ያሉትን አራት ፊደላት/ድምጾች)( ከ፣ ወ፣ ዘ፣ ዠ)፤<br>• ድምጾችን መነጠልና ማጣመር<br>• ፊደሉንና ድምጾቱን ማዛመድ<br>• ተዘውታሪ ቃላትን መለየት | **ማዳመጥና መናገር**<br>**ስነድምጻዊ ግንዛቤ**<br>አምስት የተመረጡ ድምጾች/ፊደላት ከምዕራፍ 3ቀጥሎ የሚመጡ<br>**ትዕምርተ ድምጻዊ ግንዛቤ**<br>አምስት የተመረጡ ድምጾች/ፊደላት ማዛመድ፤<br>ተመሳሳይ ድምጽ ያላቸውን ቃላት መለየት፣<br>የጭብጨባ ድምጽ፣ በቃል መጀመሪያ የሚመጣ ድምጽ<br>**ቃላት፡** ተዘውታሪ ቃላት(በትምህርት ውስጥ)<br>-የቃላት እውቀት ማዳበር<br>-ጽንሰሀሳባዊ ስያሜ<br>**ማዳመጥና መናገር፡**<br>ድምጾችን | መምህር ተማሪዎችን ማነሳሳት የቀደመ ዕውቀታቸውን የማዳመጥ እውቀታቸውን በጥያቄ መልክ በማቅረብ ቀጥለው ምን እንደሚያዳምጡ እንዲገምቱ ማድረግ፡፡<br>መምህር ምንባቡን ማንበብ<br>ተማሪዎች፡ ሀሳብን ማድመጥና መለየት ከርዕሱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ቃላት መለየት (የድምጾችን/ የፊደላትን ቅርጽ፣ የባለቀለም ወረቀት፣ የካርቱን ስዕሎች ፣ የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ መጠቀም)<br>**መለየት፡** መምህር አስር በተመሳሳይ ድምጾች የሚጀምሩ/የሚጨርሱ ቃላትን አቅርቦ ተማሪዎች ደግሞ አምስት<br>በትክክል የሚመሳሰሉ ቃላትን መለየት<br>ተማሪዎች በተመሳሳይ ድምጾች የሚጀምሩ/የሚጨርሱ አዳዲስ ቃላትን መለየት፡፡<br>**መቁጠር፡**ተማሪዎች በቃላት ውስጥ ባሉ ድምጾች መጠን ያህል ያጨበጭባሉ፡፡ (የድምጾችን/ የፊደላትን ቅርጽ፣ የባለቀለም ወረቀት ፣የካርቱን ስዕሎች ፣የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ መጠቀም<br>**ተዘውታሪ ቃላት**<br>መምህር ለተወሰኑ ቃላት ትርጉም ይሰጣል፡፡ ተማሪዎች ለተቀሩት ቃላት ትርጉም ይሰጣሉ፡፡<br>**ተመሳሳይ ዜማ**<br>መምህር ተማሪዎች ተመሳሳይ ቀለም ያላቸው የአንድ ቤተሰብ ቃላት እንዲፈጥሩ መፍቀድና ሰሌዳ ላይ መጻፍ፡፡<br>ተማሪዎች ተመሳሳይ ቀለም ያላቸውን ቤተሰባዊ ቃላት መጥራት (ቀስበቀስ ራስን የማብቃት ሞደልን መጠቀም)<br>**ማጣመርና መነጠል፡**<br>መምህር በቃላት ያሉትን ድምጾች ውስጥ | በቃል/በጽሁፍ ጥያቄዎችን መጠየቅ፤<br>አካላዊ ምላሽ፤<br>ተማሪዎች በግላቸው ለጥያቄዎች የሚሰጡት ምላሽ፤<br>ኢ-መደበኛ ቁጥጥር፤<br>ምልከታ<br>በሚታይ ነገር መወከል፤<br>ተራ በተራ ማቅረብ፤<br>መውጫ ካርዶች<br>ስልታዊ ልምምድ፤ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ማዳመጥና መናገር<br><br>**ማንበብ፡ ድምጾችን ከሚወክሏቸው ፊደላት ጋር** በትክክል፣ በፍጥነት፣ በጥሩ ሁኔታ ማንበብ<br>**መጻፍ፡ ትክክለኛነት** በተደጋጋሚ የሚከሰቱ ፊደላትን መቅረጽ<br>**ድምጸታዊ ግንዛቤ** የሚታወቁ ቃላትን/ዐረፍተ ነገሮችን ከሚታወቁ አነጋገር ደረጃዎች ጋር | መጥራት በመምህር የተጠሩትን ድምጾች በፍጥነት መጥራት፡፡<br>መምህር፡ ፊደላትን በማሳየት መነጠል<br>**ቀስበቀስ ማብቃት፡**<br>ሀ.መምህር ፊደላትን በማሳየት መጥራት፡፡<br>ለ.መምህር ፊደላትን በማሳየት ተማሪዎች እንዲጠሩ መጠየቅ ፡፡<br>ሐ.ተማሪዎች ፊደላትን እያሳዩ መጥራት፡፡<br>**እንቅስቃሴ፡** መምህር ድምጾችን ከእንቅስቃሴ ጋር እንዴት እንደሚገናኙ ማሳየት ፡፡ ይሄ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን ማድረግ ድምጾችንና ፊደላትን እንዲያስታውሱ ይረዳቸዋል፡፡<br>**የአፍ እንቅስቃሴ፡**<br>ተማሪዎች ድምጾች በአንደበት ውስጥ እንዴት እንደሚፈጠሩ ማስተማር፡<br>**ቃላትን መመስረት፡** ተማሪዎች የተለያዩ የቃል ክፍሎችን ተጠቅመው አዳዲስ ቃላትን መመስረት፡፡<br>**ድምጾችን/ፊደላትን በአየር ላይ መጻፍ፡**<br>መምህር ድምጾችን ወይም የፊደል ስሞችን መጥራት፡፡ ተማሪዎች በአየር ላይ ወይም በሚጻፍ ነገር ላይ ፊደላትን በአመልካች ጣታቸው መጻፍ፡፡ ተማሪዎች ፊደላትን በአየር ላይ ወይም በሚጻፍ ነገር ላይ መጻፍ፡፡<br>**መጻፍ፡** ሀ.መምህር በቃላት ውስጥ ያሉትን ድምጾች በማሳየት እያንዳንዳቸውን መጥራት ከዚያም ድምጾቹን ማጣመር፡፡ (በታወቁ ትዕምርተ ድምጻዊ ድምጾች መጠቀም)<br>**አርአያ፡** መምህር ተማሪዎች ማንበብ ከሚጠበቅባቸው ደረጃ በላይ ድምጹን ከፍ አድርጎ ማንበብ፡፡<br>**ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ፡** መምህር ተማሪዎች ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ የሚያደርጉበትን እድል ማቅረብ ፡፡ ተማሪዎች በተደጋጋሚ ማንበብ<br>**ቀስበቀስ የማብቃት ሞዴል፡** በጣታቸው እያመለከቱ ማንበብና በገደል ማሚቶ ምንባብ መማር፣ በህብረት ማንበብ፣ ከጓደኞቻቸው ጋር ተባብረው ማንበብ፣<br>ቀስ ብሎ ከሌላ አንባቢ ጋር ማንበብ<br>**ድምጾችን/ፊደላትን በአየር ላይ መጻፍ** | |

**ምዕራፍ አምስት፡ተክሎች (18 ክፍለ ጊዜ)**

**የሚጠበቁ ውጤቶች**

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ምንባብን አዳምጠው ይረዳሉ፡፡
- የተመረጡ ድምጾችን/ፊደላትን ይለያሉ፡፡
- የፊደል ድምጽ ግንኙነትን ይሰራሉ፡፡
- ድምጾችን ከቃላት መነጠልና ማጣመር፡፡
- ቀላል ዐ. ነገሮችን ይመሰርታሉ፡፡
- ተዘውታሪ ቃላትን ትርጉም ይሰጣሉ፡፡

| **ብቃቶች** | **ይዘቶች** | **የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች** | **ምዘና** |
|---|---|---|---|
| ምንባቦችን አዳምጦ መረዳት፤<br><br>ከምዕራፍ 4 በኋላ ቀጥሎ የሚመጡ አምስት ድምጾችን /ፊደላትን (የ፣ ደ፣ ጀ፣ ገ) መለየት /<br><br>ተዘውታሪ ቃላትን ትርጉም ይሰጣሉ.<br><br>ቀላል አ/ነገሮችን ይመሰርታሉ. | **ድምጻዊ ግንዛቤን ማዳመጥና መናገር፡**<br>የተመረጡ አምስት ድምጾች/ፊደላት ከምዕራፍ 4 በኋላ ቀጥሎ የሚመጡ<br><br>**የትምህርተ ድምጽ ግንዛቤ፡** አምስት የተመረጡ የፊደል ድምጽ ግንኙነት ፣ ተመሳሳይ ቀለማት ያላቸው ቃላት በመነሻ ሲያጋጥሙ ማጨብጨብ<br>**የቃላት ጥናት፡** ተዘውታሪ የትምህርት ቃላት ጽንሰ ሀሳቦችን መጥራት<br><br>**ማንበብና** | **መምህር፡** ተማሪዎችን የሚያዳምጡትን ምንባብ የቀደመ ዕውቀታቸውን በመጠቀም ቃላዊ ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>**መገመት፡** ስእሎችን፣ ምዕራፎችንና ቁልፍ ቃላትን በመመልከት ስለምን እንደሚያዳምጡ መገመት፡<br>**መምህር፡** ተማሪዎች አስር ቃላትን እንዲጠሩና ከጠሩት አምስት ቃላት በተመሳሳይ ድምጽ የሚጀምሩ ቃላትን እንዲለዩ መጠየቅ፡፡ ተማሪዎችም አምስት በድምጽ የሚመሳሰሉ ቃላትን መጥራት፡፡ (የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣ የባለቀለም ወረቀት ፣ የካርቱን ስዕሎች ፣ የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ መጠቀም)<br>**መቁጠር፡** በቃላት ተመሳሳይ ድምጽ ሲከሰት ያጨበጭባሉ /የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣ የባለቀለም ወረቀት ፣ የካርቱን ስዕሎች ፣ የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ መጠቀም)<br>ተመሳሳይ ድምጸት ተመሳሳይ ቀለም ያላቸውን ቃላት መዝሙሮችን ለመፍጠር //ቤተሰባዊ ቃላትን/መፍጠር፡፡<br>**ማንበብ፡** ሀ. መምህር በቃሉ ውስጥ ያሉትን ድምጾች ሁሉ ማሳየት፤ ከዚያም ድምጾቹን መነጠል፡፡<br>**ቃላትን መመስረት፡** ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን ቃል ክፍሎችን በመጠቀም መጻፍ ይለማመዳሉ፡፡<br>**ተዘውታሪ ቃላት፡** መምህር የቃላትን ቀጥተኛ ትርጉም መጻፍ<br>ተማሪዎችን ቃላትን ከቀጥተኛ ትርጉማቸው ጋር ማዛመድ፡፡<br>ተማሪዎች መምህራቸው መዝሙር ሲዘምር መከተል፡፡<br>**መነጠልና ማጣመር፡** የተለዩ ድምጾችን ይለዩና በፍጥነት መፍጠር<br>(መምህር ማጣመርን ለማስተማር ቃላትን ሲከፋፍል ተማሪው የተከፋፈለውን በማጣመር ቃሉን መጥራት<br>**ቀስ በቀስ ራስን ማስቻል፡**<br>ሀ. መምህርፊደላትን ቅርጻቸውን በማሳየት | በቃልና በጽሁፍ ጥያቄዎችን መጠየቅ፤<br><br>**አካላዊ ምላሽ፤**<br>የተማሪዎች በግል ለጥያቄዎች የሚመልሱት አካላዊ ምላሽ፤<br><br>ኢ-መደበኛ ቁጥጥር፤<br><br>ምልከታ፤<br><br>በስዕል መወከል፤<br>ተራ በተራ ማቅረብ፤<br><br>ስልታዊ ልምምድ፤ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | **መጻፍ**<br>**ድምጾችን ማንበብና መጻፍ** | የሚወክሏቸውን ድምጾች መጥራት፡፡<br>ለ. መምህርቅርጻቸውን በማሳየት ተማሪዎች ድምጾችን እንዲጠሩ መጠየቅ ሐ.ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው ፊደላትን ከድምጾቻቸው ጋር በማያያዝ መጥራት፡፡<br>**እንቅስቃሴ፡** ድምጾችን ከእንቅስቃሴ ጋር ማያያዝ፤ይህ ተማሪዎች ድምጾችንና/ፊደላትን ለመለየት ያስችላል፡፡<br>**አፋዊ እንቅስቃሴ፡** ድምጾች አንደበት ውሰጥ እንዴት እንደሚፈጠሩ መማር፡፡<br>**አርአያነት፤** መምህር ተማሪዎች ካላቸው የማንበብ ችሎታ በላይ በትክክል ማንበብ<br>**ተደጋጋሚ የቃል ንባብ፡** መምህር ተደጋጋሚ ለቃል ንባብ ያጋልጣል፤<br>ተማሪዎችም በተደጋጋሚ ትክክለኛነትን ለማጎልበት ማንበብ<br>**ቀስ በቀስ ራስን የማስቻል ሞዴል፤**<br>ጣትን በመጠቆም በገደል ማሚቶ፣<br>የጋራ ንባብ፣ ከጓደኛ ጋር ማንበብ፣ ሌላውን ተከትሎ ማንበብ<br>ድምጾችን /ፊደላትን መቅረጽ<br>ቀላል አ/ነገሮችን መጻፍ ፤<br>መምህር ሞዴል በመሆን ቀላል አ/ነገሮችን ይጽፋል፤<br>ተማሪዎችም ቀላል አ/ነገሮችን መጻፍ መጀመር፤<br>**በአየር ላይ መጻፍ፡** ተማሪዎች ፊደላትን በአመልካች ጣታቸው በአየር ላይ ወይም በሚጻፍ ነገር ላይ መቅረጽ፤ መምህር የፊደል ድምጾችን መጥራት፤ ተማሪዎችም በጣታቸው በአየር ላይ ፊደላትን መጻፍ፡፡ | |

# የሁለተኛ ወሰነ ትምህርት

**ምዕራፍ ስድስት፡ የመንገድ ደህንነት** (18 ክፍለ ጊዜ)
**የሚጠበቁ ውጤቶች**
ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ምንባብን በማንበብ መልእክትን ይጨብጣሉ፡፡
- በአዳዲስ ፊደላት ቃላትን ይጽፋሉ፡፡
- ቀላል አ/ነገሮችን ይጽፋሉ፡፡
- ቅጥያዎችን ከቃላት ይለያሉ፡፡

| ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| በማዳመጥ መልእክቶችን መጨበጥ፤<br><br>በአዳዲስ ፊደላት/ድምጾች ቃላትን መጻፍ<br><br>አጫጭር አ/ነገሮችን መጻፍ<br>ቅጥያዎችን ከቃላት መለየት | **ማዳመጥና መናገር**<br>በምዕራፍ አምስት ከቀረቡት ቀጥለው የሚመጡ አምስት ድምጾች/ፊደላት ማዳመጥና መናገር<br>**ቃላት** ፡<br>ተዘውታሪ /የትምህርት ቃላት የቃላት እድገት<br>ቃላትን መተርጎም<br>**ማንበብና መጻፍ**፡<br>ድምጾችን ማንበብና መጻፍ<br>**ማንበብ፡**<br>የፊደል -ድምጽ ግንኙነትን በትክክለኛነት፣ በጥሩ አገላለጽ፣ በተገቢ ፍጥነትና በመረዳት ማንበብ | **መምህር፡** ቃላትን ያነባል/ይዘምራል (ለምሳሌ ቀኝ ፣ ግራ፣ መንገድ፣ ወዘተ)<br>**ተማሪዎች፡** ከላይ የቀረቡትን ቃላት በማዳመጥ ለብቻቸው ማንበብ፡፡<br>**መለየት፡** መምህር አስር በተመሳሳይ ድምጾች የሚጀምሩ/የሚጨርሱ ቃላትን ማቅረብ ተማሪዎች ደግሞ ስድስት በትክክል የሚመሳሰሉ ቃላትን መለየት፡፡<br>ተማሪዎች በተመሳሳይ ድምጾች የሚጀምሩ/የሚጨርሱ አዳዲስ ቃላትን ይለያሉ፡፡ (/የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣ የባለቀለም ወረቀት፣ የካርቱን ስዕሎች፣ የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ መጠቀም)<br>**ቃላትን መመስረት፡** ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን የቃላት ክፍሎችን በመጠቀም መጻፍ<br>**ተዘውታሪ ቃላት፡** በከፍተኛ ደረጃ ድግግሞሽ ያላቸውን ቃላት በፍጥነት የመገንዘብ ችሎታን ማጎልበት፡፡<br>**መቁጠር፡** በቃላት ውስጥ ተመሳሳይ ድምጾች ሲያጋጥሙ ማጨብጨብ (/የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣ የባለቀለም ወረቀት፣ የካርቱን ስዕሎች፣ የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ መጠቀም)፡፡<br>**ድምጸት፡** ተማሪዎች ተመሳሳይ ቀለም ያላቸውን ቃላት ሲጠሩ መምህር በሰሌዳ ላይ ምልክት ማድረግ፡፡<br>**ቀስ በቀስ ራስን ማስቻል፡**<br>ሀ. መምህር ፊደላትን እያሳየ ይጠራል<br>ለ. መምህር ፊደላትን እያመለከተ ተማሪዎች እንዲናገሩ መጠየቅ<br>ሐ.ተማሪዎች ብቻቸውን ፊደላትን እያሳዩ መጥራት<br>**እንቅስቃሴ፡** ድምጾችን ከእንቅስቃሴ ጋር ማገናኘት፡፡<br>ተማሪዎች አፋቸውን ማንቀሳቀሳቸው ድምጾችን መለየት እንዲችሉ ያግዛቸዋል፡፡ | በቃልና በጽሁፍ ጥያቄዎችን መጠየቅ፤<br><br>አካላዊ ምላሽ<br><br>የተማሪዎች በግል ለጥያቄዎች የሚመልሱት አካላዊ ምላሽ፤<br><br>ኢ.መደበኛ ቁጥጥር፤<br><br>ምልከታ፤<br>በስዕል መወከል፤<br>ተራ በተራ ማቅረብ፤<br><br>ስልታዊ ልምምድ<br>መውጫ ካርድ፤ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | **መጻፍ፡** ፊደላትን በትክክል መጻፍ ድምጸታዊ **ግንዛቤ፡** የሚታወቁ ቃላትና አ/ነገሮችን ከታወቀ የድምጸት ደረጃ ጋር | **የአንደበት እንቅስቃሴ፡** ተማሪዎች ድምጸች አንደበት ውሰጥ እንዴት እንደሚፈጠሩ መማር፡፡ **ማንበብ፡** መምህር በቃላት ውስጥ ያሉትን ድምጾች መጥራት ፤ከዚያም ድምጸችን ማጣራት (በታወቁ የፊደል ድምጽ ግንኙነት) **አርአያነት፤** መምህር ተማሪዎች ካላቸው የማንበብ ችሎታ በላይ በትክክል ማንበብ፤ ተደጋጋሚ የቃል ንባብ መምህር ተደጋጋሚ ለቃል ንባብ ያጋልጣል፤ተማሪዎችም በተደጋጋሚ ትክክለኛነትን ለማጎልበት ማንበብ **ቀስ በቀስ ራስን የማስቻል ሞዴል፤** ጣትን በመጠቆም በገደል ማሚቶ፣ የጋራ ንባብ፣ ከጓደኛ ጋር ማንበብ፣ ሌላውን ተከትሎ ማንበብ ድምጸችን /ፊደላትን መቅረጽ **ቀላል አ/ነገሮችን መጻፍ ፤** መምህር ሞዴል በመሆን ቀላል አ/ነገሮችን መጻፍ ፤ ተማሪዎችም ቀላል አ/ነገሮችን መጻፍ መጀመር **በአየር ላይ መጻፍ፡** ተማሪዎች ፊደላትን በአመልካች ጣቶቻቸው በአየር ላይ ወይም በሚጻፍ ነገር ላይ ይቀርጻሉ፤ መምህር የፊደል ድምጸችን ይጠራል፤ ተማሪዎችም በጣቶቻቸው በአየር ላይ ፊደላትን መጻፍ፡፡ | |

**ምዕራፍ ሰባት፡ ተረቶች (18 ክፍለ ጊዜ)**

**የሚጠበቁ ውጤቶች**

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ምንባቦችን በማዳመጥ ታሪኮችን ይተርካሉ፡፡
- በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ አዳዲስ ቃላትን ያነባሉ፡፡
- በቃላት ውስጥ ያሉ ድምጾችን በመነጠልና በማጣመር ያነባሉ፡፡(ተለይተው የተዘረዘሩ ድምጾች/ፊደላት)፡፡

| ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ታሪኮችን አዳምጦ መተረክ፤ አዳዲስ ቃላትን ማንበብ ድምጾችን በመነጠልና በማጣመር ማንበብ (አራት ድምጾችን /ፊደላትን (ጠ፣ ጩ፣ ጸ፣ ፀ)<br><br>ተዘውታሪ ቅጥያዎችን መለየ | **ድምጻዊ ግንዛቤ** ከምዕራፍ ስድስት አራት፤ የተመረጡ ድምጾች /ፊደላት **ትእምርተ ድምጻዊ ግንዛቤ፤** የተመረጡ ድምጾች /ፊደላት ማዛመድ፡ በተመሳሳይ ቀለም፣ ማጨብጨብ፣ በቃል መነሻ የሚገኙ ድምጾች **የቃል ጥናት፡** ተዘውታሪ /የትምህርት ቃላት<br>-የቃላት እድገት<br>-የጽንሰ ሀሳብ ስያሜ<br>**ማንበብና መጻፍ፡ቃላትን መነጠልና ማጣመር ማንበብ፡ ትክክለኛነት፣ ፍጥነት፣ ጥሩ** | **መምህር፡** ተማሪዎች በቡድን ተቀምጠው የሚያውቁትን ታሪክ እንዲለዋወጡ መጠየቅ ፡፡ **ተማሪዎች፡** እርስ በእርሳቸው የሚያውቁትን ታሪክ መተረክ፡፡ መምህር የተመረጡ ታሪኮችን አቅርቦ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን መጠየቅ፡ ፡<br>**መለየት፡** መምህር ቃላትን በቃል መጥራት፤ በቃሉ ውስጥ ያሉትን ድምጾች መነጠል እና ማጣመር፡፡ ተማሪዎችም መምህር የሚያሳዩአቸውን ድርጊት በመከተል በቃላቱ ውስጥ የሚገኙትን ድምጾች መጥራት፤ማጣመር፡ ፡ (/የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣ የባለቀለም ወረቀት፣ የካርቱን ስዕሎች፣ የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ ወዘተ መጠቀም)<br>መምህር በአንድ ጎን ቃላትን በቃላት ካርድ ላይ፣ በሌላ ጎን የታወቁ ቅጥያዎችን መጻፍ፡፡ ከዚያም የሚገናኙትን ማዛመድ፡፡<br>**መቁጠር፡** ተማሪዎች አዳዲስ ቃላት ከሚታወቁ ቅጥያዎች ጋር በምንባቡ ውስጥ ሲያገኙ ማጨብጨብ (የድምጾችን /የፊደላትን ቅርጽ፣ የባለቀለም ወረቀት ፣ የካርቱን ስዕሎች ፣ የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ ወዘተ መጠቀም)<br>**ተመሳሳይ ዜማ፡** ተማሪዎች በመድረሻ ላይ ተመሳሳይ ቀለሞች ያሏቸውን ቤተሰባዊ ቃላት መጥራት፡፡ ከዚያም መምህር ምላሹን በሰሌዳ ላይ መጻፍ፡፡<br>**መነጠልና ማጣመር፡** መምህር የታወቁ ቅጥያዎችን በቃላት ላይ በማጣመርና በመነጠልን ማሳየት፡፡ ተማሪዎች የታወቁ ቅጥያዎችን ከቃላት ላይ መነጠልና ማጣመርን መለማመድ፡<br>**ቃላትን መመስረት፡** ተማሪዎች የቃላት | በቃልና በጽሁፍ ጥያቄዎችን መጠየቅ፤<br><br>አካላዊ ምላሽ፡<br><br>የተማሪዎች በግል ለጥያቄዎች የሚመልሱት አካላዊ ምላሽ፤<br><br>ኢ.መደበኛ ቁጥጥር:<br><br>ምልከታ፤<br><br>በስዕል መወከል፤ ተራ በተራ ማቅረብ፤ ስልታዊ ልምምድ፤ መውጫ ካርድ፤ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | **አገላለጽና አንብቦ መረዳት፣**<br><br>**መጻፍ፡**<br>**ትክክለኛነት**<br>**ድምጸታዊ**<br>**ግንዛቤ፡** | ክፍሎችን በመጻፍ አዳዲስ ቃላትን መመስረት መለማመድ፡፡<br>**ተዘውታሪ ቃላት፡**<br>መምህር የግድግዳ ላይ ቃላትን ከፍቺዎቻቸው ጋር ማዘጋጀት፡፡ ከዚያም ለቃላቱ ትርጉማቸውን መስጠት፡፡<br>**ቀስበቀስ ማብቃት ፡** ሀ.መምህርፊደላትን በማሳየት መጥራት፡<br>ለ.መምህርፊደላትን እያሳየ ተማሪዎችን ፊደላቱን እንዲጠሩ መጠየቅ፡፡<br>ሐ.ተማሪዎች ፊደላትን ድምጾችን ማዛመድን መልመድ፡፡<br>**እንቅስቃሴ፡** ድምጾችን ከእንቅስቃሴ ጋር ማገናኘት፡፡ ይህ ተማሪዎች አካላቸውን በማንቀሳቀስ ድምጾችንና ፊደላትን እንዲያስታውሱ ያግዛቸዋል፡፡<br>**አፋዊ እንቅስቃሴዎች፡** ተማሪዎች በአንደበት አካላት ውስጥ ድምጾች እንዴት እንደሚፈጠሩ መማር፡፡<br>**መጻፍ፡** መምህር በቃላት ውስጥ ያሉትን ድምጾች በመነጠል መጥራት፡፡ (የታወቁ የፊደል ድምጾችን መጠቀም)<br>**አርአያ፡** መምህር ተማሪዎች ከሏቸው የማንበብ ችሎታ በላይ የሚነበቡ ምንባቦችን በከፍተኛ ድምጽ ማንበብ፡፡<br>**ተደጋጋሚ የቃል ንባብ፡** ይህ ተማሪዎች ትክክለኛነትን እንዲያዳብሩ እድል መስጠት፡፡<br>**ቀስበቀስ ማብቃት፡** ጣትን በመጠቆም በገደል ማሚቶ፣ የጋራ ንባብ፣ ከጓደኛ ጋር ማንበብ ፣ ሌላውን ተከትሎ ማንበብ፡፡<br>ድምጾችን /ፊደላትን መቅረጽ፤ በተደጋጋሚ የሚከሰቱ ፊደላትን መጻፍ<br>**መጻፍ፡** መምህር ቀላል አረፍተ ነገሮችን መጻፍ በመቀጠል ተማሪዎች መምህርን በመከተል በትክክል ቀላል አረፍተ ነገሮችን መጻፍ፡፡<br>በተደጋጋሚ የሚከሰቱ ፊደላትን መጻፍ | |

**ምዕራፍ ስምንት፡ ምግብ** (18 **ክፍለ ጊዜ**)

**የሚጠበቁ ውጤቶች**

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ምንባቡን በማዳመጥ የምግብ አይነቶችን ይዘረዝራሉ፡፡
- አዳዲስ ፊደላትን/ድምጾችን ያነባሉ፡፡
- ድምጾችን ከቃላት ውስጥ በመነጠልና በማጣመር ያነባሉ፡፡
- ተዘውታሪ ቃላትን ያነባሉ፡፡

| ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ምንባቡን አዳምጠው ዝርዝር ሀሳቦችን ይናገራሉ፡፡<br><br>አዳዲስ ፊደላትን/ድምጾችን ከምዕራፍ ሰባት በኋላ የሚመጡ ሶስት ፊደሎችን ያነባሉ(ፈ፣ ፐ፣ ቨ)<br><br>ድምጾችን በመነጠልና በመጣመር ያነባሉ ማንበብ፤<br><br>አዲስ ቃላትን ያነባሉ ማንበብ<br><br>ቅጥያዎችን ይለያሉ፡፡ | **መናገርና ማዳመጥ**<br><br>**ስነድምጻዊ ግንዛቤ፡** ከምዕራፍ ስምንት በኋላ የሚመጡ የተመረጡ ሶስት ድምጾች/ፊደች<br>**ትዕምርተ ድምጻዊ ግንዛቤ፡** የተመረጡ የድምጾች/ፊደላት ተዛምዶ፣ ቃላት በመነሻቸው ተመሳሳይ ቀለምና ድምጽ ሲኖራቸው ተማሪዎች ማጨብጨብ<br>**የቃላት ጥናት** ተዘውታሪ ቃላት (የትምህት)<br>-የቃላት እድገት<br>-ጽንሰ ሀሳባዊ ስያሜ<br>**ማንበብና መጻፍ፡** | **መምህር፡** በቤታቸው ውስጥ ስለሚገኙ ምግቦች ቃላዊ ጥያቄዎችን ማቅረብ፡፡ ከዚያም መምህር ምንባቡን በቃል ማንበብ፡፡<br>**መምህር ቢጋር ሰንጠረዥን በአዕምሮ መሳል፡፡**<br>ተማሪዎች የምንባቡን ዋና መልእክትና ተዘውታሪ ቃላትን የተዘጋጀውን ቢጋር ሰንጠረዥ በመመልከት መግለጽ፡፡ (ለምሳሌ ስም፣አይነት፣ጥቅም፣አዘገጃጀት)<br>**መምህር፡** በተለዩ ድምጾች የሚጀምሩ/የሚጨርሱ ቃላትን መጻፍ፡፡<br>**ተማሪዎች፡** በቃላት ውስጥ ያሉትን ድምጾች በመለየት በመነጠልና በማጣመር መጥራት፡፡ (የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣የባለቀለም ወረቀት፣ የካርቱን ስዕሎች ፣ የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ ወዘተ መጠቀም)<br>**መቁጠር፡** ተማሪዎች በቃላት ውስጥ ባሉ ቅጥያዎች ብዛት መጠን በመለየት ማጨብጨብ፡፡<br>**ተመሳሳይ ድምጽ፡** ተማሪዎች ተመሳሳይ ቀለም ያላቸውን ቃላት ይፈጥራሉ፤<br>መምህሩም በ ሰሌዳ ላይ ምላሽ መስጠት፡ ፡ (የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣ የባለቀለምወረቀት ፣ የካርቱን ስዕሎች ፣ የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ ወዘተመጠቀም)<br>**መነጠልና ማጣመር፡** ተማሪዎች በቃል | በቃልና በጽሁፍ ጥያቄዎችን መጠየቅ፣<br><br>አካላዊ ምላሽ፣ የተማሪዎች በግል በጥያቄዎች የሚመለሱ አካላዊ ምላሽ፣<br><br>ኢ.መደበኛ ቁጥጥር፣<br><br>ምልከታ፣ በስዕል መወከል ተራ በተራ ማቅረብ፣ ስልታዊ ልምምድ መውጫ ካርድ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | **ማንበብ፡ በትክክል ፣ በፍጥነት፣ በጥሩ አገላለጽና በመረዳት፣ መጻፍ፡ ትክክለኛነት የፊደላትን ድምጸት መጻፍ ተመሳሳይ ድምጽ፤** የሚታወቁ ቃላትና አረፍተ ነገሮች ከሚታወቁ የድምጸት ደረጃዎች ጋር | ውስጥ የተለዩ ድምጾችን ለይተው በፍጥነት መጥራት፡፡<br>መምህር ደግሞ ማጣመርን ለማሳየት ፊደላትን ማቀናጀት<br>ተማሪዎች በቃላት ውስጥ ያሉትን ቀለማት ወይም ድምጾች መጥራት፡፡<br>**ቀስበቀስ ማብቃት፡**<br>ሀ.መምህር ፊደላትን በማሳየት መጥራት፡፡<br>ለ.መምህር ፊደላትን በማሳየት ተማሪዎች ፊደላቱን እንዲጠሩ መጠየቅ፡፡<br>ሐ.ተማሪዎች ፊደላትን፣ ድምጾችን ማዛመድን መለማመድ፡፡<br>**እንቅስቃሴ፡** ድምጾችን ከእንቅስቃሴ ጋር ማገናኘት፡፡ ይህ ተማሪዎች አካላቸውን በማንቀሳቀስ ድምጾችንና ፊደላትን እንዲያስታውሱ ያግዛቸዋል፡፡<br>**ቃላትን መመስረት፡** ተማሪዎች የቃላት ክፍሎችን በመጻፍ አዳዲስ ቃላትን መመስረት ማለማመድ፡፡<br>**ተዘውታሪ ቃላት፡** በከፍተኛ ደረጃ ተደጋግመው የሚነገሩ ቃላትን ለማወቅ ልምድ ማዳበር<br>**አፋዊ እንቅስቃሴ፡** ተማሪዎች ድምጾች በአንደበታቸው ውስጥ እንዴት እንደሚፈጠሩ መማር፡፡<br>**በአየር ላይ መጻፍ፡** ተማሪዎች የተለዩ ፊደላትን በአየር ላይ ወይም በሚጻፍ ነገር ላይ በአመልካች ጣቶቻቸው መጻፍ፡፡<br>መምህር የፊደሉን ድምጽ ይጠራል፡፡<br>ተማሪዎች በአየር ላይ ወይም በመጻፊያ ነገር ላይ በጣቶቻቸው መጻፍ፡፡<br>**ማንበብ፡** መምህር በቃላት ውስጥ ያሉ ድምጾችን እያሳየ መጥራት፡፡ ከዚያም ድምጾቹን ማጣመር ፡፡ (የታወቁ የፊደል ድምጽ ግንኙነቶችን መጠቀም)<br>**አርአያ፡** መምህር ተማሪዎች ካሏቸው የማንበብ ችሎታ በላይ የሚነበቡ ምንባቦችን በከፍተኛ ድምጽ ማንበብ፡፡ | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | **ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ፡** ተማሪዎች በትክክል ማንበብን እንዲያዳብሩ ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብን ማቅረብ፡፡<br>**ቀስበቀስ ማብቃት፡**<br>በአመልካች ጣትና መርህን ተከትለው በገደል ማሚቶ ንባብ፣ በጋራ ንባብ፣ ከሌሎች ጋር አብሮ ማንበብ፡፡<br>በተደጋጋሚ የሚከሰቱ ፊደላትን መቅረጽ፡ አረፍተ ነገሮችን መጻፍ፡፡<br>አጭር ምንባብ መጻፍ፡፡ | |

**ምዕራፍ ዘጠኝ፡ የግል ንጽህና (18 ክፍለ ጊዜ)**
**የሚጠበቁ ውጤቶች**
ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ምንባብን አዳምጠው መልዕክቱን በቃል ይገልጻሉ፡፡
- አዳዲስ ፊደላትን/ድምጾችን ያነባሉ(የተመረጡ ድምጾች/ፊደላት)ይዘረዝራሉ፡፡
- ድምጾችን በመነጠልና በማጣመር(የተመረጡ ድምጾች/ፊደላት) ያነባሉ፡፡ ከግል ንጽህና ጋር የተያያዙ ቃላትን ያነባሉ፡፡
- ለሁለት ቀለም ቃላትን ነጥለው ያጣምራሉ፤

| ብቃት | ይዘቶች | የመማር ብልሀቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ምንባብን አዳምጦ መልዕክቱን በመጨበጥ፣ በቃል መግለጽ፣ የአዳዲስ ፊደላትን/ድምጾችንማንበብ(ከምዕራፍ ስምንት በኋላ የሚመጡ አራት ድምጾች)(ሀ፣ ሐ፣ ኀ፣ ኸ) | **ድምጻዊ ግንዛቤ፡** ከምዕራፍ ስምንት ቀጥሎ የሚመጡ አራት ድምጾች/ፊደላት | መምህር በክፊል የተዘጋጀ የቢጋር ሰንጠረዥ ማዘጋጀት ቀሪውን ተማሪዎች ከሚያዳምጡት ምንባብ እንዲያሟሉ መጠየቅ፡፡ ከግል ንጽህና ጋር የተያያዙ ቃላትን(ለምሳሌ፡ - ጽዱ፣ንጹህ፣ ማጠብ፣ ቆሻሻ፣ ዘዴ፣ጥቅምና አደገኛ) መለየት<br>**መለየት፡**መምህር በቃላት ውስጥ የተመረጡ ድምጾችን/ፊደላትን መጥራት፡፡ መጀመሪያ መምህር በቃላት ውስጥ ያሉትን ድምጾች በመነጠልና በማጣመር ሞዴል መሆን፡፡ ከዚያም ተማሪዎች አምስት ድምጾችን በቃላት ውስጥ ለይተው በመነጠልና በማጣመር (የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣የባለቀለም ወረቀት ፣ የካርቱን ስዕሎች ፣የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ ወዘተ)መጠቀም፡፡ | **አካላዊ ምላሽ** ተማሪዎች በግል ለጥያቄዎች የሚመልሱት አካላዊ ምላሽ፤ ኢ-መደበኛ ቁጥጥር፤ ምልከታ፤ በስዕል፤ መወከል |
| ድምጾችን በመነጠልና በማጣመር ማንበብ፣ | **ትዕምርተ ድምጻዊ ግንዛቤ፡** የተመረጡ | **መቁጠር** ተማሪዎች በአረፍተነገር ውስጥ ባሉ ቃላት፣ በቃል ውስጥ ባሉ ተመሳሳይ ቀለሞች፣በቃላት ውስጥ ባሉ ድምጾች መጠን ማጨብጨብ (የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣የባለቀለም ወረቀት ፣የካርቱን ስዕሎች ፣የቃላት | ተራ በተራ ማቅረብ፤ ስልታዊ ልምምድ፤ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| አዳዲስ ቃላትን መጻፍ፣<br><br>ቅጥያዎችን መለየት፣ | የድምጽ/ ፊደል ተዛምዶ፣ ተመሳሳይ ቀለም ያላቸው ቃላት በቃል መነሻ ሲመጡ ማጨብጨብ | ካርድ፣ ሰሌዳ ወዘተ መጠቀም)<br>**ተመሳሳይ ድምጽ** ተማሪዎች ተመሳሳይ ቀለም ያላቸውን ቃላት መፍጠር፤ መምህሩም በሰሌዳ ላይ ምላሽ መጻፍ፡፡<br>**ማጣመርና መነጠል፡**ተማሪዎች በቃሉ ውስጥ ያሉትን ድምጾች በመነጠል መናገር፡፡ (በፍጥነት ማስባል) በመቀጠል (መምህርመነጠልን ለማሳየት ፊደላትን ማጣመር)፡፡ ተማሪዎች ቃሉን ጠርተው በቃሉ ውስጥ ያሉትን ቀለሞችና ድምጾች መጥራት፡፡<br>**ቀስበቀስ ማብቃት፡**<br>ሀ.መምህርፊደላትን በማሳየት መጥራት፡፡<br>ለ.መምህርፊደላትን እያሳየ ተማሪዎችን ፊደላቱን እንዲጠሩ መጠየቅ፡፡<br>ሐ.ተማሪዎች ፊደላትንና ድምጾችን ማዛመድን መለማመድ፡፡<br>**እንቅስቃሴ፡** ድምጾችን ከእንቅስቃሴ ጋር ማገናኘት፡፡ ይህ ተማሪዎች አካላቸውን በማንቀሳቀስ ድምጾችንና ፊደላትን እንዲያስታውሱ ማገዝ፡፡<br>**ቃላትን መመስረት፡** ተማሪዎች የቃላት ክፍሎችን በመጻፍ አዳዲስ ቃላትን መመስረት መለማመድ፡፡<br>**ተዘውታሪ ቃላት**፡ በከፍተኛ ደረጃ ተደጋግመው የሚነገሩ ቃላትን ለማወቅ ልምድ ማዳበር<br>**መናገር**<br>ሀ.መምህር ቃላትን በማሳየት፣ እያንዳንዱን ድምጽ በመጥራት፣ድምጾችን በመነጠል (የታወቁ የድምጾችን ምልክቶች በመጠቀም) ማስተባበር፡፡<br>መምህር መር በሆነ ዘዴ ተማሪዎች ድምጾችን መነጣጠል፡<br>**አርአያ፡** መምህርተማሪዎች ካሏቸው የማንበብ ችሎታ በላይ የሚነበቡ ምንባቦችን በከፍተኛ ድምጽ ማንበብ፡፡<br>**ድምጾችን መቅረጽ**<br>**ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ፡** ተማሪዎች ለተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ እንዲጋለጡ እድል መስጠት፡፡<br>**ቀስበቀስ ማብቃት፡** በአመልካች ጣትና መርህን ተከትለው በገደል ማሚቶ ንባብ፣<br>በጋራ ንባብ፣ ከሌሎች ጋር አብሮ ማንበብ፡፡<br>በተደጋጋሚ የሚከሰቱ ፊደላትን መቅረጽ፡፡<br>ተማሪዎች የተለዩ ፊደላትን በአየር ላይ ወይም በሚጻፍ ነገር ላይ በአመልካች ጣቶቻቸው መጻፍ፡፡ መምህር የፊደሉን ድምጽ መጥራት፡፡ ተማሪዎች በአየር ላይ ወይም በመጻፊያ ነገር ላይ በጣቶቻቸው መጻፍ፡፡ | መውጫ ካርድ ጽብረቃ |

**ምዕራፍ አስር፡ የቤት እንስሳት (18 ክፍለ ጊዜ)**

**የሚጠበቁ ውጤቶች**

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ምንባብን አዳምጠው ከነባራዊው ሁኔታ ጋር ያዛምዳሉ፡፡ የፊደላትን ድምጾች ይጠራሉ፡፡
- ባለሶስት ቀለም ቃላትን ወደ ድምጾች በመነጠል መልሰው ያጣምራሉ፡፡
- ቃላትን በአዳዲስ ፊደላት ይጽፋሉ፡፡
- ቅጥያዎችን ይለያሉ፡፡

| ብቃት | ይዘቶች | የመማር ብልሀቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ምንባቡን አዳምጠው ሀሳቡን ከነባራዊው አለም ጋር ያዋህዳሉ፡፡<br><br>አዳዲስ የፊደላትን ድምጾች(ከምዕ ራፍ ዘጠኝ ቀጥሎ የሚመጣ ሶሰት ድምጾችን ይጠራሉ) (ጸ፣ ሰ፣ ዐ)<br><br>ባለሶስት ቀለም ቃላትን መነጠልና ማጣመር ቅጥያዎችን መነጠል | ስነድምጻዊ ግንዛቤ፡ ከምዕራፍ ዘጠኝ ቀጥሎ የሚመጡ ሶስት ድምጾች፣<br><br>ትዕምርተ ድምጻዊ ግንዛቤ፡ የተመረጡ የድምጽ/ ፊደል ተዛምዶ፣ ተመሳሳይ ቀለም ያላቸው ቃላት በቃል መነሻ ሲመጡ ማጨብጨብ፣<br><br>የቃል እውቀት፡ ተዘውታሪ ቃላት፣ (ትምህርታዊ) -የቃላት እድገት -ጽንሰ ሀሳባዊ ስያሜ ማንበብና መጻፍ፡ አጫጭር ምንባቦችን ማንበብ፣ በትክክል፣ በፍጥነት፣ በጥሩ፣ አገላለጽና በመረዳት | መምህር የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት መቀስቀስ፡፡ መምህር የተወሰኑ ሀሳቦችን ከሚደመጠው ምንባብ የሚያመለክቱ የቢ.ጋር ሰንጠረዦችን ሞልቶ የተቀሩትን ክፍት መተው፡፡ ተማሪዎችም ክፍት ቦታ በመተው ምንባቡን በማዳመጥ የቢ.ጋር ሰንጠረዡን ማሟላት፡፡<br>**መለየት፡** መምህር በተመሳሳይ ድምጾች/ፊደላት የሚጀምሩ ወይም የሚጨርሱ ቃላትን እንዲጽፉ መጠየቅ፡፡ ከዚያም መምህር ሞዴል የሚሆኑ ቃላትን መጥራት፡፡ ተማሪዎች አምስት ድምጾችን በመነጠልና በማጣመር ለይቶ ማንበብ፡፡ (የድምጾችን/የፊደላትን (ቅርጽ፣ የባለቀለም ወረቀት፣ የካርቱን ስዕሎች፣ የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ ወዘተ መጠቀም)<br>**መቁጠር፡** ተማሪዎች በአረፍተነገር ውስጥ ባሉ ቃላት፣ በቃል ውስጥ ባሉ ተመሳሳይ ቀለሞች፣ በቃለት ውስጥ ባሉ ድምጾች መጠን ማጨብጨብ<br>**ተመሳሳይ ድምጽ፡** ተማሪዎች ተመሳሳይ ቀለም ያላቸውን ቃላት መጥራት፣ መምህርም በሰሌዳ ላይ ምላሽ መስጠት፡፡<br>**ማጣመርና መነጠል፡** ተማሪዎች በቃሉ ውስጥ ያሉትን ድምጾች በመነጠል መናገር፡፡ (በፍጥነት ማስባል) በመቀጠል (መምህር መነጠልን ለማሳየት ፊደላትን ማጣመር)፡፡ ተማሪዎች ቃሉን ጠርተው በቃሉ ውስጥ ያሉትን ቀለሞችና ድምጾች መጥራት፡፡ (የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣ የባለቀለም ወረቀት ፣ የካርቱን ስዕሎች ፣ የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ ወዘተ መጠቀም)<br>**ቃላትን መመስረት፡** ተማሪዎች የቃላት ክፍሎችን በመጻፍ አዳዲስ ቃላትን መመስረት መለማመድ፡፡<br>**ተዘውታሪ ቃላት፡** በከፍተኛ ደረጃ ተደጋግመው የሚነገሩ ቃላትን ለማወቅ ልምድ ማዳበር፡፡ | ቃላዊና ጽሁፋዊ ጥያቄዎችን መጠየቅ፣ አካላዊ ምላሽ፣<br><br>ተማሪዎች አካላዊ ምላሽ በመጠቀም፣ በግል የሚመልሷቸው ጥያቄዎች፣<br><br>ኢ-መደበኛ ቁጥጥር፣ ምልከታ፣<br><br>በስዕል መወከል፣ ተራ በተራ ማቅረብ፣<br><br>ስልታዊ ልምምድ፣ መውጫ ካርድ፣ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | **ቀስበቀስ ማብቃት፡**<br>ሀ. መምህር ፊደላትን በማሳየት መጥራት፡፡<br>ለ .መምህር ፊደላትን እያሳየ ተማሪዎችን ፊደላቱን እንዲጠሩ መጠየቅ፡፡<br>ሐ.ተማሪዎች ፊደላትንና ድምጾችን ማዛመድን መለማመድ፡፡<br>**እንቅስቃሴ፡** ድምጾችን ከእንቅስቃሴ ጋር ማገናኘት፡፡ይህ ተማሪዎች አካላቸውን በማንቀሳቀስ ድምጾችንና ፊደላትን እንዲያስታውሱ ያግዛቸዋል፡<br>**አፋዊ እንቅስቃሴ፡** ተማሪዎች ድምጾች በአንደበታቸው ውስጥ እንዴት እንደሚፈጠሩ መማር፡፡<br>**መናገር** መምህር በቃላት ውስጥ ያሉ ድምጾችን እያሳዩ መጥራት፡፡ ከዚያም ድምጾቹን ማጣመር፡፡ (የታወቁ የፊደል ድምጽ ግንኙነቶችን መጠቀም)<br>**አርአያ፡** መምህር ተማሪዎች ካሏቸው የማንበብ ችሎታ በላይ የሚነበቡ ምንባቦችን በከፍተኛ ድምጽ ማንበብ፡፡<br>**ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ፡** ተማሪዎች ለተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ እንዲጋለጡ እድል መስጠት፡፡<br>**ቀስበቀስ ማብቃት ሞዴል፡** በአመልካች ጣትና መርህን ተከትለው በገደል ማሚቶ ንባብ፣ በጋራ ንባብ፣ ከሌሎች ጋር አብሮ ማንበብ፡፡ በተደጋጋሚ የሚከሰቱ ፊደላትን መቅረጽ | |